# የእውነተኛ ነቢይ አካሄድ

አመሰግናለሁ፡ ወንድም ቦርደርስ። አሁን ስንጸልይ እንደ ቆምን እንቆይ። ዛሬ ምሽት የጸሎት ጥያቄ ኖሮት፡ እጁን በማንሳት፡ “ጌታ ሆይ፡ እኔ ነኝ” የሚል ሰው ይኖር ይሆን? አሁን ራሳችንን ዝቅ እናድርግ።

2 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ “ጌታ ሆይ፡ አምናለሁ” የሚለውን፡ ያንን መዝሙር ስንሰማ፡ በ—በዓለም ዙሪያ፡ ይህንን መዝሙር በብዙ ቋንቋዎች፡ የሰማሁበትን ጊዜ ትዝ ይለኛል፡ “ጌታ ሆይ፡ አምናለሁ።” **እመን ብቻ**። አባት ሆይ፡ ዛሬ ምሽት ይህ ለእኛ ከመዝሙር በላይ እንዲሆንልንና፡ እውነታ እንዲሆን እንጸልያለን። ዛሬ ምሽት በአንተ ላይ ታላቅ እምነት ይኑረን።

3 አሁንም ስለዚህች ትንሽ ቤተ ክርስቲያን፡ ስለ ፓስተሯ፡ ስለ አገልጋይህ፡ ስለ ወንድማችን ፋለር፡ እምነታችንን ስለምንጥልበት ወንድም እንጸልያለን። ስለ ቤተሰቡ፡ እዚህ ስላሉ አገልጋዮች፡ ስለ ዲያቆናት፡ ስለ ባላደራዎችና፡ ወደዚህ የተቀደሰ በር ወደሚገቡት ሁሉ እንጸልያለን። ጌታ ሆይ፡ ሁልጊዜ የኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን ቤት ሆና እንድትቀጥል፡ እንጸልያለን።

4 ዛሬ ምሽት እዚህ ያሉትን አገልጋይ ወንድሞች ሁሉ፡ በመንገድ ሁሉ፡ ከእኛ ጋር አብረው የሚወጡና የሚገቡትን ባርካቸው። አባት ሆይ፡ አትረፍርፈህ እንድትባርካቸው፡ እንጸልያለን።

5 ዛሬ ምሽትም፡ መገኘትህ በላያችን ላይ እንደገና እንዲፈስ፡ እንለምናለን። ጌታ ሆይ፡ የሚያስፈልገን ነገር አለ። ታስፈልገናለህ። ጌታ ሆይ፡ እዚህ ውሳኔዎች በሚሰጡበት፡ በጦር ሜዳ ላይ ስላለን ሁልጊዜ አንተ ታስፈልገናለህ። አባት ሆይ፡ በመገኘትህ ዘወትር እንድታበረታን፡ እንጸልያለን። ከእኛ ጋር መሆንህን ማወቃችን፡ ለእኛ ብዙ ትርጉም አለው። ጌታ ሆይ፡ መገኘትህን ብቻ ግለጥልን፡ ያኔ ወደ ፊት ለመቀጠል ያበረታናል። የታመሙትንና የተቸገሩትን ፈውሳቸው። የጠፉትን አድን። ተስፋ የቆረጡትን አበረታቸው። ክብርንም ለራስህ ውሰድ። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

መቀመጥ ትችላላችሁ።

6 ዳዊት ይመስለኛል፡ “‘ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ’ ባሉኝ ጊዜ፡ ደስ አለኝ” ያለው።

7 ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ ቢሊ፡ እንዲህ አለኝ፡ “አባዬ፡ ትንሽ አልደከመህም? ”

8 እኔም፡ “አዎ። ዘመን ሁሉ እንደደከመኝ ነው ያለሁት” አልኩት። አሁን ግን ለምጄዋለሁ።

9 “እንግዲህ፡ በጣም እያረጀሁ ነው። ትንሽ ቀነስ ማድረግ ይገባኛል፡” ብዬ ማሰብ ጀምሬያለሁ። ከዚያ ደግሞ የእኔን ዕድሜ፡ ሁለት እጥፍ የሚጠጉ፡ ታውቃላችሁ፡ ዕድሜያቸው ሰማንያ ወይም ዘጠና የሆኑ ሰዎች፡ አገሪቱን ሲያቀጣጥሉ አያለሁ። እኔም፡ “እቤት! በራሴ አፍራለሁ” ብዬ አሰብኩ።

10 በዚያ በእኛ አገር በሚገኘው ተበርናክል ውስጥ፡ ከኦሃዮ የሚመጡ፡ ኪድ የሚባሉ ምስኪን አሮጊትና ሽማግሌ ባልና ሚስት አሉ። አሁን፡ ሁለቱም፡

በሰማንያ-አምስት ወይም በሰማንያ-ስምንት ዓመት ዕድሜ ክልል፡ ውስጥ ናቸው። በጣም ከማርጀታቸው የተነሳ… ድምፃቸው ስለማይወጣ፡ ወደ ቤተ ክርስቲያናት በብዛት መሄድ አይችሉም። ነገር ግን ምን እንደሚያደርጉ ታውቃላችሁ? ሁሉም ቴፕ… ይህች ምስኪን አሮጊት ሴት ገንዘቧን ቆጥባ የቴፕ መቅጃ ገዛች። ስለዚህም ቴፖችን ታገኛለች። እኔም ቴፖችን እልክላታለሁ። እነዚህን ቴፖችን ትወስድና፡ ወደ ሆስፒታሎችና፡ ይህን የቴፕ መቅጃ ልታስቀምጥበት በምትችልበት ቦታ ሁሉ በመሄድ፡ እሷና ምስኪን ሽማግሌ ባሏ፡ እነዚህን ቴፖቹን ያጫውታሉ። እኔም የጸለይኩባቸውን ብዙ የ—የጸሎት ጨርቆች እልክላታለሁ። አልፎ አልፎም፡ “ወንድም ዊሊ፡ የጸሎት ጨርቆቹ እንደገና አልቀውብኛል” ትለኛለች። ከዚያም ሳያቸው፡ ጸጉሯ ነጭ ሆኖ፡ ትንሿን ፎጣዋን ደርባ፥ እሱም፡ ትንሽ ምስኪን ሰው፡ ወደ ቤተክርስቲያን ይመጣሉ።

ከአራት ወይም ከአምስት ዓመት በፊት፡ እኔ በ…

11 በየዓመቱ ያን ትልቅ ስብሰባ የሚያደርጉበት፡ የዚያ የኦሃዮ ሰፍራ ሰሙ ምን ነበር? ሾቶኳ ብለው ይጠሩታል። አሁን ግን ረሳሁት። እዚያው ግቢ ውስጥ ነው የሚደረገው። ነገር ግን የ—የከተማዋ ስም፡ አሁን ሊመጣልኝ አልቻለም። [አንድ ወንድም፡ “ፍራንክሊን” አለ። አንዲት እህት፡ “ማያሚ፡ በሚድልታውን በኩል” አለች።—አርታዒ።] አሁን፡ እንግዲህ፡ በጣም ተቃርባችኋል። አንድ ሰው በማያሚ በኩል ነው የምናልፈው አለ። [አንድ ወንድም እንደገና፡ “ፍራንክሊን” አለ።] ወደ ፍራንክሊንም ቅርብ ነው። አዎን። ልክ ነው። በቀጥታ… በፍራንክሊን መካከል ያለ ይመስለኛል… [ሁለት ወንድሞች፡ “ሚድልታውን” አሉ።] ሚድልታውን። ያ ነው። በትክክል። ስለዚህ፡ በትክክል፡ ሚድልታውን፡ ወንዙ ጋ፡ እዚያ ባለው በሾቶኳ ግቢ ውስጥ። ያ ታላቅ የቅርጫት ኳስ፡ የስፖርት ማዕከል ያለበት ሰፍራ ነው።

12 ይህ ወንድም፡ ኦህ፡ ለዓመታት አውቃቸዋለሁ፡ ምስኪን ሽማግሌ ወንድም ኪድ፡ ኦህ፡ ወደ ሆስፒታል ሲወስዱት ዕድሜው ሰማንያ ገደማ ይመስለኛል፡ ሐኪሞቹም የፕሮስቴት እጢው ወደ ካንሰርነት እንደተለወጠ ደረሱበት። ይህ እብጠትም ተጠምጥሞበት ነበር። እንግዲህ፡ ቀዶ ጥገና መደረግ አለበት አሉ። ነገር ግን ሆዱን በከፈቱት ጊዜ፡ “እያችሁ፡ ምንም ቀዶ ጥገና ማድረግ አያስፈልግም። በጣም አልፎበታል” አሉ። አያችሁ? “በጭራሽ፡ የሚደረግበት ምንም መንገድ የለም” አሉ። እንግዲህ፡ ምስኪኑን ሰው ወደ ቤቱ መለሱት። ቀዶ ጥገናው፡ ደግሞ፡ ለሰማንያ-ዓመት-ሽማግሌ በጣም ከባድ ነው። ክብደቱም፡ ኦህ፡ ከመቶ ፓውንድ፡ ያንሳል ብዬ እገምታለሁ።

13 ስለዚህ፡ ወይዘሮ ኪድ፡ ደወለችልኝ። እኔም የሆነ ቦታ ሄጄ ገና ወደ ቤት መመለሴ ነበር። ወንድም ኪድ በሞት አፋፍ ላይ ነበር። “ወንድም ብራንሃም፡ እርሱ… ከመሞቱ በፊት፡ አንተን ማየት ይፈልጋል፡” አለችኝ። እንግዲህ፡ እኔና ቢሊ ተራ በተራ ነዳን። መ—መልእክቱ የደረሰን፡ በአንድ ምሽት፡ አሰር ሰዓት ገደማ ነበር። በማግስቱ ጠዋት፡ በአራት ሰዓት፡ ጉዞ ጀመርን። ምክንያቱም፡ በማግስቱ እኩለ ቀን ላይ፡ እንደገና መሄድ ነበረብኝ። ወደዚያ ለመድረሰም፡ የመኪናችን ጎማዎች ልቀዳዱ እስኪቃረቡ ድረስ ነው የነዳነው።

14 ምስኪን ሽማግሌ ሰው፡ እዚያ ስደርስ አስነስተውት ነበር። በትከሻው ላይ ትንሽ ፎጣ ደርቦ፡ እንደ ጥንት አባቶች እዚያ ተቀምጦ ነበር። ይህ በውስጤ

የሆነ ነገር ፈጠረ። ልመለከተው ስሄድ፡ እርሱም ተመለከተኝ።

15 እዚያ የተቀመጠች ሌላ አሮጊት ሴት ነበረች፡ እርሱ በኬንታኪ ተራራማ የከሰል አገር ይሰብክ በነበረበት ጊዜ፡ የቤተ ክርስቲያኑ አባል ከነበሩት አንዷ ነበረች፡ ባሏ ወጥቶ ወንጌልን እንዲሰብክ፡ በቀን በአሥራ አምስት ሳንቲም ልብስ እያጠበች ባልዋን ታስማራው ነበር። ያ እኔ ከመወለዴ አሥር ዓመት በፊት ገደማ ነበር፥ መልእክቱን ይሰብክ ነበር! እርሱም ተመልክቶ፡ "እያቴ" አላት፡ እርሱ ገና ሰማንያ ዓመቱ ነበር። እሷ ደግሞ ከዘጠና ዓመት በላይ ሆኗታል። እርሱም፡ "እያቴ፡ እንደ በረዶ ነጭ ትመስያለሽ" አላት።

16 በልቤም፡ "አንድ አገልጋይ እዚያ ተኝተው፡ ተቀምጠው፡ ለሞት እያጣጣሩ ያሉትን፡ የጉባኤውን አባላት ሊመለከታቸው የሚገባው በዚህ መንገድ ነው። 'እያቴ፡ እንደ በረዶ ነጭ ሆነሻል' በማለት" አሰብሁ። አዎ።

ከዚያም ዞር ብሎ አየኝ። "ወንድም ብራንሃም፡" አለኝ?

እኔም፡ "አቤት ወንድም ኪድ፡" አልኩት?

17 እርሱም፡ "እንግዲህ፡ ጌታ ሰረገላውን የሚልክበት ጊዜ ብዙ የሚቆይ አይመስለኝም" አለኝ። "ዛሬ ጠዋት፡ ወደ ላይ ልወጣ ነው፡" አለ።

18 እኔም፡ "ድንቅ ነው፡ ወንድም ኪድ" አልኩት። "እንዲህ ሊሰማህ ይገባል፡" አልኩት።

19 ምስኪን አሮጊቷ እህት ኪድስ፡ እዚህ፡ ሰንቶቻችሁ ታውቋታላችሁ? አዎ። ኦህ፡ ብዙዎቻችሁ እንደምታውቋት፡ አውቃለሁ። እሱም... እሷም እንዲህ አለች፡ "ነገር ግን፡ ወንድም ዊሊ፡ እግዚአብሔር አሁን አባዬን ሊፈውሰው ይችላል ብለህ አታስብምን? "

እኔም፡ "እርግጥ ነው፡ ይችላል" አልኳት።

20 እርሱም፡ "እንግዲያውስ፡ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን" አለ! እንዲህም አለ፡ "ሊፈውሰኝ ከፈለገ፡" እርሱ፡ "እ—እንደገና ለመሥራት ዝግጁ ነኝ" አለ።

"በሰማንያ ዓመቱ፡" ብዬ አሰበኩ!

ለመንበርከክ ጀመርኩ። እነሆ ራእይ መጣ። ነገሩ ያ ነበር።

21 ከሁለት ቀናት በኋላ፡ ተመልሰው ወደ ሆስፒታል ወሰዱት። ልጆቹ በከተማዋ የፖሊስ አባላት ነበሩ። ነገሩ ሊገባቸው አልቻለም ነበር። ወደ ሐኪሙም ወሰዱት። ሐኪሙም ራሱን እያከከ፡ እንዲህ አለ፡ "አንተ ሰው፡ ምንም ዓይነት ምልክት እንኳን ማግኘት አልቻልኩም፡ አሁን፡ እስቲ ምን እንደተፈጠረ ንገረኝ" አለው። እርሱም በደስታ ሆስፒታሉን ሊያናውጠው ምንም አልቀረውም ነበር። ወዲያውኑ ወደ ቴፕ መቅጃው ተመልሶ፡ እነሆ፡ መልእክቱን እያጫወተ ቀጠለ። እነርሱም እዚያው... በዚያ በችዋታኳ አቅራቢያ ይኖራሉ።

22 አሁን፡ ልክ **የሰባቱን የቤተ ክርስቲያን ዘመናት** ትምህርት እንዳደረግነው፡ **የሰባቱን ማኅተሞች** ትምህርት ሰጀምር፡ በቀደም ምሽት ደውላ፡ እንዲህ አለችኝ፡ "እንግዲህ፡ ማር፡ ገንዘብ ቢኖረኝ ኖሮ፡" እንዲህ አለች፡ "በእርግጥ መምጣት እፈልግ ነበር" አለች።

23 እኔም፡ “እርሺው፡ ወይዘሮ ኪድ። ክ—ክፍልሽ ተዘጋጅቷል። አንቺና ባለቤትሽ ዝም ብላችሁ ኑ” አልኳት።

እሷም አለችኝ፡ “ትንሿ ልብህ ትባረክ!”

24 ይህ በእውነት ደስ ያሰኘኛል፡ ታውቃላችሁ፡ ምክንያቱም እነርሱ ያበረቱኛል። በሰማንያ-አምስት ወይም ሰማንያ-ሰድሰት ዓመት ዕድሜያቸው፡ አሁንም እያገለገሉ ነው። እኔ ደግሞ፡ ገና በሃምሳ-ሦስት ዓመቴ፡ እማረራለሁ። ስለዚህ፡ አቤት፡ ብርታት እንድታገኙ ያደርጋችኋል።

25 እንግዲህ፡ ለመናገር እንዲህ ያለ ደስ የሚል ጉባኤም ስላለ፡ የምናወራው ብዙ ነገር አለ፡ ለምን፡ እኩለ ሌሊት እስኪሆን ድረስ እዚሁ መቆየት እንችል ነበር።

26 ነገር ግን ነገ ጠዋት ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ትሄዳላችሁ። እንግዲህ፡ መሄዳችሁን እርግጠኞች ሁኑ። እስታውሱም፡ ሁልጊዜም እንደምለው፡ ልጆቻችሁን ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት መላክ ፍጹም ኃጢአት ነው። በጭራሽ እንደዚያ አታድርጉ። ያ ስህተት ነው። ሁልጊዜም ይዛችኋቸው ሂዱ። አያችሁ? ሁልጊዜም አብራችኋቸው ሂዱ። እሱ… ስለዚህም፡ አሁን፡ ያ ነገ ጠዋት ነው።

27 ስለዚህ፡ አሁን፡ እኛን ለመስማትና፡ አብራችሁን ለመሆን ከእኛ ጋርም ለመጸለይና፡ ወዘተ፡ ሰትሉ ሥራችሁን መቅረት ቢኖርባችሁ፡ ሰራውን መቅረት አለባችሁ፡ ያ ምንም ችግር የለውም። ቀጥሉ ሥራችሁን ቅሩ ችግር የለውም፡ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያናችሁን እንዳትቀሩ። ቤተክርስቲያን እንዳይቀርባችሁ። ቤተ ክርስቲያን እንድትቀሩ የሚያደርግ ያህል አላዘገያችሁም። ነገር ግን አልፎ አልፎ፡ ሥራ መቅረት ቢኖርባችሁ፡ ያ ምንም አይጎዳችሁም። አሁን፡ ምክንያቱም፡ ሥራ፡ የዕለት ጉርሳችሁ ብቻ ነው፡ እናም፡ ለእናንተ፡ ጌታ ራሱ ያንን እንደሚያዘጋጅላችሁ ቃል ገብቷል። ስለዚህ፡ ግን፡ ይህ፡ ቤተ ክርስቲያን መምጣታችሁን በእውነት እርግጠኛ መሆን አለባችሁ። አያችሁ?

28 ነገ ጠዋት፡ እዚህ ከተማ ውስጥ ካለ ሌላ ጥሩ ወንድም ጋር የማሳልፍ፡ ይመስለኛል። ነገር ግን አሁን ሰሙ ማን እንደሆነ አላውቅም። የአፖስቶሊኩ ቸርች፡ ወይም አፖስቶሊክ ቸርች፡ የሚባል ይመስለኛል። የአፖስቶሊኩ ቸርች ነው። ምናልባት ያ ወንድም አ—አውቀው ይሆናል። ሰሙ ወረቀቱ ላይ የለም። ነ—ነገር ግን ይህ ወንድም ማን እንደሆነ አሁን አላውቅም። ከዚያም ነገ ምሽት፡ ማዶ ላይ… [አንድ ወንድም፡ “ሜሲያስ” አለ።—አርታዒ።] አቤት? [“ወንድም ሜሲያስ።”] ወንድም ሜሲያስ። ኦህ፡ ሜሲያስ። ኦህ፡ የሜክሲኮ ቤተ ክርስቲያን። ልክ ነው? ኦህ፡ ወንድም ጋርሲያ ከዚህ ሲሄድ በእርሱ ቦታ የተተካው እርሱ ነውን? [“በትክክል።”] መልካም። በጣም ጥሩ ነው።

29 በነገራችን ላይ፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ ከሴቷ ልጁ፡ ደብዳቤ ደርሶኝ ነበር፡ ከ… ወንድም ጋርሲያ፡ እ—እዚያ ካሊፎርኒያ ውስጥ፡ አሁንም እንደበረታ ነው። ስለዚህ፡ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው። ወንድምና እህት ጋርሲያን ያየኋቸው በሳን ሆሴ ሳለሁ፡ ይመስለኛል፡ ከወንድም ቦርደርስ ጋር እዚያ። በጥሩ ሁኔታ ላይ ናቸው። በዚያች ትንሽ የሜክሲኮ ቤተ ክርስቲያን ያሳለፍናቸውን ምሽቶች መቼም አልረሳቸውም። በሕይወቴ ዘመን ሁሉ እንዲህ ያለ “ግሎሪያ አዲዮስ” የሚል አባባል ሰምቼ አላውቅም ነበር። ያንን መቼም አልረሳውም፡ “ግሎሪያ አዲዮስ።”

30 [ወንድም ዊሊያምስ ለወንድም ብራንሃም ተናገረው—አርታዒ።] ማይ! አመሰግናለሁ፡ ወንድም ዊሊያምስ። ያ ጥሩ ነው። ነገ ጠዋት፡ በዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፡ አንድ ሺህ አምስት መቶ መቀመጫዎች አሉ። በሉ፡ ሁላችሁም ወደዚህ ኑ፡ የሆነ… አሁን፡ አንድ ደቂቃ። ስለዚህ ነገር ብጠነቀቅ ይሻላል። ያኔ የሆነ የተሳሳተ ነገር ተናግሬ ነበር። አይደለም። በሙሉ ቅንነት፡ እያንዳንዱ ሰው በተመደበበት በዚያ የኃላፊነት ቦታው ላይ መገኘት አለበት። አያችሁ? እ… አሁን፡ ይሁን ችግር የለውም።

31 ዛሬ ደግሞ የገጠመኝ… አንድ ድንኳን አየሁ። እዚህ ሰክሰቲንዝ ኤንድ ሄንሾው አካባቢ ነበርኩ። ወይም፡ ከሰላሳ-አምስት ዓመታት በፊት፡ እዚህ አሪዞና ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ፡ ቦታው እንዲህ ነበር የሚባለው፡ ያኔ ያረጀ የአፈር መንገድ ነበር። እነርሱ ወዳሉበት ወጣሁ፡ ሰክሰቲንዝ ኤንድ ሄንሾው ነበር። እዚያ ፍራንሲስኮ፡ ከተወሰኑ ሰዎች ጋር እኖር ነበር፡ እ—አሁን ግን ያንኑ ቦታ እንደሆነ ፈጽሞ አታውቁትም። ሰሙ ሳይቀር ተቀይሯል። አሁን ባክአይ ሮድ ይባላል መሰለኝ።

አቤት፡ ነገሮች ሁሉ እንዴት፡ እንደሚለወጡ፡ እግዚአብሔር ግን አይለወጥም።

32 ስለዚህም እዚያ በነበርኩበት ጊዜ አንድ ወንድም የድንኳን ስብሰባ ሲያደርግ አየሁ። ድንኳን የዘረጋ አንድ ወንድም በዚያ አቅጣጫ ነበር። እርሱን ላገኘው እችል እንደሆን ዞር ዞር ብዬ ነበር፡ ነገር ግን የትም አላገኘሁትም፡ እኛ እዚህ የመጣነው ከእርሱ ጋር ለመወዳደር እንዳልሆነ ልነግረው ፈልጌ ነበር። ነገር ግን፡ እዚህ በጣም ብዙ ሕዝብ አለ!

33 ጃክ ሹለርን አስታውሳለሁ። ይህ ለእናንተ ለሜቶዲስት ወገኖች ጥሩ ይሆናል። አንድ ጊዜ እዚህ በመጣሁበት ወቅት፡ በማዲሰን ስኩዌር ጋርደን ሳለሁ፡ ጃክ ደግሞ እዚህ በ—በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ አካባቢ ነበር። እ—እኔም ደወልኩለት። አልኩትም፡ "ወንድም ጃክ? "

እርሱም፡ "አቤት፡ ወንድም ብራንሃም ነህ" አለኝ?

እኔም፡ "አዎን" አልኩት። "እየተሻማሁብህ ነው፡" አልኩት።

34 እርሱም፡ "አይ" አለ። "አይ። እኔ ረጅም ጊዜ ስለቆየሁ የአንተን ጊዜ ተሻማሁ እንጂ፡" አለኝ።

35 እኔም፡ "ኦህ፡ አዝናለሁ፡ ወንድም ጃክ" አልኩት። እኔም፡ "እኔ… "

36 "እህ፡" እ—እንዲህ አለ፡ "ምንም አይደለም፡ ወንድም ብራንሃም" አለኝ። "እንድቆይ ፈልገው ነው፡" አለኝ።

37 እኔም፡ "ኦህ፡ በርግጥ፡ የእኔ ቡድን እዚያ አንተ ጋር አይረብሽህም ጃክ፡" አልኩት፡ "ምክንያቱም የእኔ ሰዎች ብዙዎቹ ጴንጤቆስጤዎች ናቸውና፡" አልኩት።

እርሱም፡ "እርግጥ ነው፡ የእኔም፡ እንደዚያው ናቸው" አለኝ።

እኔም፡ "ነው'ዴ" አልኩት?

"ታዲያስ፡" "በእርግጠኝነት፡" አለኝ። "እኔም ጴንጤቆስጤ ነኝ፡" አለኝ።

38 እኔም፡ “እንግዲያውስ፡ ይህንን ቦብ እንዲያውቅ ብታደርግ ይሻላል” አልኩት። አባቱ ነው፡ ታውቃላችሁ፡ እርሱም ደግሞ፡ እንደምታውቁት፡ አጥባቂ፡ ሜቶዲስት ነው።

39 “እንግዲህ፡” አለ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ጴንጤቆስጤ ማ—ማለት ምን ማለት እንደሆነ አታውቅምን? ”

እኔም፡ “የማውቅ ይመስለኛል” አልኩት።

እርሱም፡ “ኦርቶዶክስ ሜቶዲስት ማለት ነው” አለኝ።

40 ይህ በትክክል ልክ ነው፡ ኦርቶዶክስ ሜቶዲስት። በትክክል። የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን በመልእክቷ ብትገፋበት ኖሮ፡ ቀጥታ ወደ ጴንጤቆስጤነት በገባች ነበር። እ—እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ገብታለች።

41 አይደለም፡ አሁን ለሃይማኖት ተቋማችሁ ማንቋሸሼ አይደለም፡ ወንድሜ። አያችሁ? ምክንያቱም፡ ጴንጤቆስጤ ድርጅት አይደለም። ያንን ለማድረግ ሞክረው ነበር፡ ነገር ግን በእርግጥ አልተሳካላቸውም። አያችሁ? ልምምድ ነውና። አዎን። ጴንጤቆስጤ ለካቶሊኮች፡ ወ—ወይም ለአይሁዶች፡ ወይም ለማንኛውም ሰው ነው... ጴንጤቆስጤ ልምምድ እንጂ፡ ድርጅት አይደለም።

42 አሁንም መጽሐፍ ቅዱሳችሁን የከፈታችሁ፡ ወይም ዘግታችሁ ያስቀመጣችሁ፡ አብራችሁኝ ጥቂት ቃላትን ለማንበብ የተዘጋጃችሁ ሁሉ። ቃሉን ማንበብ እወዳለሁ፡ እናንተስ? ምክንያቱም፡ በመጨረሻ፡ እኔ ያልኩት ሊወድቅ ይችላል፡ ሰው ነኝና። እርሱ የሚለው ግን ሊወድቅ አይችልም። አያችሁ? “ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን አያልፍም።” ኦህ! ይህ ድንቅ አይደለምን? ቃሉ ፈጽሞ አይወድቅም። ምንኛ ክቡር ነገር ነው! ቃሉ ፈጽሞ አይወድቅም።

43 አሁን ዛሬ ማታ ከሚከተሉት ጥቅሶች፡ ትንሽ አውድ እንሳል፡ እንደ ጌታ ፈቃድ፡ ርዕስ ከማወጣበት ክፍል እናነባለን። እርሱም በአሞጽ መጽሐፍ፡ በአሞጽ ትንቢት ውስጥ ይገኛል። እርሱም የኖረው ክርስቶስ ከመምጣቱ ሰባት መቶ... ሰባት መቶ ሰማንያ-ሰባት ዓመታት ገደማ በፊት ይመስለኛል። በአሞጽ ወደተነገረው የእግዚአብሔር ቃል፡ ወደ አሞጽ ምዕራፍ 3 እንክፈት። ይ—ይህ ሰው እወደዋለሁ። ከአናሣዎቹ ነቢያት አንዱ ተደርጎ ይቆጠራል፡ ነገር ግን በእርግጥም የእግዚአብሔር ቃል ነበረው።

**የእስራኤል ልጆች ሆይ እግዚአብሔር በእናንተ፡ ከግብጽ ምድር ባወጣሁት ወገን ሁሉ ላይ የተናገረውን፡ ይህን ቃል ስሙ፡ እንዲህም ብሎአል፡**

**እኔ ከምድር ወገን ሁሉ... እናንተን ብቻችሁን አውቄአችኋለሁ፥ ስለዚህ ስለ ኃጢአታችሁ ሁሉ እበቀላችኋለሁ።**

**በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ፡ በአንድነት ይሄዳሉን?**

**ወይስ አንበሳ የሚነጥቀው ነገር ሳያገኝ፡ በጫካ ውስጥ ያገሣልን? ወይስ የአንበሳ ደቦል አንዳች ሳይዝ፡ በመደቡ ሆኖ ይጮኻልን?**

**ወይስ ወፍ አጥማጅ ከሌለው፡ በምድር ላይ በወጥመድ ይያዛልን? ወይስ ወስፈንጠር አንዳች ሳይዝ፡ ከምድር ይፈነጠራልን?**

**ወይስ በከተማ ውስጥ መለከት** ሲነፋ፡ **ሕዝቡ አይፈራ**ምን? **ወይስ ክፉ ነገር በከተማ ላይ የመጣ እንደ ሆነ፡** ያደረገው **እግዚአብሔር አይደለምን?**

**በእውነት ጌታ...** ምሥጢሩን **ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም።**

**አንበሳው** አገሣ፡ **የማይፈራ ማን ነው? ጌታ እግዚአብሔር** ተናገረ፡ **ትንቢት የማይናገር ማን ነው?**

44 ጌታ በእነዚህ ቃላት ላይ በረከቱን ይጨምር።

45 ያ ጠዋት ሞቃቱ ፀሐይ፡ ነጭ ጺሙንና ጸጉሩን ሲመታው ከሰማርያ በስተሰሜን ያለውን ኮረብታ ወጥቶ ከተማዋን ቁልቁል ሲመለከት፡ ትንንሽ ዓይኖቹ ጠበብ ሳያደርግ አልቀረም። ልብሱ ተራ፡ እግሮቹም አቧራማ ነበሩ። ሲታይ ያን ያህል ማራኪ ሰው ባይሆንም፡ ለሕዝቡ የሚሆን **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነበረው።

46 የዛሬው ዘመናዊ የወንጌል አገልግሎታችን ከእርሱ ምንኛ የተለየ ነው! እርሱ ከነበረው ይልቅ፡ እኛ ያለን ነገር ምንኛ የተለየ ነው!

47 ይህ አሞጽ የተባለው፡ ምስኪን ሰው፡ ለዚያ ኃጢአተኛ ትውልድ፡ የእግዚአብሔርን ቃል የያዘ፡ እውነተኛ የጌታ ነቢይ ነበር! ፍርሃት አልባው፡ ይህ ትንሽ ሰው በኢዮርብዓም ሁለተኛው ዘመን ትንቢት ተናገረ።

48 ኢዮርብዓም ብልህ፡ በጣም ብልህና፡ ጥበበኛም ሰው ነበር፡ ሆኖም ጣዖት ያመልክ ነበር። ኢዮርብዓም መንግሥቱን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ጫፍ አድርሶት ነበር፡ ነገር ግን በጣዖት አምልኮ ውስጥ ነበረ። ያደረገውም በተሳሳተ መንገድ ነበር። ነገር ግን በኢዮርብዓም ስር መንግሥቱ በልጽጎ ነበር።

49 ብዙውን ጊዜ፡ ብልጽግና፡ ለኃጢአት ምክንያት ይሆናል። ብዙ ሰዎች ብልጽግናን እንደ በረከት ይመለከቱታል። በአግባቡ ብንጠቀምበት፡ በረከት በሆነ ነበር። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔርን ወደማያከብር፡ ኃጢአት ይመራል።

50 በእርሱ ዘመን መንግሥቱም ሆነ ሕዝቡ፡ ይበለጽጉ ያብቡ ነበር። በዙሪያው ካሉ አገሮች ሁሉ ጋርም ሰምምነት ኅብረት አድርጎ ነበር።

51 እስራኤል እንዴት ወደ አስከፊ ኃጢአት እንደተንሸራተተች፡ ከእግዚአብሔር፡ ከትእዛዛቱና ከሥርዓቱ እንደራቀች፡ እንዲሁም ሙሉ በሙሉ፡ ልጓም አልባ ወደ መሆን፡ እንደሄደች አስተውሉ። ሴቶቹ ነውር በሆኑ፡ ውብ ልብሶቻቸው፡ በጎዳናዎች ይሄዱ ነበር። ወንዶቹም ቁማር እየተጫወቱና እየጠጡ፡ ይዞሩ ነበር። ዛሬ የመዝናኛ ስፍራዎች የምንላቸው፡ የምሽት ቤቶች፡ በከተማዋ በየቦታው ተከፍተው ነበር።

52 ኃጢአት በአገልጋዮች ዘንድ ቸል ተባለ፡ እንዲሁ በግልጽ ተተወ። ውብ ስፍራ፡ ታላቅ የቱሪስቶች ማዕከል ነበረች፡ በገሃዱ ተከፍታ ነበር። ኃጢአት ከመድረክ አይገሰጽም ነበር። ልቅ ሆኖ ነበር።

53 ይህ ትንቢት ሲወጣ፡ ይመስል የነበረው ሊሆን የማይችል... ሊከሰት የሚችለው የመጨረሻው ነገር ይመስል ነበር። ይህ ነቢይ ያንን ትውልድ ከረገመበት መንገድ አንጻር፡ እንደተናገራቸው፡ በእነርሱ ላይ ሊደርስ የሚችለው የመጨረሻው ነገር ይህ ይሆናል። ሆኖም፡ ግን፡ በሃምሳ ዓመታት ውስጥ፡ መንግሥታቸው ከምድር ገጽ ፈጽሞ ጠፋ።

54 እግዚአብሔር ቃሉን ይናገራል። የእግዚአብሔርም ቃል እንደ ዘር ነው። ሲዘራም፡ ያ ነቢይ የእግዚአብሔርን ቃል ይዞ መጥቶ እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ቃላት ከሆኑ፡ መፈጸም ነበረባቸው። የ—የእግዚአብሔር ቃል የተቀባ ከሆነ፡ እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ፡ በጊዜው ሰፍራውን መያዙ መፈጸሙ አይቀሬ ነው።

55 ከሺህ ዓመታት በኋላም፡ ዛሬ ሰፍራውን ሲይዝ፡ እያየነው ነው። እርሱ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነና፡ ሊጠፋ ስለማይችል፡ መፈጸሙ አይቀሬ ነው።

56 ሰሞኑን አንድ ሰው እያነጋገረኝ ሳለ፡ እንዲህ አለኝ፡ "የዘፍጥረት መጽሐፍና፡ እግዚአብሔር የተናገረው የሰድስት ቀናት የፍጥረት ታሪክ፡ ስህተት ነው።"

57 እኔም፡ "ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እስከ (ዘፍጥረት) 2 ፍጹም የተለያዩ ነገሮች ናቸው" አልኩት። የዘፍጥረት 1ኛው ምዕራፍ የሚለው፡ "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ነው" አለቀ። እንዴት እንደፈጠረውና፡ መቼ እንደፈጠረው፡ የእርሱ ጉዳይ ነው። አዎን። ከዚያም፡ "ምድርም ባዶ ነበረች፡ አንዳችም አልነበረባትም" ይላል፡ ፍጥረት በተመለከተ የምንጀምረው፡ ከዚያ ነው። ነገር ግን፡ ያ "መጀመሪያ" የተባለው፡ ምን ያህል ርቀት እንደሆነ፡ አናውቅም። ውኃው ገለል ባለ ጊዜ እዚያ ከነበሩት ዘሮች ሁሉ፡ ሕይወት እንደገና ወደ ምድር ተመለሰች፡ ምድርንም ሞላቻት። የእግዚአብሔር ቃል ሲዘራ፡ እንዳይፈጸም ሊያግደው የሚችል ምንም ነገር የለም።

58 ይህ ደፋርና ትንሽ ነቢይም ከየት መጣ ሳይባል ድንገት ተገለጠ። ስለ እርሱ የተነገረን ብቸኛው ነገር፡ እረኛ እንደነበረ ብቻ ነው። አባቱ ማን እንደሆነ አናውቅም። እናቱ ማን እንደሆነች አናውቅም። ትውልዱ ከየት እንደሆነም፡ ሆነ ስለ እርሱ ምንም አናውቅም።

59 ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች ብዙውን ጊዜ በቦታው ብቅ የሚሉት በዚህ መንገድ ነው። ከየት መጡ ሳይባሉ ይመጣሉ፡ በዚያውም መንገድ ይሰወራሉ። ምን እንደሆነ፡ የሚገልጽ ምንም ዓይነት መረጃ አልነበረንም።

60 ይህ ታ—ታላቅ የአእምሮ ብቃት የነበረው፡ ታላቅ ሰው ኢዮርብዓም፡ ሕዝቡን በብልጽግና ውስጥ ያኖረ ነበር፡ ሆኖም፡ በኃጢአት ውስጥ ነበር።

61 ዛሬ ምሽት ያንን ሁኔታ አገራችን፡ ህዝባችን ካለበት፡ የኃጢአት ሁኔታ ጋር፡ ትንሽ ማመሳሰል ብንችል ብዬ እሰባለሁ። ሆኖም፡ ብልጽግና አለ፡ የታክስ ቅናሽ በቅርቡ፡ እንደሚደረግም፡ ሰምቻለሁ። እርግጥ ነው፡ ምርጫ እየመጣ ስለሆነ፡ ማንኛውም ሰው ከዚህ በስተጀርባ ያለውን ሊረዳው ይችላል። ነገር ግን፡ እነዚህን የመሳሰሉ፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች እየተከናወኑ ነው።

62 የእስራኤል፡ ሰባኪዎች፡ ካህናትና፡ መንግሥት የእግዚአብሔርን ቃል ትተው፡ ሲያመቻምቹ ነበር። ምንም እንኳ እንደ ድሮው ብዙ ካህናትና፡ ሰባኪዎች ቢኖሯቸውም፡ አገሪቱ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ያለችው ለዚህ ነው። ነገር ግን

የእግዚአብሔርን ቃል ትተው፡ ከእርሱ ርቀው ነበር። ሁልጊዜም እንደዚህ ባለ ጊዜ፡ እግዚአብሔር ነገሩን ወደ ትክክለኛው መንገድ እንዲመልስ፡ በድንገት የሆነ ሰው ይልካል። የሆነ ደፋር ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ይዞ ይነሳና ሕዝቡን ወደ ቃሉ እንዲመለሱ ያናውጣቸዋል።

63 እዚህ ጋር እያስተዋልኩ ነበር። እንደገና ልጠቅሰው የፈለግሁትን፡ አንድ ነገር እዚህ ጽፌ ነበር። እርሱም በምዕራፍ 2፡ ቁጥር 4 ላይ ይገኛል። ላነብበው እወዳለሁ። ይህ ትንሽ ሰው እንዲህ ሲል አዳምጡት።

> **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ የእግዚአብሔርን ሕግ ጥለዋልና፡ እናም... ትእዛዙንም፡ አልጠበቁምና፥ አባቶቻቸውም የተከተሉት ሐሰታቸው አስቶአቸዋልና፡ ስለ ሦስት፡ ወይም ስለ አራት የይሁዳ ኃጢአት መቅሠፍቴን ከማድረግ፡ አልመለስም፥**

64 መልእክቱ ምን እንደነበረ አያችሁ? በቀጥታ የሚመልሳቸው ነው፡ ከእግዚአብሔር ቃል ርቀው ነበርና። ለማንኛውም መጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ፡ ይህ እውነተኛ ነቢይ መሆኑን ያሳውቃችኋል። ከወደቁበት ስፍራ፡ ወደ ቃሉ በቀጥታ መለሳቸው።

65 ኦህ፡ ምናልባት አብያተ ክርስቲያናቸው በልጽገው ነበር። ጥሩ ሕንጻዎች ነበሯቸው ይሆናል። ከተማቸውም ምናልባት ከፊኒክስ ይልቅ ያሸበረቀች ነበረች። ሁላችንም እንደምናውቀው፡ ሰማርያ፡ ታላቅ የቱሪስት ማዕከል ነበረች። አሁንም ቢሆን፡ ውብ ስፍራ ናት።

66 ሆኖም፡ ግን፡ ከእግዚአብሔር ርቀው ነበር። እግዚአብሔርም ይህንን መልእክተኛ ላከላቸው። እንዴት ያለ ከእግዚአብሔር የመጣ የተግሣጽ መልእክት ነው! ይህ ትንሽ ነቢይ መልእክቱን ይዞ ወጣ።

67 አሁን፡ አሞጽ ከበረሃው ወጥቶ፡ ወደዚያች የተሸሞነሞነች ከተማ መጣ። ኮረብታው ጫፍ ላይ ሲደርስ ከእግዚአብሔር-የተሰጡት ትንንሽ ዓይኖቹ መጥበባቸው አያስደንቅም። እርሱም...

68 እንደ ቱሪስት፡ እመቤቶች፡ እንደሚሉት፡ "ሴቶቹ የሚያደርጉትን ግብይት ሁሉ ተመልከቱ። እዚህ ያመጧቸውን አዳዲስ ፋሽኖች እዩ፡" ብሎ ለማለት፡ ወይንም አንዳንድ ወንዶች እንደሚያስቡት፡ "የቁማር ቤቶቹና የመሳሰሉት በከተማዋ ውስጥ በጣም ድንቅ ነበሩ፡" ብሎ አላሰበም፡ ወይንም በመንገድ ጥግ ተቀምጠው የሚያልፉትን ተቃራኒ ጾታዎች በፍትወት እንደሚመለከቱ አይደለም።

69 ነገር ግን ይህ ነቢይ፡ ዓይኖቹ የጠበቡት በከተማዋ ባየው ኃጢአት ምክንያት ነበር። በሚያደንቃቸው ነገሮች ምክንያት ሳይሆን፡ ነገር ግን የተጠሩትና የተመረጡት እነዚያ ሕዝቦች፡ ከእግዚአብሔር ምን ያህል እንደራቁ በማየቱ ነበር። እዚህ ጋር አስተዋላችኋል? እንዲህ አለ፡ "ከእናንተ በቀር ሌላ ሕዝብ አላውቅም። ከግብፅ አወጣኋችሁ፡ እናንተ ግን እንደዚህ ትታችሁኝ ሄዳችሁ።"

70 ይህ ነቢይ፡ በሰተሰሜን ካለው አገር ከእረኝነት ተነስቶ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ይዞ ሲመጣ፡ ያቺን ከተማ እንዴት እንዳያት እስቲ አስቡት። ላቡን ጠረግ አድርጎ መሆን አለበት። ልብሱ የተጎሳቆለ ነበር። ምናልባት ለ—ለዚያች

ሌሊት የሚያርፍበት ክፍል የሚከራይበት በቂ ገንዘብ አልነበረውም። ይህም ለእርሱ ምንም ልዩነት አልፈጠረበትም። በልቡ ውስጥ የሚነድ መልእክት ነበረው፡ እርሱንም መናገር ነበረበት። ያ ብቻ አይደለም፡ እዚያ በረሃ ውስጥ ሳለ ያገኘው የመንፈስ ቅዱስ ቅባት፡ የዓለም ድምቀት እንዳይታየው ዓይኑን ጋርዶት ነበር።

71 ማንኛውም የተቀባ የክርስቶስ አገልጋይ፡ ዓይኑ ከዚህ ዓለም ነገሮች የታወረ ነው። እነዚያን ነገሮች አያዩም። አይፈልጓቸውም። አንድ ነገር ብቻ ነው ያላቸው፥ ክርስቶስ በፊታቸው ነው። የሚያዩት ያንኑ ብቻ ነው። ምንም ነገር አይፈሩም። ክርስቶስ በፊታቸው ነው። መልእክቱ ግዴታ ለሕዝቡ መድረስ አለበት፡ ለዚህም በምንም ነገር አይቆሙም። ያንን ከውስጣቸው አውጥታችሁ ማቃጠል አትችሉም። እስር ቤት፡ ወይም ወህኒ፡ የፈለጋችሁትን አድርጉባቸው። እንደገና ከዚያ ውስጥ ወጥተው ይመጣሉ። ይህም የጌታ ቅባት ነው። አዎን።

72 እርሱ የከተማይቱን መንፈሳዊ መበስበስ፡ የሥነ ምግባር ብልሹነትና፡ የከተማይቱን መንፈሳዊ መበስበስን ተመለከተ።

73 ስንት የጌታ አገልጋዮች ይሆን እዚህ ከላይ ያለውን ተራራ አቋርጠው ሲወርዱ፡ ፊኒክስን የሚመለከቷት? ወደዚህ የምትመጡት ለድምቀቱ፡ ለፀሐይ ብርሃኑም ሆነ፡ ለማረፍ ነው፡ ያንንም አቃለን መናገር አንችልም።

74 በቅርቡ፡ ባለፈው እዚህ በነበርኩበት ወቅት፡ በሳውዝ ማውንቴን ላይ ተቀምጬ ሳለሁ፡ ባለቤቴ እዚያ ኋላ ነበረች፡ እኔም እያወራኋት ነበር። እንዲህም አልኳት፡ "ከሦስት ወይም ከአራት መቶ ዓመታት በፊት፡ ይህ ሸለቆ የሶልት ሪቨር በውስጡ ሲፈስ፡ ተኩላዎች ሲዞሩበትና፡ ወዘተ፡ ቁልቋሎች ሲያብቡበት፡ ያለጥርጥር ውብ ስፍራ ነበር። አሁን ግን እንዴት እንደሆነ ተመልከቺ... ነገሩ ሁሉ የኃጢአት ክምችት ሆኗል።"

እሷም፡ "ታዲያ፡ አንተን ወደዚህ ያመጣህ ምንድን ነው" አለችኝ?

75 እኔም እንዲህ አልኳት፡ "ወደዚህ ያመጣኝ ይህ ነው። በከተማይቱ ውስጥ ባለው በዚያ ጨለማና ኃጢአት መካከል እንኳ፡ እዚያ ታች፡ የጌታ ምስክሮች፡ ሕያው የክርስቶስ አምሳያዎች አሉ። እኔም ከእነርሱ ጋር ትከሻዬን ለመግጠምና፡ የወንጌልን ብርሃን ለማብራት መጥቻለሁ። እዚያ የሆነ የመንገድ ዳር ጥግ ላይ ሆነው በልባቸው ውስጥ ያለውን መልእክት ይዘው፡ በላባቸው፡ በለቅሶና በጸሎት፡ ሥራውን የሠሩ፡ አንዳንድ አዛውንት ወንድሞች አሉ። ያልተበረዘውን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ብርሃን፡ በዚህ ታላቅ የፊኒክስ ከተማ አካባቢ ለማብራት ድርሻዬን ከእነርሱ ጋር ለማበርከት መጥቻለሁ" አልኳት።

76 በውስጧ፡ ምንም እንኳን፡ ድንቅ ስፍራ ልትሆን ብትችልም፥ ሰው ማድረግ የቻለውን ሰኬቶቹን ብቻ ወስዶ፡ እንደ ካሜልባክ ተራራ፡ ካቫሊየር ተራራ ላይ እንዳሉት ያሉ ውብ ቤቶችን ለመገንባት ቢጠቀምበት። በዚያ ሳልፍ፡ ለምን፡ ከሰላሳ-አምስት ዓመታት በፊት፡ ያ ቦታ በረሃ ነበር። በፈረስ ጀርባ ሆነን እህዮችን በዚያ እናባርር ነበር። እዚህም በሳውዝ ማውንቴን፡ እህዮችንና ፈረሶችን እናባርር ነበር።

77 አሁንም የዚች ድንቅ ከተማ መትሮፖሊታን አካባቢ ሆኗል። በሺዎች በሚቆጠሩ እእላፋት ሕዝብ እያደገ ነው። ከተማይቱ እስከ ተሰፋፋች ድረስ፡

የራሷ መበሰበስ ወደ ትርምስ እያመጣት ነው። ጉም እየገባ ነው። የእርጥበት መጠኑም፡ በኢንዲያና ጄፈርሰንቪል፡ በኦሃዮ ሸለቆ እንዳለው የከፋ ሆኗል። መስኖ... ሰው ሁልጊዜም ዓለምን ይበክላል። ኢንዲያኖች በያዙት ጊዜ፡ ውብ ስፍራ ነበር። ነጭ ሰው በመጣ ጊዜ ግን፡ ኃጢአቱን፡ መጠጡንና፡ ብልግናውን ይዞ መጣ። ምድሪቱንም የቆሻሻ ጉድጓድ እስክትመስል ድረስ በክሏታል። ለማየት የሚከብድ ነገር ነው! እግዚአብሔር ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፡ ከምድር ገጽ ጠራርጎ ያጠፋታል።

78 እርሱም እንደ ንጉሥ እንደሚነግሥ፡ በምድር ላይ የሚነግሡ፡ የጽድቅ ሕዝቦችን፡ እየመረጠ ነው። አሁን ለሰሙ የሚሆኑ ሕዝቦችን፡ ለመንግሥቱ የሚሆኑ ሕዝቦችን እየወሰደ ነው።

79 አሁን፡ ይህ ብልህ፡ አስተዋይና፡ ምሁር የሆነው የእስራኤል ህዝብ፡ ታላቁ፡ ኃያሉና፡ ምሁሩ፡ ፕሬዚዳንታቸው፡ ወይም፡ ንጉሣቸው የሆነው፡ ብልሁ ሰው፡ ኢዮርብዓም፡ ይህንን፡ ትንሽና፡ የማይታወቅ ነቢይ ይሰሙት ይሆን? በልቡ ውስጥ በሚቃጠለው፡ በዚህ ታላቅ መልእክት፡ በጎዳናዎቹ ላይ ሲመላለስ፡ ሰዎችስ፡ ሴቶቹስ፡ እንደገና በስርዓት ይለብሱ ይሆን፡ ወንዶችም መጠጥ ቤቶችንና የኃጢአት ሰፍራዎችን ትተው፡ በዚህ ትንሽ ያልታወቀ ሰው ሰብከት፡ ወደ እግዚአብሔር ይመለሱ ይሆን? እዚያ ቆሞ፡ ትንሿ ራስ በረሃ ጭንቅላቱ፡ በፀሐይ ላይ ስታንፀባርቅ ሳየው፡ ይህ ጥያቄ በአእምሮው ሳይመጣ አይቀርም፡ ወይም በእኔም አእምሮ ይመጣል። ሽበት የወረሰው ጺሙም ኮቱ ላይ ተንጠልጥሏል። በዚያ በኩል፡ ቁልቁል ወደዚያች ከተማ ሲመለከት፡ ዓይኖቹ ጠበብ ብለውና፡ ልቡ እየመታ ይታየኛል።

80 ሆኖም፡ በዚያ ውስጥ፡ በኃጢአት የተጫነ ቢሆንም እንኳ፡ እዚያ መመሥረት ያለባትን፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ተመለከተ። ከንጉሡ ጀምሮ በመንገድ ላይ እስከሚለምነው ለማኝ ድረስ፡ እያንዳንዱን ካህን፡ ሰባኪ፡ ንጉሥ፡ ገዥ፡ ባለሥልጣን፡ ማንኛውም ቢሆን፡ የሚገሥጽ የእግዚአብሔር ተግሣጽ ነበረው፡ በእነርሱም ላይ የሚያሳርፈው የእግዚአብሔር እርግማን ነበረው። ምክንያቱም እነርሱ... ይቀበሉታል ብላችሁ ታስባላችሁ። ኦህ፡ ይረዱት ይሆን?

81 አስታውሱ፡ እርሱ ምንም ዓይነት የድጋፍ ደብዳቤ አልነበረውም። ከዛሬዎቹ ወንጌላውያን የተለየ ሆኖ ነው የመጣው። ከካህናቱ ምንም ዓይነት የድጋፍ ደብዳቤ አልነበረውም። ይህ ሰው ማን እንደሆነ እንኳ አያውቁም ነበር። ነገር ግን እርሱ ማን እንደሆነ የሚያውቅ አንድ አካል ነበረ። እርሱም የላከው ነው። ከወዴት እንደተላከ እስከሚያውቅ ድረስ፡ ለእርሱ የሚቆጠረው፡ ያ ብቻ ነበር። ምንም ቢሆን፡ መልእክቱ እንደዚያው መውጣት ነበረበት።

82 ወደ ከተማዋ ሲገባ ምንም ዓይነት የሐይማኖት ተቋማት መሸኛ አልያዘም ነበር፡ በአገልጋዮች ማኅበር ቀርቦ፡ እንዲህ የሚልበት አልነበረውም፡ "ወንድሞቼ ሆይ፡ እኔ የተላክሁት **እንዲህ** ከሚባለው ወገን ነው፡ እንዲህ ከተባለው የሃይማኖት ወገን ነው። **የዚህ-የዚያ** አባል ነኝ።" ያ አልነበረውም። ከእነዚህ ነገሮች አንዳቸውም አልነበሩትም። ከመጣበት አገር ካለው የአገልጋዮች ማኅበር ጋር በመልካም ኅብረት ላይ እንዳለ የሚያሳይ የኅብረት ካርድም አልነበረውም። እንቅስቃሴን የሚደግፍ ምንም ዓይነት ትብብር አልነበረውም። ስለዚህ ጉዳይ ማንንም እንኳ አላማከረም ነበር።

83 ይህ ትንሽ ሰው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ቆሞ ነበር። ዝም ብሎ ቢያስብ ኖሮ፡ ተመልሶ ወደ እረኝነቱ ለመሄድና፡ ካቆመበት ለመቀጠል፡ በቂ ምክንያት በሆነው ነበር።

84 ነገር ግን፡ እያችሁ፡ ሰውየው በጭራሽ አላመነታም። ስለ ምንም ዓይነት ማስረጃም ሆነ፡ ስለ ኅብረት ካርድ አላሰበም። ያሰበው ስለ አንድ ነገር ብቻ ነበር፡ እርሱም የጌታ ቃል ነው። እግዚአብሔር ወደዚያ ሄዶ ትንቢት እንዲናገር፡ ኃላፊነት ሰጥቶታል። ለእርሱ ትርጉም የሚሰጠው ያ ብቻ ነበር። የጌታ ቃል ስላለው፡ ምንም ዓይነት ማስረጃ፡ የድጋፍ ደብዳቤ፡ ወይም ትብብር እንደማያስፈልገው ተሰማው። ያስፈለገው፡ ብቸኛው ነገር፡ ከእግዚአብሔር ጋር ትብብር ነበረው፡ ያ ደግሞ በቂ ነበር። በጌታ ፈቃድ ውስጥ እስከሆነ ድረስ፡ ምን ለውጥ አለው? መልእክቱ ከእግዚአብሔር መሆኑን እስከሚያውቅ ድረስ፡ እግዚአብሔር ያንን መልእክት ያረጋግጠዋል። ማረጋገጥም ነበረበት።

85 መልእክቱን ባመጣ ጊዜ፡ የሰፍራውን ሁኔታ፡ የሞራል ብልሹነቱን፡ አይተው ስለነበር፡ የዚያ ዘመን ካህናት፡ ሰባኪያንና ነቢያት ሁሉ መጥተው፡ ንሰሐ የሚገቡ ሊመስል ይችል ነበር። በጌታ ቃል ትንቢት መናገር ሲጀምር ግን፡ ለእነርሱ እንግዳ ነገር ሆነባቸው። ስለዚህ ነገር ምንም የሚያውቁት ነገር አልነበረም።

86 ልክ የአሁን ዘመን ተምሳሌት ነው። የጌታ መልእክት፡ እንግዳ ነው! ቤተ ክርስቲያንም ምንም የምታውቀው ነገር የላትም። ሰዎች ተነሰተው በማይታወቅ ልሳን መልእክት ሲሰጡና፡ ትርጓሜ ሲሰጡት፡ እንዲሁም የሆነ ነገር ሊከሰት እንደሆነ ሲናገሩ ሲሰሙ፡ ሰዎች ጭንቅላታቸውን አዙረው ጥለውት ይሄዳሉ፥ ሰዎችም እብድ እንደሆኑ ያስባሉ። አንድ ሰው በመንፈስ ተነስቶ ትንቢት ሲናገር፡ ወይም ከጌታ መልእክት ሲያመጣ ሲያዩ፡ እያችሁ፡ ዛሬ ባለው የቤተ ክርስቲያን ዓለም ውስጥ ያሉ ሰዎች ግለሰቡ እእምሮውን የሳተ ይመስላቸዋል። ለእነርሱ እንግዳ ነው፡ ምክንያቱም ዛሬ፡ ያሉበት ሁኔታቸው፡ በዚያን ዘመን ሰማርያ ከነበረችበት ሁኔታ ጋር አንድ ዓይነት ነውና።

87 ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ አገሮች ወይም የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ፡ ወደዚህ ሁኔታ ውስጥ ሲገቡ፡ እግዚአብሔር የጌታን ቃል የያዘ ነቢይ ሊያስነሳላቸው ይችላል። እርግጥ ነው።

88 ከረጅም ጊዜ በፊት፡ ዘንግተውታል። ነገር ግን በመጽሐፎቻቸው ውስጥ ተመልክተው፡ ከትምህርት ቤቶቻቸው የወጣ፡ ዶክተር አሞጽ የተባለ ሰው፡ መኖሩን ማረጋገጥ ቢችሉም፡ ባይችሉም። ነገር ግን፡ ይህንን፡ "የአብርሃም አምላክ ከነዚህ ድንጋዮች ለራሱ የሚሆኑ ልጆችን፡ ወይም ነቢያትን፡ ቃሉን የሚያመጡትን፡ ሊያስነሳ እንደሚችል" ማወቅ ነበረባቸው።

89 ያው አምላክ ያኔ እንደነበረው ዛሬ ምሽትም ይችላል። በእርግጥም፡ ለሰዎቹ፡ መረዳት ያልቻሉት ነገር ነበር። እርሱ ቃሉን እንዲያመጡ ሰዎችን፡ ሊያስነሳና፡ ሊቀባ ይችላል። ቃሉን በአንድ ሰው ውስጥ አኑሮ፡ ሊልከው፡ ራሱንም በሚያዋርድና ራሱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ በሚሰጥ፡ እግዚአብሔርንም በቃሉ ለመውሰድ በማይፈራ ሰው፡ እርሱ አምላክ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይችላል። ይህን ለማድረግ ይችላል፡ ያደርገዋልም። እንደሚያደርግም ቃል ገብቷል።

90 በዚያን ዘመንም ቃላቱ፡ በእርግጥም፡ በማረጋገጫ የታጀቡ ነበሩ። ምክንያቱም፡ ያው ትውልድ በሕይወት ሳለ፡ አሞጽ የተናገረው ትንቢት ሁሉ ተፈጽሟልና።

91 አሁን፡ ዛሬ አሞጽ ወደ እኛ ቢመጣ፡ እንቀበለው ይሆንን፡ ብዬ እሰባለሁ? ፊኒክስ አሞጽን ትቀበለው ይሆን? እዚህ ከተራራው ማዶ፡ ከሆነ ቦታ፡ ወይም ከአገሪቱ የሆነ ክፍል፡ እንዲህ ያለ ምስኪን፡ የተጎሳቆለ-ልብስ የለበሰ ሰው፡ መጥቶ እዚህ ቢገባና አገልጋዮቹን ሰባኪዎቹን ሥርዓት እንዲይዙ ቢገሥጽ፡ "የጌታ ቃል አለኝ፡" ቢል፡ የምንቀበለው ይመስላችኋልን? በፍጹም አንቀበለውም።

መጀመሪያ የምንጠይቀው፡ "ከየትኛው ወገን ቡድን ነህ" የሚል ነው?

92 እርሱም ዞር ብሎ፡ "ከሰማያዊው ወገን ነኝ፡" ቢልስ? ያ ለእኛ እንግዳ ነገር ይሆንብናል ብዬ፡ እሰጋለሁ።

93 ነገር ግን በዚያን ጊዜም የነበረው ሁኔታ እንደዚሁ ነበር። ዛሬም አሞጽ ቢገለጥ ምናልባት ሁኔታው ያው ሊሆን ይችላል።

94 እስቲ፡ ለተናገርኩት ነገር ሲባል፡ ለጥቂት ደቂቃዎች፡ ወደዚህ እናምጣውና፡ ምን ያደርጋል ብለን እንደምናስብ እንመልከት። ምን እንደሚያደርግ ታውቃላችሁ? አጠቃላይ ከአደረጃጀታችን ሥርዓት ጋር እንደማይስማማ አምናለሁ። አዎ፡ ወዳጄ። ከሃይማኖት ተቋማችን ትምህርት ጋር አይስማማም። ሜቶዲስቶችን፡ ባፕቲስቶችን፡ ፕሬስቢቴሪያኖችን፡ ሉተራኖችን፣ ካቶሊኮችንና፡ ጴንጤቆስጤዎችን ይኮንናችኋል። ሁሉንም በአንድ ላይ ይጨምራቸዋል። በእርግጥም ያደርገዋል። ከሐይማኖት ተቋም ትምህርቶቻቸው ጋር አይስማማም። ቀጥታ ወደ ቃሉ መሠረት ይሄዳል፡ በቃሉም ላይ ይጀምራል። እንቅስቃሴው **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** በሚለው ላይ ይጀምራል።

95 ታዲያ፡ ታዲያ፡ ፊኒክስ የምትቀበለው ይመስላችኋል? ሉዊስቪል፡ ኒው ዮርክ፡ ቦስተን፡ ማሳቹሴትስ፡ ወይም ካሊፎርኒያ፥ ወይም የትም ቢሆን የሚቀበሉት ይመስላችኋል? አይ፡ ወዳጄ። በቻሉት ፍጥነት ያንን ትንሽ ሰው እስር ቤት ያስገቡት ነበር። በእርግጠኛነት። በእርግጠኛነት ያደርጉታል። ወደ ቃሉ ከተመለሰ፡ እንዲህ እንደሚያደርጉት እርግጠኛ ነኝ፡ ምክንያቱም ሁሉም ቡድኖች ከእርሱ ጋር አይስማሙም። ማንም ከእርሱ ጋር የሚስማማ አይኖርም፡ ምክንያቱም ከቃሉ ጋር ላለመስማማት የራሳቸውን ወጎች መያዝ አለባቸውና።

96 እርሱ እውነተኛ ነቢይ እንደሆነ ማስታወስ ይኖርብናል። እርሱ ከእግዚአብሔር የተላከ ነቢይ፡ ቢሆን ኖሮ፡ ነቢይ መሆኑን የምናውቅበት፡ አንዱና ግልጽ የሆነ ምልክት ይኖረዋል፥ እርሱም ከቃሉ ጋር መጽናቱ ነው። ምክንያቱም፡ የእግዚአብሔር ቃል የሚመጣው፡ ወደ ነቢያት ነውና።

97 ምን እንደሚያደርግ ታውቃላችሁ? ይህንን ትውልድ ያወግዛል ይገሥጻልም። በአገሪቱ ያለችውን ፀጉሯን-የተቆረጠች ሴት ሁሉ ይኮንናል። እያንዳንዱን የሐይማኖት ተቋም ሰባኪ ይኮንናል። በእርግጥም ያደርገዋል። እያንዳንዱን ሲጋራ አጫሽ፡ ቁምጣ ወይም ሱሪ የምትለብሰን ሴት ሁሉ ይገሥጻል። ይገነጣጥላቸዋል። ለምን? ከቃሉ ጋር የሚቃረን ነውና። በትክክል!

98 የምንቀበለው ይመስላችኋል? በፍጹም። አይቀበሉትም።

99 በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ሥነ ምግባር ብልሹነት ይኮንናል። ያቺን የተሸበሸበች ትንሽ ጣቱን በነዚያ ሰባኪዎች ፊት እያወዛወዘ እንዲህ ይላቸዋል፡ "በመድረክ ላይ ቆመህ ሴቶቻችሁ በወንዶች መካከል በፍትወት በሚቀሰቅስ ሁኔታ እንዲለብሱና፡ እንዲህ ያሉ ነገሮች እንዲሆኑ እየፈቀድክ፡ ራስህን የተቀባ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነኝ ትለኛለህን? ወጣት ሴቶች እንዲህ እንዲሆኑ ትፈቅዳለህን? ወንዶች ሁለትና ሦስት ጊዜ እንዲያገቡና፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዲያቆናት እንዲሆኑ ትፈቅዳለህ? ምን ለማለት እየሞከርክ ነው በእጅህ የያዝከውን ያንን የሹመት ማስረጃ ይዘህ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ወደ ጎን ትላለህን?" ኦህ፡ ማይ! ሁሉንም ነገር ያወግዘዋል። አዎን፡ ወዳጄ። የቤተ ክርስቲያን ስነ ምግባር ብልሹነት፡ የአባላቱንም ስነ ምግባር ብልሹነት፡ ያወግዘዋል። አቤት! እያንዳንዱን አባል፡ ያፈርሳል። እያንዳንዱን በሰው-የተሠራ የሴሚናሪ ትምህርት ዶክትሪን፡ ይገነጣጥለዋል።

100 አሁን፡ እንዲህ ያለውን ሰው ልትቀበሉት ትችላላችሁን? በጭራሽ። አያደርጉትም። በእርግጠኝነት አያደርጉትም። በቻሉት ፍጥነት ያንን ሰው ከከተማ ያስወጡታል። እንዲያውም፡ ማኅበሩ ተሰብስቦ፡ እንዲህ ይሉ ነበር፡ "ስሙ፡ ስለዚህ ነገር የሆነ ነገር ማድረግ አለብን። ያንን ለመስማት ወደዚያ እንዳይሄዱ ለጉባኤህ ንገር።" በጭራሽ። በጭራሽ። በምንም ዓይነት መንገድ፡ አንቀበለውም፡ በፍጹም አንቀበለውም። በእርግጠኝነት። ሊያደርጉት አይችሉም።

101 እንዴት ሲያወግዝ ሰሙት። ኦህ፡ እዚህ ያለውን ነገር እወደዋለሁ። የተናገረውን እያነበብኩ ነው። እንዲህ አለ፡ "ያ እናገለግላለን የምትሉት እግዚአብሔር ራሱ ያጠፋችኋል።"

102 ዛሬም ቢሆን ያንኑ ይናገር ነበር። እኛ አሜሪካውያን በብዙ አስደናቂ ነገሮች እራሳችንን አስከብበናል፡ በትላልቅ ሕንፃዎችና፡ በድርጅቶቻችን ውስጥ ባለ ታላቅ ቁጥር፡ በዚህ ሁሉ ታዋቂነትና፡ ከቤተ ክርስቲያን እንዳይባረሩ በመፍራት፡ ዝም እንዲሉ በሰለጠኑ የሴሚናሪ አገልጋዮች ሁሉ ተይዘናል። እርግጥ ነው። ያንን ነገር ያፈራርሰዋል፡ ምክንያቱም ከቃሉ ጋር ይቃረናልና። በእርግጥም ያደርገዋል። እናገለግለዋለን የ—የምንለው ያው አምላክ ከነዚህ ቀናት በአንዱ፡ ይህን ነገር ያቃጥለዋል። ያፈራርሰዋል።

103 አሞጽ ዛሬ እዚህ ቢገኝ ኖሮ፡ ቃላቱን አይለውጥም ነበር። ወደ ቃሉ ተመለሱ! አቤት! ምን? እንዲህ ሲላቸው ሰሙት፡ "እግዚአብሔር ወደዳችሁ። አመጣችሁ። የተመረጠ ሕዝብም አደረጋችሁ።"

104 አንድ ቀን በጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲናገር ብሰማው ደስ ባለኝ ነበር። አሞጽ እንደሆነ ብታምኑት፡ ምናልባት ለተወሰነ ጊዜ፡ ከጀርባዬ ትወርዱልኛ ይሆናል። አያችሁ? አዎን፡ ይነግራቸው ነበር። ምንም ባላቅማማ ነበር። በሚችለው ኃይል ሁሉ አጥብቆ ይናገራል፡ ከቃሉ የት ጋር እንደጎደሉ ይነግራቸዋል።

105 ከዓመታት በፊት ከእነዚህ ቤት-ሰራሽ፡ ሰው-ሰራሽ የሬሳ ማቆያዎች፡ ያወጣችሁ እግዚአብሔር! ከአምሳ ዓመት በፊት፡ አባቶቻችሁና እናቶቻችሁ ዓለምን በውስጣቸው ካጠመዱና ከያዙ እነዚህ ሥርዓቶች ወጡ።

እግዚአብሔርም ምሕረቱን ልኮ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከነበረው፡ ኃጢአትና ነ—ነገሮች ጠርቶ አወጣችሁ። አሁን ግን ሰማርያ እንዳደረገችው፡ ተመልሳችሁ ዞራችኋል። ይህም፡ እግዚአብሔር ከእነዚያ አገሮች አወጣቸው፡ እነርሱ ግን ተመልሰው ከእዚያው አገር ጋር ሳብረት ፈጠሩ፡ እኛም ዛሬ እንደዚያው ነን፡ ከነዚያ ትልልቅ የሐይማኖት ተቋም አብያተ ክርስቲያናት ጋር ለመወዳደር እየሞከርን ነው። ትልልቅ ትምህርት ቤቶችን እየገነባን ነው። ምን? ትልልቅ ትምህርት ቤቶች አያስፈልጉንም። ይሁን፥ በዚህ ላይ ተቃውሞ የለኝም።

106 ነገር ግን በዘመኑ የሚሠራን መሰራች ወይም መሪ በወሰዳችሁ ቁጥር፡ እንግዲህ፡ በዘመኑ መልካም ያደርጋል፡ ነገር ግን፡ እሱ እንደሄደ፡ ወዲያውኑ እሱ በሰራው ሥራ ላይ ድርጅት ይገነባሉ። ከዚያም በዚያ ውስጥ ትንንሽ ቅምጥሎችና፡ ኤልቪሶችን ያስገባሉ፡ ከዚያም፡ የመጀመሪያው ነገር፡ ሳታውቁትም ነገሩን ለራሳቸው እንዲመች አድርገው ያጣምሙታል። ከዚያም **ሌላኛው** ይመጣና እርሱ ደግሞ የሆነ ከሀርቫርድ፡ ወይም ከመሰል ቦታዎች የወጣ ታላቅ ምሁር ሰለሆነ፡ ሌላ ነገር ይከትብበታል። በመጀመሪያም፡ **ይህን** መጨመር፡ **ያንን** ማውጣት ይጀምራሉ፡ **ይህ** ማለት **እንዲህና እንዲያ** ማለት አይደለም ይላሉ። አሁንም ተመልሳችሁ በዚያው ባረጀ አዙሪት መንገድ ውስጥ ትገባላችሁ። አዎ።

107 አሞጽ እዚህ ቢሆን ኖሮ፡ ነገሩን ሁሉ መሬት እስኪነካ ድረስ ያፈራርሰው ነበር። አገልግሎቱን የገነባው ሰንት አብያተ ክርስቲያናት አብረውት እንደሚሠሩ በማየት አልነበረም። ቤተ ክርስቲያኑን በሆነ ድርጅት ወይም በሆነ የቤተ ክርስቲያን ክፍልፋይ ላይ ፈጽሞ አይገነባም ነበር። የሚያደርገው ነገር ቢኖር፡ አገልግሎቱን **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** በሚለው ላይ መገንባት ነበር። እግዚአብሔርም እንደተለመደው ከእርሱ ጋር በመሆን፡ ትክክል መሆኑን ያረጋግጥለት ነበር። እርሱም፡ "ችግር አለ፡ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ውጥንቅጥ አለ" ይል ነበር።

108 ዛሬስ ምን ይል ይሆን? ያ የእግዚአብሔር ቃል በፊታችን ተንጠልጥሎ እያለ ምን ይል ይሆን? በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3 ላይ፡ እንዲህ ይላል፡ "ችኩሎች፡ በትዕቢት የተነፉ፡ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ፥ እርቅን የማይሰሙ፡ በሐሰት የሚከሱ፡ ራሳቸውን የማይገዙ፡ መልካም የሆነውን የሚጠሉ፥ የአምልኮ መልክ አላቸው፡ ኃይሉን ግን ክደዋል" ይላል። አንድ ነቢይ ተነሰቶ ይህንን ትንቢት ሳይናገር ያልፈዋል ብላችሁ ታሰባላችሁ?

109 እርሱም፡ "ይህ ዛሬ በዓይናችሁ ተፈጽሟል" ይል ነበር፡ ቤተ ክርስቲያን እንዴት መደበኛ እንደሆነች፡ እንዴት ነገሮችን እንደሚያደርጉ ይናገር ነበር። እ—እነዚያን የእግዚአብሔር ቃላት ያሳሰባችሁ ነበር። አሞጽ በቦታው ቢነሳ ኖሮ፡ እግዚአብሔር በዚህ ዘመን አደርገዋለሁ ያለውን ነገር ያሳሰባችሁ ነበር። ያ ብቻ ሳይሆን፡ እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ለማድረግ ቃል የገባውን፡ በአሞጽ፡ ያረጋግጥ ነበር። በእርግጠኝነት። ያደርጋል። በዚያን ዘመን አድርጎታልና። ሁልጊዜም ያደርገዋል። በእርግጠኝነት።

በሁኔታው ላይ አሞጽ ቢነሳ እንቀበለውም ነበር።

110 አሁን፡ እንዴት፡ “የአምልኮ መልክ ያላቸው፡” እ—እዚያ በመዘምራን ውስጥ ቆመው፡ ከ—ከዚያም፡ በረጅም-ቀሚስ አሸብርቀው፡ እ—እንደ መላእክት ይዘምራሉ፥ ይጨፍራሉም፡ በማግስቱ ምሽትም፡ እንደ አጋንንት ይሆናሉ። በትክክል። አያችሁ? እውነቱ በትክክል ይህ ነው። አንዳንዶች ታላቅ፡ ረጅም ቀሚስ ለብሰው፡ እንደ አበባ-አሸብርቀው፡ እንደ መልአካዊ ፍጡር ይታያሉ፥ እዚያው ቆመው ግን እንደ ማንኛውም ክፉ መንፈስ፡ ቃሉን ይክዳሉ። “የአምልኮ መልክ አላቸው፡ ኃይሉን ግን ክደዋል።” ሄዳችሁ፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ብትናገሩ፡ እርሱ፡ ከ—ከቤተ ክርስቲያን ያባርራችኋል። አያችሁ? ለምን? የግድ ማድረግ አለበት። ነገር ግን በእነዚህ ቤተክርስቲያናት ውስጥ ቆመው፡ አባሎቻቸውም በምድር ቤት፡ ትዊስትና ሮክ-ኤንድ-ሮል እንዲጨፍሩ ይፈቅዳሉ።

111 የኛዎቹ Y.M.C.A. ተብዬዎች፡ C ምንን እንደሚወክል እንጃ። ወደ እነርሱ ዘንድ ስትገቡ፡ ከጌታ ስም ውጭ ሌላ ነገር አትሰሙም-... ያ የወጣቶች የስድብ ማኅበር ነውን?

112 በቅርቡ፡ በአንድ ሆቴል ውስጥ፡ አርፌ ነበር፡ Y.W.C.A አካባቢ ነበር። እስከ ከምሽቱ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ እነዚያ ትንንሽ ልጃገረዶች እዚያ ወለል ላይ፡ ትዊስት ጭፈራ እየጨፈሩ፡ እግራቸውን ለመሰበር ሲሞክሩ ማየት፡ ውርደት ነበር። በትክክል። ሁሉም ደግሞ የቤተ ክርስቲያን አባላት ናቸው፡ በመዘምራን ውስጥ ይዘምራሉ፡ ሰንበት ትምህርትም ይማራሉ። እዚያ ወለል ላይ እነዚያን ትንንሽ ልጆች፡ ሃይማኖት በተባለ ሥርዓት የሚያስተምራቸው፡ ዲያብሎስ እንጂ፡ ሌላ አይደለም። እርግጥ ነው። እውነተኛ ነቢይ ያንን ነገር ወደመጣበት ወደ ገሃነም ጢስ መልሶ ያወግዘው ነበር። በእርግጠኛነት እውነት ነው።

113 አሞጽ እዚህ መድረክ ላይ ቆሞ ወንጌልን ሲሰብክ፡ ፀጉራቸውን-የተቆረጡ ሴቶችን አይቶ ሳይገሥጽ ያልፋል ብላችሁ ታስባላችሁ? ኢሳይያስ 5ንና፡ 1ኛ ቆሮንቶስ 14ን አይጠቅስም ብላችሁ ታስባላችሁ? እናስ፡ ኦህ፡ ታዲያ—ታዲያስ እንዳለ አይዘረግፍባቸውምን? በእርግጠኛነት። ያደርገዋል። በጎዳናዎች ሲመላለስ እንደ ወንድ የሚመስሉ፡ ትንንሽ ልብሶችን የለበሱ፡ ቆዳቸው ወደ ውጭ የወጣ እስኪመስል ድረስ፡ በጣም የጠበቀ ልብስ የለበሱ ሴቶችን ሲያይ፥ እየተወዛወዙ፡ ሲውረገረጉ፡ ሲቀማጠሉ፡ በትዕቢት እየተራመዱ፡ ሲሄዱ አይቶ፡ የእግዚአብሔር ሰው በመድረክ ላይ ቆሞ ያንን እያወግዘውም ብላችሁ ታስባላችሁን? እንዲህ ያለው ነገር፡ በመድረክ ላይ መነገሩ፡ በጣም ብርቅ በሆነበት በዚህ ዘመን። ይህም በጴንጤቆስጤ ቤተክርስቲያናትም ውስጥ፡ ጭምር ነው። ይህ በትክክል እውነት ነው። ለአሞጽ ግን ምንም ለውጥ አያመጣም። ኡህ-ሃህ። አንዳንድ... የሚናገር ሰው ይሆን ነበር። አይፈራም ነበር፡ ምክንያቱም በጌታ የተቀባ ነበረና። **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** የሚል ቃል ካለው፡ ያ የእግዚአብሔር ቃል መሆን ነበረበት።

114 ወደ ሰማርያ የመጣው፡ ድምቀታቸውን ለማየት፡ ሰንት ድርጅቶችና ምን ያህል ቁጥር እንዳላቸው፡ ለመቁጠር አልነበረም።

115 በቀደም ምሽት እንደተናገርኩት፡ ዛሬ እንደሚመስለው መላው ቤተክርስቲያን የተገነባችው፡ ዛሬ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለው

ዋናው ነገር "ብዛት፡ ብዛት፡" እንዲ ከሌላው ለመብለጥ የሚሞክር መሆኑ ነው። "ብዛት!" እግዚአብሔር ብዛት አይፈልግም። እርሱ የሚፈልገው ባህርይ ነው። እግዚአብሔር የሚፈልገው ባህርይን ነው፡ እጁን ሊጭንበት የሚችለውን ሰው፡ ለረጅም ጊዜ ፀጥ ብሎ የሚቆምለትን ሰው ይፈልጋል።

116 እንዳልነውም፡ "ውሳኔዎች! ዓመቱን ሙሉ፡ **በጣም-ብዙ** ውሳኔዎች ነበሩን።" እነዚያም **ድንጋዮች** ናቸው፡ "ነሰሃዎች" ናቸው። ስለታም የእግዚአብሔር ቃል የያዘው ድንጋይ ጠራቢ ሳይኖር፡ ግለሰቡን ጠርቦ የእግዚአብሔር ወንድ፡ ወይም ሴት ልጅ አድርጎ፡ ወደሚገባበት የቤተ ክርስቲያን ሰፍራ ካላሰገባቸው ድንጋዮቹ ምን ይጠቅማሉ? ድንጋዮችን ማንከባለል ብቻ ሕንፃ አይሆንም። እነርሱን መጥረብና ቅርጽ ማስያዝ አለብህ።

117 ዛሬ የምንፈልገው፡ እንደ አሞጽ ያሉ፡ የተቀቡ፡ ዓለምን ከሴቲቱ ከርክመው በማስወገድ የእግዚአብሔር ሴት ልጅ የሚያደርጉ፡ ዓለማዊነትን ከወንዱ ቆርጠው የሚያወጡ ሰዎች ያስፈልጉናል። ሰንት የባለአደራ ቦርድ አባላት ቢያባርሩትም ሆነ፡ ምንም ቢሆን፡ እርሱ ግን **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** በሚለው ላይ ይቆማል። አዎን።

118 እንደዚህ ከሆነ ግን፡ አሞጽን የምንቀበለው፡ አይመስለኝም። አሞጽ በመንፈስ ቅዱስ እመራለሁ ወደምትል የዛሬዋ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ቢገባና፡ በመንፈስ ቅዱስ እመራለሁ በምትለው፡ በዚያችው ጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያንኑ ነገር ቢያይ ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል? ይገርመኛል። አሁን፡ ስለ ባፕቲስት፡ ስለ ሜቶዲስትና፡ ስለ ሉተራን ማውራት እንችላለን፡ ነገር ግን፡ ወደ እኛው ወደ ረከሰው ደጃፍ ሲመጣስ፡ ምን ይባላል? ከእግዚአብሔር ቃል ርቀናል! የሆነ ቦታ፡ የሆነ ነገር ተበላሽቷል። ይህ በትክክል እውነት ነው። አዎን። ይመጡና እነዚህን ሁሉ ልዩ ልዩ ነገሮችን ያደርጋሉ፡ በመንፈስ እንደተመሩም ይናገራሉ፡ በመንፈስ ይጨፍራሉ፡ አንዳንዴም በልሳን ይናገራሉ።

119 በልሳን በመናገር አምናለሁ። በመንፈስ በመጨፈር አምናለሁ። በደስታ በመጮህ አምናለሁ። ነገር ግን ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄድ ሌላ ብዙ ነገር አለ። በትክክል። እነዚህን ሁሉ እያደረግህ፡ ቃሉን እየካድህ፡ የሆነ ቦታ የሆነ ችግር ካለህ፡ የተሳሳተ መንፈስ ይዞሃል። ኡህ-ሃህ። ለማንኛውም፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች አይመራም። አይ። አይመራም።

120 አሁን እንደገና የመውጫ-ጊዜ፡ እንደሚነገረው፡ እንደ ቦስተን ቲ ፓርቲ ዓይነት ጊዜ ይመስለኛል። ቤተ ክርስቲያን አንድ እንዲህ ያለ ነገር ያስፈልጋታል። እውነተኛና ጥሩ ማጽዳት ያስፈልጋታል።

121 ጆን ኦፍ አርክ፡ በድሮ ጊዜ፡ በሕይወት ሳለች፡ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት መሆኗን ሳታውቅ ቀረች፡ ምክንያቱም ራእዮችን ታይ፡ ሕልሞችን ትተረጉም ነበር፡ በመንፈስም-የተሞላች ሴት ነበረች። እግዚአብሔርም ያችን ምስኪን እመቤት ተጠቀመባት። እነርሱ ግን ጠንቋይ መሰላ ታየቻቸው። እንደ ጠንቋይም፡ በእንጨት ላይ አቃጠሏት። ያንን ታውቃላችሁ። የካቶሊክ ቄሶች ይህን ያደረጉት ራሳቸው ናቸው። በመቶዎች የሚቆጠሩ ዓመታት ካለፉ በኋላ፡ ቅድስት እንደነበረች አወቁ። ከዚያም፡ ቅድስት ብለው ለመሰየም በፈለጉ ጊዜ፡

የፍትሐት ሥራ መሥራት ወደዱ። ስለዚህ የነዚያን ቄሶች አስከሬን ቆፍረው በማውጣት ለካሳ መታሰቢያ እንዲሆን፡ ወደ ወንዝ ወረወሯቸው። አያችሁ፡ ነገሩ በፊታቸው ሲያልፍ ማየት ተሳናቸው። በቅዱስ ፓትሪክና በሌሎችም ላይ ያደረጉት እንደዚሁ ዓይነት ነገር ነበር።

122 ኢየሱስ እንዲህ ማለቱ ምንም አያስደንቅም፡ "የነቢያትን መቃብር ትገነባላችሁ በኖራም ታስጌጣላችሁ፡ ነገር ግን በዚያ መቃብር ያኖራችኋቸው እናንተ ራሳችሁ ናችሁ።" በትክክል። ዛሬ የሚያስፈልገን የጌታን ቃል ወደ እኛ የሚመልስ እንደ አሞጽ ያለ ሰው ነው። በእርግጥም ያስፈልገናል።

123 አሁን፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ለመደገፍ እዚያ ካልሆነ በስተቀር የምናቀርበው ሙግትና የምንለው ነገር ምንም ትርጉም የለውም። አኗኗራችን ከምንናገረው ነገር ጋር የማይጣጣም ከሆነ፡ የሆነ የተበላሸ ነገር አለ ማለት ነው።

124 ጆን ኦፍ አርክ ፈረንሳይን ወደ አብዮት መራች። አብዮተኛ ያስፈልጋቸው ነበር። በትክክልም ያደረጉት ያንን ነው። አብዮተኛ ያስፈልጋቸው ነበር፡ እርሷም መራችው። ነገር ግን ከአብዮቱ በኋላ፡ የተፈጠረው ስህተት፡ ያመጹበትን ነገር ለ—ለማስተካከል ሌላ-ተቃራኒ አብዮተኛ አስፈለጋቸው።

125 ዛሬ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የተቀራረበችው ቤተ ክርስቲያን የጴንጤቆስጤ ቤተክርስቲያን መሆኗን እውቃለሁ። እንዲህ ባይሆን ኖሮ፡ ሌላ ቦታ እሆን ነበር። በትክክል። ተሰፋ አለ ብዬ ባላሰብ ኖሮ፡ እዚህ ቆሜ ለጴንጤቆስጤ ሕዝብ እየተናገርኩ፡ ጊዜ ባላቃጠልኩ ነበር። በትክክል። ጴንጤቆስጤ ትክክል ነው። ነገር ግን ጴንጤቆስጤዎች ተሰብስበው ወኅቻችን እንዲሰባበሩ በሚያስፈልግበት ጊዜ፡ ሌላ-አብዮት እንፈልጋለን። ሌላ-ተሃድሶ ያስፈልገናል፥ እኔ... የምፈልገው የጴንጤቆስጤ ነኝ የሚል የይገባኛል ጥያቄን ሳይሆን፡ የጴንጤቆስጤ የሆነ ንጹሕ መታደስን ነው።

126 እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። በእርሱ የሚኖሩ ቅዱሳን ሆነው መኖር አለባቸው። እርሱ ቅዱስ አምላክ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፡ "ያለ ቅድስና፡ ጌታን ሊያይ የሚችል የለም" ይላል። ይህ እውነት ነው። ሕይወቱ ቅዱስ ነው። ሕይወቱ በውስጣችሁ ካለ፡ ቅዱስ ያደርጋችኋል። ያለ እርሱ፡ ጌታን አታዩም። ቤተ ክርስቲያንም ወዴት እየተንሸራተተች እንደሆነ ተመልከቱ።

127 እኛም በዚያን ዘመን፡ እስራኤል እንደነበረችው ዓይነት ነን። እስራኤልም እንደዚያ ነበረች፡ ምክንያቱም እየበለጸገች ስለነበረ፡ ሁሉ ነገር መልካም እየሄደ መሰሏት ነበር። በዘመናቸውም፡ ከሌሎች ከተሞች ጋር፡ ስምምነት ነበራቸው። ስምምነት ነበራቸው። መንግሥት ከአገልጋዮች፡ ከካህናትና፡ ከነቢያት ጋር ኅብረት ቃል ኪዳን ነበረው። እነርሱም ይህ ትክክል መሰላቸው። ይህም ትክክልና ጌታን ደስ የሚያሰኝ መሰሏቸው ነበር። ነገር ግን ተነስቶ ወደ መስመር የመለሳቸው አንድ ምስኪን ሰው ነበራቸው። በትክክል።

128 ስለበለጸጉ ብቻ፡ ስህተት የምንሠራው እዚህ ጋር ነው። ብልጽግና የመንፈሳዊ በረከት ምልክት አይደለም። በትክክል። ቅንጣት ታህል እንኳ አይደለም። እንዲያውም፡ ብልጽግና፡ አንዳንዴ እንቅፋት ነው።

129 ጌታ ስለ እስራኤል የተናገረውን ታስታውሳላችሁ? "ትንሽ በነበርሽ ጊዜ፡ ምንም ባልነበረሽ ጊዜ፡ በደምሽም ውስጥ ተለውሰሽ ባየሁሽ ጊዜ፡ የሚያጸዳሽ

እንኳ በሌለበት ጊዜ፡ እኔ ተቀበልኩሽ። ያኔ አገለገልሽኝ። ነገር ግን ራስሽን- እንደቻልሽና ደኅንነትሽ እንደተጠበቀ እስከሚመስልሽ ድረስ ባደግሽ ጊዜ፡ እኔን ተውሽኝ።" ሁልጊዜም የሚያደርጉት ይህንኑ ነው።

130 ባለፈው ጠዋት በቢዝነስ መንስ ቁርስ ፕሮግራም ላይ እንደተናገርኩት፡ ዖዝያ፡ ታላቅ ሰው ነበር። ጌታን አጥብቆ ይይዝ ነበር። ነገር ግን አንድ ቀን እግዚአብሔር ካጠናከረው በኋላ... ለነቢዩ ኢሳይያስ ታላቅ ምሳሌ ነበረ። ነገር ግን ከጠነከረና፡ ከከበረ በኋላ፡ አሕዛብ ሊፈሩት ጀመሩ። ግንቦቹን ገነባ የሚያምሩት ነገሮቹን ማግኘት ጀመረ። ያኔ በትዕቢት-ተነፋ። ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ማየት ጀመረ። ከዚያም የሰባኪውን ቦታ ለመያዝ ሞከረ። እግዚአብሔርም በለምጽ መታው፡ ለምጻም ሆኖ ሞተ። እያችሁ? በልባችን ከፍ ከፍ ማለትን፡ ፈጽሞ አንፈልግም።

131 አንዳንዴ፡ ድርጅቶቻችን ሲበለጽጉ ስናይ፡ እንዲህ ማለት እንጀምራለን፡ "እኛ ትልቅ ቡድን ነን። እኛ ካሉት የጴንጤቆስጤ ቡድኖች ሁሉ ትልቅ ነን። እኛ ከሌሎቹ የሚበልጥ አለን።" ወይም፡ "የእኛ ቡድን አባል ካልሆንክ በቀር ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት አትችልም፡" ወይም ሌላ ነገር እንላለን። እንዲህ ስትሆኑ ግን፡ ራሳችሁን ከጌታ ቃል ለይታችኋል። በትክክል። አስታውሱ፡ ብርድ ልብሱ ወንድምህን ጭምር ሊሸፍን የሚችል በቂ ሰፋት አለው። ይህ በትክክል እውነት ነው። እርሱንም አካትቱት።

132 ኦህ፡ ዛሬ፡ ወደ ጌታ ቃል የሚደረግ ጥሪ፡ ምንኛ ያስፈልገናል። ዛሬን፡ ተመልከቱ። አገራችንም ወደ ቃሉ የመመለስ ጥሪ ያስፈልጋታል።

133 ከነዚህ ምሽቶች በአንዱ፡ ከቻልኩኝ፡ አንድ ነገር መናገር፡ እፈልጋለሁ... ክስ አዘጋጅቼአለሁ። ሰባኪዎቹን ሁሉ በአንድ ላይ እስካገኝ መጠበቅ ይኖርብኛል። አዎን። ይህንን ትውልድ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም እከሳለሁ፡ ላረጋግጥላችሁም እፈልጋለሁ። እያችሁ? አሁን፡ ይህን ለማድረግ፡ የሆነ ቦታ መሄድ ይኖርብኛ ይሆናል። ነገር ግን፡ የሆነ ቀን ጠዋት ለአገልጋዮች ብቻ የሚሆን፡ የቁርስ ፕሮግራም ሊኖረን ይችል እንደሆነ እንመለከታለን። ጌ—ጌታ ቢረዳኝ፡ ወዴት እየሄድን እንደሆነ፡ የ—የተሳሳተ መንገድ መሆኑን፡ በትክክል ላሳያችሁ እፈልጋለሁ። መመለስ አለብን። ከመመለስ ውጭ ሌላ መንገድ የለም። በትክክል።

134 ዛሬ አገራችንን ተመልከቱ። ምን ለማድረግ እየሞከርን እንዳለንም ተመልከቱ፡ ልክ በጨለማው ዘመን የተከናወነውን ያንኑ ነገር፡ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥትን አንድ ላይ ለማጣመር እየሞከርን ነው።

135 ኅብረቱን፡ ወይም፡ የ—የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤትን ተመልከቱ፡ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ወደዚህ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት እየገቡ ነው፡ ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር አንድነት ኅብረት ነው ብለው ያስባሉ፡ ምክንያቱም፡ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ፡ የዩናይትድ ብረዘረን፡ የመሠረታዊ አብያተ ክርስቲያናት ሰዎች ሁሉ ወደዚህ አንድ ታላቅ ድርጅት እየገቡ ያሉት፡ የእግዚአብሔርን ቃል ካለማወቅ የተነሳ ነው። ነቢዩ እንዲህ ያለ ነገር እንደሚፈጠር ተናግሯል፡ "ለአውሬው ምስል ያደርጋሉ፡ እርሱም የመናገር ሥልጣን ይኖረዋል።"

136 ኦህ፡ አሞጽ ዛሬ ምሽት እዚህ ፊኒክስ ውስጥ ቢሆን ኖሮ፡ በመድረክ ላይ ቆሞ፡ ስለዚህ ነገር ሳይጮህ ያልፋል ብላችሁ ታስባላችሁ? ወንድሞቹን፡ እኛን ስለሚቃወም ሳይሆን፡ ከቃሉ እያራቀን ያለውን ያንን ሥርዓት ስለሚቃወም ነው። እርሱ የሚያደርገው ያንን ነው። “እነዚያ ሰዎች እንዴት አብረው ይሄዳሉ?” መጽሐፍ ቅዱስ፡ እዚህ አሞጽ ላይ፡ እንዲህ ይላል። ጌታም እንዲህ አለ፡ “ለሕዝቡ እንዲህ ብለህ ንገራቸው፡ ‘ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ፡ እንዴት አብረው ይሄዳሉ?’”

137 አሁን፡ በዚያ ካሉት መካከል ግማሹ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት፡ ሰማንያ-አምስት ወይም ዘጠና-አምስት በመቶ የሚሆኑት፡ ከድንግል መወለድን እንኳ በሚክዱበት ሁኔታ፡ እንዴት የጴንጤቆስጤ ቡድኖቻችንን ይዘን፡ ወደ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት እንገባለን? ይክዳሉ። ዘጠና-ዘጠኝ በመቶ የሚሆኑት፡ መለኮታዊ ፈውስን የሚክዱ፡ ይመስለኛል። የመጽሐፍ ቅዱስን መርሆች ይክዳሉ። በልሳን መናገርን ይክዳሉ። ያንን የሚቀበለው የጴንጤቆስጤ ቡድን ብቻ ነው። ታዲያ እንዴት ከእነርሱ ጋር በአንድነት እንጣመራለን? እንዴትስ ከእነርሱ ጋር አንድ እንሆናለን? ሳንስማማስ እንዴት አብረን እንሄዳለን? እንዴት ልታደርጉት ትችላላችሁ? ከእነርሱ ጋር ለመሄድ ያላችሁን ያንን ታላቅ የወንጌላዊነት እምነትና፡ የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረታዊ መርሆችን፡ መካድ ይኖርባችኋል።

138 እላችኋለሁ፡ እግዚአብሔር ግለሰቦችን ነው የሚጠራው። አንተን፡ እንደ ግለሰብ፡ ከቃሉና ከእርሱ ጋር እንድትጸና እየጠራህ ነው።

139 በገዛ ዓለማዊ ጥበባቸው የፈጠሩት፡ የሃይማኖት መግለጫቸው፡ ቃሉን በሚክድበት ሁኔታ፡ እግዚአብሔር እንዴት ከእነርሱ ጋር ይሄዳል? አንድ የሃይማኖት መመሪያ የሰዎችን ቡድን ትምህርት ተቀብሎ፡ አንድላይ፡ የቃሉን እውነት ሲክድ፡ ያኔ እግዚአብሔርን ከእናንተ ታርቃላችሁ። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚለው፡ እግዚአብሔር፡ ቃሉን ለማረጋገጥ፡ ይጠብቀዋል። ቃሉ በሌለበት ሁኔታስ፡ እንዴት ቃሉን ሊያረጋግጥ ይችላል? ከልጆች ይልቅ አባላት ያሉን ለዚህ ነው። የሃይማኖት መግለጫ ያለን፡ ለዚህ ነው። ሁሉም ሰው...

140 ዓለም ታላቅ ሰው እየፈለገች ነው። እየሰሩ ያሉት... ክርስቲያን ነን የሚለውን ሰማቸውን ይዘው እንደፈለጉ እንዲኖሩ የሚፈቅድላቸውን ነገር እየፈለጉ ነው። ሴቶቹ እንደ ሆሊውድ መሆን ይፈልጋሉ ሆኖም መንፈስ ቅዱስ አለን ማለታቸውን መቀጠል ይፈልጋሉ። ሰባኪዎቹ ትልቁን ቤተ ክርስቲያን መገንባትና እነዚህን ሁሉ ነገሮች ማድረግ፡ እንዲሁም ብዙ ጊዜ ያገቡ ዲያቆናት እንዲኖሯቸው ይፈልጋሉ። እ—እነዚህን ትንንሽ ነገሮች ማድረግና **እንዲህ** ያሉ ልብሶችን መልበስ ይችላሉ፡ ይህንንም የሴቶች ነጻነት ይሉታል።

141 አሞጽ ለዚህ ነገር ዝም ብሎ ይቆማል ይታገሳል ብላችሁ ታስባላችሁ? አይ። በእርግጥም አያደርገውም። አሞጽ ዝም ብሎ፡ እዚያ ካሉት የሃይማኖት ባለሥልጣናትና፡ ጳጳሳት ጋር ተገናኝቶ፡ “ወንድሞች ሆይ፡ ታላቅ ነገር አድርጋችኋል ብዬ አስባለሁ” ይላል ብላችሁ ታስባላችሁ?

142 እንዲህ ይላቸዋል፡ “እናንተ ከሃዲዎች! እናንተ አስመሳዮች! እናንተ እምነቱን የካዳችሁ!” ሚክያስ በዚያን ቀን በእነዚያ አራት መቶ ራሳቸውን-ነቢይ

ብለው በሰየሙት፡ የዕብራውያን ነቢያት ፊት የተናገረውን ያንኑ ይናገር ነበር።

143 እነርሱም፡ "በቁጥር ብዛት፡ በብዛት ውስጥ፡ ደኅንነት አለ" አሉ። ይህም ያንን ጥቅስ የት ጋር ለመተግበር እንደምትፈልጉ ይወስነዋል።

144 እኔም እንዲህ ማለት እችላለሁ፡ "ይሁዳ ሄዶ ታነቀ፥ እናንተም ሄዳችሁ ያንኑ አድርጉ።" ነገር ግን ጥቅሱ እዚያ ጋር አይሠራም።

145 እንዲሁም፡ "በመካሪዎች ብዛት ውስጥ ደኅንነት አለ" የሚለው ጥቅስ፡ እዚህ ጋር አይሠራም። እንዲህ ከሆነማ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በሁላችሁም ላይ የበላይነት አላት።

146 በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ደኅንነት አለ። መጽሐፍ ቅዱስ፡ "የጌታ ስም የጸና ግምብ ነው። ጻድቅ ወደ እርሱ ይሮጣል ደኅንነትንም ያገኛል" ይላል። እኔ የማውቀው ብቸኛው የደኅንነት ስፍራ እርሱ ነው። ነቢያት ሁልጊዜ ይህን ያምኑ ነበር። አብርሃም፡ ሲሞት... ኢዮብ ሲሞት፡ መቃብሩን፡ በተስፋይቱ ምድር አደረገ።

147 አብርሃም በሞተ ጊዜ፡ በዚያው ስፍራ በኢዮብ አቅራቢያ፡ አንዲት የመሬት ክፍል ገዛ። ምን አደረገ? ያንን ነቢይ ይከታተለው ነበር። ያ የእግዚአብሔር ሰው እንደነበረ ያውቅ ነበር፡ እርሱም፡ "ቤዛዬ ሕያው እንደሆነ፡ በመጨረሻውም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም አውቃለሁ። ምንም እንኳ ትሎች ይህን አካሌን ቢያጠፉትም፡ በሥጋዬ ግን እግዚአብሔርን አያለሁ" አለ። አዎን። አብርሃምም ይህንን ያውቅ ነበር። ሣራንም በዚያ ቀበራት። አንዲት የመሬት ክፍል ገዝቶ፡ ቀበራት... እርሱ፡ ራሱም፡ በዚያ ተቀበረ።

148 ይስሐቅም፡ በሞተ ጊዜ፡ ተወስዶ በዚያው ተቀበረ። ይስሐቅም ያዕቆብን ወለደ።

149 ያዕቆብም እዚያው ግብፅ ውስጥ ሞተ። ነገር ግን ከመሞቱ በፊት፡ ነቢይ የሆነውን ልጁን፡ ዮሴፍን ጠራው። ነቢይ፡ መንፈሳዊ ሰው፡ ሕልም ተርጓሚና፡ ራእይ የሚያይ እንደሆነ፡ በእያንዳንዱ ጊዜም ፍጹም ትክክል እንደነበረ ያውቅ ነበር። እንዲህም አለው፡ "ልጄ ዮሴፍ፡ ነብዩ ሆይ፡ ወደዚህ ና። ከዓመታት በፊት ሁሉን የሚችል አምላክ በእጄ በነካው በጭኔ ላይ እጅህን አኑር፡ እርሱ ስሜን 'ከአታላይ' ወደ 'ከእግዚአብሔር ጋር መሰፍን' ለወጠው። እጅህን እዚህ ላይ ጭነህ እዚህ ግብፅ ውስጥ እንደማትቀብረኝ በዚያ አምላክ ማልልኝ" አለው። ለምን? ለምን? ምን ለውጥ ያመጣል?

150 ዛሬም የሚሉት ይህንኑ ነው፡ "ምን ለውጥ ያመጣል?" ሰዎችን እንሰበስባለን፡ ከመንገድ አንስተን፡ የቤተ ክርስቲያን አባል እንዲሆኑ እናደርጋቸዋለን። አንዳንዴ ግን በመንገድ ላይ ከነበረው ይልቅ ሁለት እጥፍ የገሃነም ልጅ ታደርጉታላችሁ። በትክክል። ለውጥ ያመጣል።

151 ዮሴፍ፡ በሞተ ጊዜ፡ "አንድ ቀን እግዚአብሔር አምላክ ይጎበኛችኋል፡" በማለት፡ ተናገረ። እርሱ ነቢይ ነበረ። እንዲህ አለ፡ "እግዚአብሔር አምላክ ይጎበኛችኋል። አጥንቶቼንም እዚህ አትተውአቸው፡ ነገር ግን ወደ ተስፋይቱ ምድር ይዛችሁ ውጡ" አለ። ለምን? የትንሣኤው በኩር ከተስፋይቱ ምድር እንደሚወጣ ያውቅ ነበርና። በትክክል።

152 ኢየሱስ፡ በሞተና፡ በትንሣኤ ማለዳ በተነሳ ጊዜ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ “በመቃብር ተኛተው ከነበሩት ቅዱሳን ብዙዎች ተነሱ፡ ከመቃብራቸውም ወጥተው ለብዙዎች ታዩ፡” ይላል። እነማን ነበሩ? አብርሃም፡ ይስሐቅ፡ ያዕቆብ፡ ዮሴፍ ነበሩ። ለምን? በትክክለኛው ሰፍራ ላይ ስለነበሩ ነው።

153 ልዩነት አለው የምለውም ለዚህ ነው። እኔን እዚህ የሆነ ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ወይም ሌላ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አትቅበሩኝ። በኢየሱስ ውስጥ ቅበሩኝ፡ “በክርስቶስ ሆነው ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና።” በእርግጥ ልዩነት አለው። በእርግጥም፡ አለው።

“ቤተ ክርስቲያን ስለተቀላቀልክ፡” የሚሏችሁን አትስሙ።

154 አሞጽ ለዚህ ዝም አይልም ነበር። እንዲህም ይል ነበር፡ “ያ እናገለግላለን የምትሉት አምላክ ራሱ… ”

155 በጌታ ስም ይህንን እናገራለሁ፥ ይህች አገር ትወክለዋለች የተባለው ያው አምላክ ራሱ ይህችን አገር ያጠፋታል። እነዚህንም አብያተ ክርስቲያናት ያጠፋቸዋል። የሰማይ አምላክ ቁጣውን በፍርድ ይልካል እነዚህን ቤተ ክርስቲያናትን፡ ቤተ ክርስቲያናትን ተብለው የሚጠሩትን ያጠፋቸዋል። አስታውሱ፡ ይህን ቃሌን ያዙ።

156 ማንም ሰው ቤተ ክርስቲያንን መቀላቀል አይችልም። የምትቀላቀሉት ሎጅን ነው። ቤተ ክርስቲያንን አትቀላቀሉም፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትወለዳላችሁ። አያችሁ? የሜቶዲስት ሎጅን፡ የባፕቲስት ሎጅን፡ የካቶሊክ ሎጅን፡ የጴንጤቆስጤ ማኅበርን ትቀላቀላላችሁ። እናንተ ግን በሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው የምትወለዱት፥ እርሱም ሊወሰድ የሚመጣው፡ ያቺኑ ቤተ ክርስቲያን ነው። ስለዚህ፡ ያሉን ሎጆች እንጂ፡ አብያተ ክርስቲያናት አይደሉም። በዚያ ሎጅ ውስጥ ግብዞችና፡ ሌላውም ነገር ሁሉ ሊሰበሰብ ይችላል። ነገር ግን እሁኑኑ ይህንን ላሳውቃችሁ፡ በቃሉ መሠረት፡ በሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድም ግብዝ የለም። ከቅዱሳን በቀር በዚያ ሌላ ምንም የለም።

157 አሁን፡ አባልነት ሊቀበላችሁ ይችላል። አ—አሞጽ ደግሞ ያንን አያፈራርሰውም ብላችሁ ታስባላችሁ? ያንን ነገር እስከ መሠረቱ ያናውጠዋል። በእርግጥም ያደርገዋል።

158 ተመልከቱ። እስራኤል በመንገዷ ላይ ሳለች፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ስትሄድ፡ በመንፈስ ቅዱስ እየተመራች፡ የእሳት ዓምድ በፊታቸው ነበረ፡ የተመታውም ዓለት ይከተላቸው ነበር።

159 ከዚያም ወንድም የነበረው፡ ሞአብም ወጣ። አስታውሱ፡ እርሱም፡ የእስራኤል ክፍል ነበረ። ከሎጥና ከልጁ የተወለደ ስለሆነ፡ ከአይሁድ ዘር፡ ወገን ነበረ። ሞአብም ከእነርሱ ወጣ።

160 ካህኑን፡ በለዓምንም ተመልከቱ፡ ወደዚያ ወጥቶ መሠዊያ ሠራ፡ ሊሆን የሚችለውን ያህል መሠረታዊ ሆኖ፡ ልክ እንደ እነርሱ ዓይነት መሥዋዕቶችን አቀረበ። አያችሁ? ታዋቂ ሰዎችንም ከእርሱ ጋር ይዞ ነበር። ንጉሡ አብሮት ነበረ። ታላላቅ ሰዎች፡ መሳፍንትና ጀነደረቦች ሁሉ፡ ከእርሱ ጋር ቆመው ነበር።

161 ነገር ግን ሙሴ ጋር የቆመ እርሱ በለዓም ያላየው አንድ አካል ነበረ። ከአሞጽ ጋር የቆመውም እርሱ ነው። ዛሬ ምሽት፡ እዚህ ላላችሁ ለእግዚአብሔርና ለጽድቅ ለምትቆሙ፡ ለእያንዳንዳችሁ አብሮ የሚቆመው እርሱ ነው። እዚያ ምንም ያህል ገዥዎችና፡ ነገሥታት ቢኖሩም፡ ነገሩ ከእነርሱ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። እግዚአብሔር የባረከውን ፈጽሞ ሊረግሙ አይችሉም። ለምን? እርሱ ሕያው ዘር ነውና። የእግዚአብሔር ቃል ነው። እስከ ፍጹምነቱ ድረስ ያድጋል። ኦህ፡ በሰፈሩ ውስጥ የሕያው እግዚአብሔር ምልክቶች አሉ! ይህም፡ እስራኤል እዚያ ታች ስህተት የሠሩ ይመስል ነበር። ነገር ግን ያንን የተመታውን ዓለትና፡ ለእስራኤል የተደረገውን ያንን ሰርየት ማየት ተሳናቸው። በሰፈሩም ውስጥ የንጉሥ እልልታ ነበረ። እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ነበረ። ለምን? እርሱ የታመሙትን ይፈውስ፡ ታላላቅ ተአምራትን፡ ምልክቶችንና ድንቆችን ያደርግ ነበር፡ የእሳት ዓምድም በላያቸው ላይ ቆሞ ነበር። ሙሴ የእሳቱን ዓምድ ይከተል ነበር። የእስራኤልም ልጆች ሙሴን ይከተሉ ነበር። ወደ ተስፋይቱ ምድርም በመጓዝ ላይ ነበሩ፡ ሊያስቆማቸው የሚችል ምንም ነገር የለም። አሜን።

162 ኦህ፡ እግዚአብሔር በእጁ ሊጠቀምበት፡ ሊቆጣጠረው የሚችል ሰው ቢያገኝ ኖሮ፡ ዛሬም እንዲህ ያለው ነገር በቀላሉ ሊደገም አይችልምን? ያ የእሳት ዓምድ አሁንም ሕያው ነው። እርሱ አሁንም ትናንት፡ ዛሬ፡ ለዘላለምም ያው ነው። ቃሉ አሁንም ሕያው ነው።

163 እግዚአብሔር ሆይ፡ ለእውነትና ለጽድቅ የሚቆም፡ እነዚህን ነገሮች የሚያናውጥ... አሞጽን ላክልን።

164 "እንግዲህ... ምን ዓይነት ውጤት ይኖረዋል ብለህ ታስባለህ፡" ትሉ ይሆናል?

165 እንግዲህ፡ እግዚአብሔር አስቀድሞ እንዲጠሩ የወሰናቸውን ሁሉ እስኪጠራ ድረስ፡ ውጤት ይኖረዋል። የሚያገኘውም እነርሱን ነው። "አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣሉ።" አዎ።

166 ሚክያስ በአክዓብ ፊት ቀርቦ ነበር፡ አክዓብም ይጠላው ነበር። የአገልጋዮች ቡድን ሁሉ ይቃረኑት ነበሩ። እነርሱም፡ በመንፈስ ተነሳስተው ነበር፡ ነገር ግን የእነርሱ መነሳሳት ከቃሉ ጋር አልተስማማም። ምናልባት፡ አሞጽም ያንኑ ነገር ሳይገጥመው አልቀረም፡ ብዬ አስባለሁ።

167 ካህናቱ ወደ መንገድ ወጥተው፡ "ቆይ እስቲ! ም—ምን... ? መሸኛህን አሳየኝ። ከየትኛው ትምህርት ቤት ነው የመጣኸው? ዘርህስ ትውልድህስ ከማን ነው? አንተ... ? ማን ነው አንተን ካህን ያደረገህ" ይሉታል?

እርሱም፡ "እግዚአብሔር ነው ያደረገኝ" ይላቸዋል።

"ከየትኛው ወገን ነህ? "

168 "ከይሖዋ እግዚአብሔር። **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** አለኝ" ይላቸዋል። ታዲያ ይሰሙታልን? በእርግጥ አይሰሙትም። ያንን ሰው መስማት አልፈለጉም ነበር። በእርግጠኝነት አልፈለጉም። አልፈለጉም...

169 ሆኖም፡ ግን፡ እነዚያ ሰዎች፡ "በመንፈስ ተነሳስቻለሁ። እንግዲህ፡ እኔ እዚህ የታላቁ የፈሪሳውያን ቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ። እግዚአብሔር እንዴት

እንደባረከን ተመልከቱ። የወርቅ መሠዊያዎችን አቆምን። ቤተ መቅደሶችን ገነባን። እነዚህን ሁሉ ነገሮች አደረግን። ኦህ፡ የእኛ የሚሲዮናውያን መባ በመላው ይሁዳ ካሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ፡ ይበልጣል። ደህና፡ **እዚህ** እነዚህን ሁሉ ነገሮች እናደርጋለን። ሕዝባችንም ታላቅ አሥራት ከፋዮችና፡ የመሳሰሉት ናቸው" ይሉ ይሆናል። ነገር ግን ሚክያስ ማለትም...

170 አሞጽ እዚያ ቆሞ፡ "ያ እናገለግላለን የምትሉት አምላክ ራሱ ያጠፋችኋል" አላቸው። እንደዛውም ሆነ።

171 አሁን፡ የሚሲዮናውያን ፕሮግራሞችን እየኮነንኩ አይደለም። ትላልቅ አብያተ ክርስቲያናትንም እየኮነንኩ አይደለም። ነገር ግን፡ ችግሩ፡ ሰዎች ዓይናቸውን፡ እዚያ ላይ ማድረጋቸውና... ከቃሉ ላይ ማንሳታቸው ነው። በመጨረሻም፡ ያ በቀጥታ ወደዚያው ነገር ይመራችኋል፡ እናንተም ራሳችሁን፡ ስትንሸራተቱ ታገኙታላችሁ። ቀጥታ ወደ ቃሉ ተመለሱ። ከእርሱ አትርቁ። ኦህ፡ ዛሬ ከምድረ በዳ የሚወጣ ጩኸት፡ ምንኛ ያስፈልገናል። አሁን በእርግጥም እውነት ነው። በእርግጠኝነት።

172 ሌሎች ምክንያቶች ደግሞ፡ የሰዎች ሀሳብ ነው። መመራመር ይፈልጋሉ። የሰውን ዘር ኅብረት ያሳጣው... የመጀመሪያው ነገር ያ ነው፡ እርሱም ሰይጣን ቃሉ እውነት ከመሆኑ ጋር የሚቃረን የአመክንዮ ፕሮግራምን ሲያስተዋውቅ ነው። እና በጣም ምክንያታዊ ይመስላል።

173 እግዚአብሔር በቃሉ አጥሮ በጠበቃቸው ጊዜ፡ ሰይጣን ለሔዋን ምን ብሏት እንደነበረ፡ እስቲ እንመልከት።

174 እግዚአብሔር ሕዝቡን ከጠላት ለመጠበቅ ለመመሸግ የሰጣቸው ብቸኛው ነገር፡ ቃሉ ነበር። የሃይማኖት መግለጫ አልሰጠንም። ከቃሉ በቀር ምንም አልሰጠንም። ያ ነው በቃ። እግዚአብሔርም ወሰን የሌለው፡ ሁሉን ቻይና፡ የማይለወጥ ነው። ሊለወጥ አይችልም። የእርሱ የመጀመሪያው ፕሮግራም ፍጹም ነው። ዳግመኛ ሊለውጠው አያስፈልገውም።

175 ሰው ኃጢአት በሠራና፡ በእርሱና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ያንን ትልቅ ገደል በተሻገረ ጊዜ፡ ራሱንም መመለሻ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ጥሎ ሳለ፡ በመጀመሪያው ውሳኔው፡ በምሕረትና በጸጋ የተሞላው እግዚአብሔር፡ ምትክን ተቀበለ። በምሕረትና በጸጋ የተሞላ አምላክ ብቻ ነው እንዲህ ያለውን ነገር ሊያደርግ የሚችለው። ምትክን ተቀበለ፡ ያም ምትክ ደም ነበረ። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንደገና ኅብረት ሊያደርግ የሚችልበት ብቸኛው ስፍራ፡ በፈሰሰው ደም ስር ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሊያደርግ የሚችልበት ሌላ ምንም ዓይነት ጊዜ አልነበረም፡ በደም ብቻ ካልሆነ በቀር። ይህም ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በሚያደርግበት ስፍራ፡ ፍጹም እውነት ነው።

176 አሁን፡ ሔዋን አጥሯን ጣለች። ሔዋን መመራመር ጀመረች። ሰይጣንም እንዲህ አላት፡ "አሁን፡ አንቺ... አታውቂም። እስካሁን ምንም ትምህርት አልተማርሽም። እኔ እዚህ ውጭ ያለው የሴሚናሪው ፕሮፌሰር ነኝ።" የራሱ ሴሚናሪ። "እልሻለሁ፡ እኛ እዚያ፡ ብዙ ነገሮችን ተምረናል። እግዚአብሔር በጣም ቸር መሆኑን ተምረናል! በሴሚናሪያችን ውስጥ እግዚአብሔር እጅግ ቸር እንደሆነ ተምረናል! እዚያ የጻፈውን ሁሉ እንድታደርጊ አይጠብቅብሽም። እሱ እንደዚያ አይጠብቅም" አላት።

እርሷም፡ “አዎ፡ ነገር ግን፡” “ጌታ አምላክ እንዲህ ብሏል” አለች።

177 አሁን፡ በዚያ በቃሉ ላይ ጸንታ ቢሆን ኖሮ፡ ጥሩ ሰባኪ በሆነች ነበር። ዛሬ እንዳትሰብክ የተከለከለችው ለዚህ ነው። አያችሁ? ከእርሱ አርቋት። አሞጽ ስለዚህ ነገር ምን ይል ነበር? መልዕክቱን ቀድቼው፡ ለአምስት ደቂቃ ያህል ብሰማው ደስ ባለኝ ነበር። በቴፕ ቀርጬው፡ ዓለም ሁሉ እንዲሰማው ባደረግሁት ነበር። ኡህ-ሃህ። ከዚያ በኋላ፡ ስለዚህ ጉዳይ ዝም እል ነበር። አስተውሉ። አዎን፡ ወዳጄ፡ እርሱ ይኮንነው ነበር።

178 የተናገረችውን አስተውሉ። አሁን፡ ሰይጣን እንዲህ አለ... እንግዲህ ከሔዋን ጋር ያንን ማድረግ አልቻለም ነበር፡ ታውቃላችሁ...

179 በአዳም ላይ ያንን ማድረግ አልቻለም ነበር፡ በሔዋን ላይ ግን አደረገ። ስለዚህ ለሔዋን እንዲህ አላት፡ አሁን፡ “አሁን አንቺ **ይህን** ታውቂያለሽ።” እንዲህም አላት፡ “እግዚአብሔር አንቺን ለመጉዳት በጣም ቸር እንደሆነ፡ ታውቂያለሽ። እግዚአብሔር... በእርግጥ አትሞቱም። እርሱ ቸር አምላክ እንደሆነ ታውቂያለሽ።”

180 ዛሬም እንዲህ ያለውን ነገር ብዙ እንሰማለን። እርሱ ቸር አምላክ ነው። ነገር ግን፡ ቸር ለመሆን ደግሞ፡ ፍትሐዊም፡ መሆን አለበት። እርሱን ቸር የሚያደርገው ያ ነው። እርሱ ወዲያና-ወዲህ የሚል አይደለም። እርሱ አምላክ ነው።

181 አሁንም፡ “እግዚአብሔር ይህን ሊያደርግብሽ በጣም ቸር ነው” አላት። ቀጠለና፡ እንዲህ አለ፡ “እንዴ፡ ጥበበኛ ትሆኛለሽ እኮ። እውቀት ይኖርሻል። ንቁና ብልህ ትሆኛለሽ። አ—አሁን የማታውቂውን ነገር ሁሉ ታውቂያለሽ” አላት። አያችሁ?

182 እሷ ማወቅ የነበረባት አንድ ነገር ብቻ ነበር፡ እርሱም ቃሉ ነው። እኛ የግድ የመጀመሪያ ዲግሪ፡ ዶክትሬት፡ የሕግ ዶክትሬትና፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሊኖሩን አይገባም። የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ ብቻ ይበቃል። ማንበብ የሚችል፡ ትንሹ ልጅ እንኳ፡ ሊያውቀው፡ ይችላል።

183 ነገር ግን፡ መመራመር፡ ምንስ አተረፉ? ምን አገኙ? ልክ እዚያው ላይ ፈረሱ። ሰይጣንም የሰውን ዘር ልክ እዚያ ላይ ድል እንደነሳው አወቀ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም እያሸነፋቸው ያለው እዚያ ላይ ነው።

184 አሞጽ የመጣውም ለዚህ ነበር። ምክንያቱም፡ ዝነኝነትና የብዙኃን አመለካከት፡ እንዲሁም፡ ብልጽግናን ያመጣ፡ ታላቅ ፕሬዝዳንት ወይም ንጉሥ ነበር። ሕዝቡም እንደ ዔሳው፡ ሕይወታቸውን ለምስር ወጥ ይሸጣሉ። ለመጉዳት ፈልጌ አይደለም፡ ነገር ግን እውነቱን ግልጽ ለማድረግ ነው እንጂ።

185 እናንተ ዴሞክራቶች በቅርቡ ብኩርናችሁን ሸጣችኋል። በትክክል። እኔ ሪፐብሊካን አይደለሁም። እኔ ክርስቲያን ነኝ። ነገር ግን፡ ወንድሜ ሆይ፡ ምንኛ ውርደት ነው! እንደዚያ አድርጎ ለመምረጥም የተጭበረበረ ማሽን መጠቀም አስፈለገ። ነገር ግን አሜሪካ የፈለገችው ያንን ነው። አገኘችውም። እርሱ ብዙውን ጊዜ የፈለጋችሁትን ይሰጣችኋል።

186 አምላክ ሆይ፡ ቃልህን ሰጠኝ። የምፈልገው ያንን ነው። “ጌታ ሆይ፡ በአንተ ላይ ኃጢአት እንዳልሠራ፡ ቃልህን በልቤ ውስጥ ልሰውር።”

187 ኦህ፡ ሌሎች ይመራመራሉ። ነገር ግን፡ እያችሁ፡ አሞጽ ነቢይ ስለነበረ መመራመር አልቻለም። ቃሉ ወደ እርሱ መጣ። በቃ።

188 ዛሬም እንደ ቃሉ ሁሉ፡ ልትተረጉሙት ይገባል፡ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችሁ ውስጥ በማረጋገጥ እንዲተረጉመው ፍቀዱለት።

189 ያ ነው የተባለው፡ ታውቃላችሁ፡ ኤርምያስ ለነቢዩ—ለሐናንያ የተናገረው፡ ያንን ነው። እንዲህ አለው፡ “ያ ነቢይ በተናገረ ጊዜ፡ የተናገረውም ሲገለጥ፡ ያኔ ነቢያት እርሱ ትክክል እንደነበረ ያውቃሉ።”

190 አሞጽ እዚህ ቢሆን ኖሮ፡ ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል? ከ—ከቃሉ ጋር ይጸና ነበር። የሚያደርገው ያንን ነበር። ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ከመጀመሪያው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት ወጥተን እንደተማርን ይነግረን ነበር። ከመጀመሪያዋ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን በጣም እንደራቅን ይነግረን ነበር። ለእኛ ለጴንጤቆስጤዎች የሚነግረን ይህንኑ ነው። “እንግዲህ፡ ራሳችሁን ለማስተካከል ወደ ሃምሳ ዓመታት ያህል ነበራችሁ፡ እናንተ ግን እስካሁን እዚያ አልደረሳችሁም፡” ይለን ነበር። ኦህ፡ ለሐይማኖት ተቋማዊ ማንነት ምን ይል ይሆን? እንግዲህ፡ ኦህ፡ ቤተ ክርስቲያናትን ስለ ብልግናቸው፡ የሐይማኖት መግለጫዎችን ስለመቀበላቸው፡ በውስጧ ከመወለድ ይልቅ፡ አባል ስለመሆናቸው፡ ይህንን ባይሰጣቸው ባያፈራርሳቸው!

191 እንግዲህ፡ በውስጧ የተወለዳችሁ ከሆነ፡ ወንድሜ፡ እህቴ ሆይ፡ ድርጊታችሁ ይለያል። ከ—ከቃሉ ጋር ትጸናላችሁ። መንፈስ ቅዱስ በውስጣችሁ ካለ፡ የሚመገበው በቃሉ ላይ ብቻ ነው። ኢየሱስም፡ “ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ፡ በእንጀራ ብቻ አይኖርም” ብሏል፡ ከፊል ቃሉ ሳይሆን፡ “ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ” ማለቱ ነው።

192 እርሱ፡ ነቢይ እንደመሆኑ መጠን፡ ይህንን ነገር በእኛ ውስጥ ያይ ነበር። የ... አሞጽ ነቢይ ነበር።

193 አሁን በጥቂት ጊዜ ውስጥ፡ እጨርሳለሁ፡ ነገር ግን እነዚህን ሐሳቦች ብችል በልባችሁ እንዲቀረጹ እፈልጋለሁ። እኔ እናገረዋለሁ፡ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እንዲጸናላችሁ ያደርጋል። አንድ ነገር ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ።

194 አሞጽ ዛሬ ምሽት እዚህ መጥቶ በዚህ መድረክ ላይ ቢቆም፡ ወይም በፊኒክስ ጎዳናዎች ላይ ወዲህና ወዲያ ቢመላለስ፡ ዛሬ በእኛ ውስጥ፡ በብሔራዊ ጉዳያችንም ሆነ፡ በቤተ ክርስቲያናችን ዓለም ውስጥ፡ በሰማርያ ያየውን ነገር ያያል፥ ይህም ሙሉ በሙሉ ለስነ ምግባር ብልሹነት መሰጠትና፡ ከእግዚአብሔር ቃል መራቅ ነው። እጅግ ሃይማኖተኛ የሆነ ቡድን ያያል። እነርሱ፡ ሁሉም፡ እስራኤላውያን ነበሩ። ነገር ግን እርሱ ብ—ብልግናንና፡ የሥነ ምግባር ብልሹነትን አየ። በሕዝቡ መካከል ማኅበራዊና ሥነ ምግባራዊ መበስበስን አየ። በአገሪቱ ላይም፡ የሥነ ምግባር መበስበስን አየ። ከቃሉ ያፈነገጠ መበስበስን አየ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንዝርናን አየ። ማለቴ... አዎ፡ ሁለቱንም፥ ሥጋዊ ምንዝርንም አየ፡ መንፈሳዊ ምንዝርንም አየ። እዚህ ውጭ ያሉትን የሰው የሐይማኖት መግለጫዎችን፡ እንደ ሰው የሐይማኖት መግለጫዎች ወሰደው፡ ከቃሉ ይልቅ እነርሱን መቀበላቸው፡ ይህም በእግዚአብሔር ላይ መንፈሳዊ ምንዝር መፈጸም ነው። ራዕይ 17ም እንዲህ ይላል፡ ይህም እነርሱ፡ ይህች

አመንዝራ፡ ኃጢአት ሠራች፡ ምክንያቱም፡ “አሕዛብ ሁሉ ከዝሙትዋ ቁጣ ወይን ጠጅ የተነሳ ሰክረዋል” ይላልና። አዎን። ሁሉም ነገር ፍጹም የተለየ ሆኖ አይተናል። እርሱ ያንን የሥነ ምግባር መበስበስ፡ አይቷል።

195 አሞጽ ግን፡ መንግሥትን ፈጽሞ አልወቀሰም። ሰሙኝ። አሞጽ በጻፋቸው ቃላት ሁሉ፡ መንግሥትን ፈጽሞ አልወቀሰም። ነገር ግን እንዲህ ያለውን መንግሥት ስለመረጡ ሕዝቡን ወቀሰ። ኦህ፡ እኔ...

196 ደከማችሁ’ዴ? [ጉባኤው፡ “አይ” አለ።—አርታዒ።] እንግዲያውስ፡ ጥቂት ደቂቃ ታገሱ። አያችሁ?

197 መንግሥታችሁን አትውቀሱ። ሕዝቡ ለአሸዋ ድምፅ በሚሰጥበት ሁኔታ መንግሥት በዓለት ላይ ቤት ሊገነባ አይችልም። ሕዝቡ የሚፈልገው ያንኑ ነውና።

198 ወንድሞቼ፡ አገልጋዮችና፡ ጥሩ ሰዎች እዚያ እንደተቀመጡ ሳውቅ፡ መድረክ ላይ ብዙ ጊዜ ነገሮችን እናገራለሁ። ወደ አንድ ጥግ ወሰጃቸውም፡ አነጋግራቸዋለሁ። እነዚህን ነገሮች እያወቅሁ፡ ለወንድሞቹ መናገር፡ ግዴታዬ ነው። እኔም አነጋግራቸዋለሁ። እነርሱም፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ትክክል እንደሆንክ እናውቃለን፡ ግን ምዕመናኔ ጥለውኝ ይወጣሉ” ይላሉ። አያችሁ? አያችሁ? ሕዝቡ የምትፈልጉት ይህንን ነውና። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።] አያችሁ? አትችሉም። ነገሩ ያለው ሕዝቡ ጋር ነው።

199 አሁን፡ እዚህ መንገድ ላይ አንድ መደብር ብከፍትና ዛሬ ላሉት ሴቶች፡ የድሮ-ፋሽን፡ ባለ ረጅም-ታኮ፡ የዳንቴል ጫማ ብሸጥላቸው፡ ብላችሁ ብታሰቡ? ምናልባት በአንዲት ጥንድ ውስጥ ብቻ፡ ዛሬ ካለው ሙሉ መደብር የ—የሚበልጥ ቆዳ ይኖራቸዋል። ነገር ግን አንዷን ጥንድ በሃምሳ ሳንቲም እንኳ ብሸጣቸው፡ በራብ እሞታለሁ። ለምን? ምክንያቱም እናንተ አትፈልጓቸውም።

200 እነዚያን ሰፊና ረጅም የድሮ-ፋሽን ቀሚሶች፡ ዛሬ ለሴቶቹ ብሸጥላቸው፡ ይገዙኛል ብላችሁ ታስባላችሁ? በእርግጥም አይገዙኝም። እነርሱ የሚፈልጉት ልክ እንደ ሶሰጅ ቆዳ፡ በሰውነታቸው ላይ ተጣብቆ የሚታይ ልብስ ነው። በ—በጣም የጠበቀ እንዲሆን ነው የሚፈልጉት። በመንገድ ላይ ሲራመዱ፡ አራት ወይም አምስት ድግሪዎች፡ ወዲህና፡ ወዲያ እየተወዛወዙ፡ ተረከዝ ያለውን ጫማ አድርገው፡ ጭንቅላታቸውን አውጥተው ይሄዳሉ። ይህንን፡ የምናገረው ለቀልድ አይደለም። እዚህ ሰፍራ ለቀልድ ቦታ የለውም። ነገር ግን እውነቱ ይህ ነው። እኔ ጥሩ ትምህርት የለኝም። የምናገረው ነገር እንዲገባችሁ ለማድረግ የምገልጽበት መንገድ ይህ ብቻ ነው፡ ታውቃላችሁ፡ ስለምን እንደምናገር ታውቃላችሁ። አያችሁ? አሁን፡ እውነቱ ይህ ነው። እነዚያን ቀሚሶች አይገዙትም።

201 ባለፈው ማታ መድረኩ ላይ፡ አንዲት ትንሽ ህንዳዊት ሴት ወደዚያ መጣች። ትንሿን እጇን ለመጨበጥ ፈልጌ ነበር። ወንድም ግሩመር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ ወይም የሆነ ቦታ። እናቴ ትለብሰው እንደነበረው ዓይነት ቀሚስ ለብሳ ነበር። በልቤም፡ “መልካም፡ እመቤቴ ልብሽ ይባረክ” ብዬ አሰብኩ። ጌታም ገና ወደ እኔ ከመድረሷ በፊት፡ እዚያው ፈወሳት። እሷ... አያችሁ? “ዝም ብ—ብ—ብል ይሻላል” ብዬ አሰብኩ። አያችሁ? “የሆነ ጊዜ እጋጣሚው እስኪመጣ ድረስ ብቻ ጠብቅ።” አያችሁ? ያም ሆነ።

202 እንግዲህ፡ እነዚያን ቀሚሶች ዛሬ ልትሸጧቸው አትችሉም። ምናልባት ለህንዳውያን ልትሸጡ ትችላላችሁ፡ እነርሱም ቢሆኑ ብዙ አይደሉም። እነርሱም እንደ ሌሎቹ ልቅ እየሆኑ ነው። በጣም የበዙ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች አሉባችሁ። ልጆቻችሁም ወደ ውጭ እየወጡ ነው፡ እነዚህም ዘመናዊ፡ ነጮቹ፡ የትምህርት ቤት መምህራንና፡ ሌላው ሁሉ ከንቱ ነገር እየገባ ነው። ከረጅም ጊዜ በፊት፡ እንደ ሲቲንግ ቡልና እንደ እነርሱ ዓይነት ብትሆኑ፡ ይሻላችሁ ነበር።

203 በአፍሪካ፡ እዚያ ጥቁር ዘሮች ባሉበት፡ ምን ያደርጋሉ? እነዚያ ሚሲዮናውያን፡ ወደዚያ ሄደው፡ ማንበብ፡ ማጻፍና፡ ሒሳብ ያስተምራሉ። ነገር ግን... ለምን፡ እነርሱ፡ በጎሳዎቻቸው ውስጥ፡ ስለ ሥነ ምግባር የሚያውቁት ነገር፡ ክርስትና ሊያመጣላቸው ከሚችለው፡ በላይ ነው። ልክ ነው። እዚያ ካሉት ሴቶች መካከል፡ በዙሉ ጎሳ ውስጥ ያለች አንዲት ሴት፡ ለጋብቻ እስከሚገባት ዕድሜ ድረስ ቆይታ፡ ማንም ሚስት አድርጎ፡ ካልወሰዳት፡ ከዚያ መውጣት አለባት። ከዚያ በኋላ የጎሳው አባል ተደርጋ አትቆጠርም። አይ፡ ወዳጄ። ስታገባም፡ ድንግልናዋ ይፈተናል። ጥፋተኛ ሆና ከተገኘች ግን፡ ያደረገባትን ሰው መናገር አለባት፡ ሁለቱም በአንድ ላይ፡ ይገደላሉ።

204 ያ ዓይነቱ አሰራር ቢኖረን እዚህ አካባቢ ብዙ ግድያ ይኖር ነበር። አይመስላችሁም? ልክ ነው። ወንዶቹንና ሴቶቹን ለመቅበር በቂ ቀባሪዎች አይኖሯቸውም ነበር። በእርግጥ። "ለማንኛውም፡ ግን ሞታችኋል፡ አታውቁትምም።" ስለዚህ ችግሩ ያ ነው። አያችሁ? ዳሩ ግን አሁን፡ እጅግ በጣም፡ ልክ ነው።"

205 ከዚያስ ምን ታደርጋላችሁ? ወደዚያ ይወስዷቸዋል፡ ትምህርትም ያስተምሯቸዋል። ከዚያም በመንገድ ላይ ታገኟቸዋላችሁ። ቀድሞም የነበራቸው፡ የራሳቸው የጎሳ ኃጢአት ነበራቸው፥ መጥተው ደግሞ፡ የነጩን ሰው ኃጢአት ይጨምራሉ፥ ከዚያም ከነበሩበት ይልቅ አሥር እጥፍ የገሃነም ልጆች ይሆናሉ። የሚያስፈልጋቸው ብቸኛው ነገር ባሉበት ሆነው ክርስቶስን ማግኘት ነው። በትክክል።

206 የአሜሪካ ሕንዶችም ሁኔታ እንደዚሁ ነው። በዚህች አገር ውስጥ፡ እጅግ የማዝንለት ሰው ቢኖር፡ ያው ሕንዳዊ ነው። በእርግጥም እጅግ ተበድሏል! እኔ... እኔ አንድ ሰው ብቻ ነኝ፡ ነገር ግን ከእነርሱ ጋር ነኝ። አዎ፡ ወዳጄ። ጌታ ከዚህ ዓይነት የአገልግሎት መስክ ቢጠራኝ፡ መልእክቴ ካለቀ በኋላም፡ የምኖርበት ጊዜ ቢሰጠኝ፡ ወደ ህንዳውያን እሄዳለሁ። አዎን፡ ወዳጄ። አዎን፡ ወዳጄ። ማይ!

207 አሞጽ በጮኸ ጊዜ ምን ሊያደርግ እንደሚችል እናያለን። መላው ሥርዓታችን ይወገዛል። በእርግጥም...

208 (ቀደም ሲል እንዳልኩት) ሕዝቡ ለአሸዋ ድምፅ በሚሰጥበት ሁኔታ፡ መንግሥት በዓለት ላይ ቤት ሊገነባ አይችልም።

209 ታዲያ ቤተ ክርስቲያናችሁን በዓለቱ ላይ እንዴት ትገነባላችሁ? አድማጮቹ ማለትም ከሕዝቡ መካከል አንዳንዶቹ ሊያባርሩት በሚፈልጉበት ሁኔታ፡ ሰባኪው እንዴት በመድረክ ላይ ቆሞ፡ ስለ ዓለቱ ይሰብካል፡ እንዲሁም እንዴት በሙሉ ወንጌል መሠረታዊ ነገሮች ላይ፡ ቤተ ክርስቲያኑን ይገነባል? አሁን፡ ሰባኪው ድፍረቱ፡ የእግዚአብሔርም መንፈስ ኖሮት፡ በሩን በመዝጋት፡ "ለዚያ

ነገር የሚቆም ሌላ ሰው ፈልጉ እንጂ ለእኔ አይሆንም” ብሎ ባለመናገሩ እወቅሰዋለሁ።” ያንን የሚያደርግን ሰባኪ—አደንቃለሁ።

210 ዳሩ ግን የተቀባ የእግዚአብሔር ሰው ቃሉን ሊያመጣላቸው ሲሞክር፡ ከዚያም ከቃሉ ጋር የማይስለፉ ከሆነ ለዚያ ጉባኤ ወዮለት። ልክ ነው። ታዲያ፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ በአግባቡና በስነምግባር የማትኖር፡ እንዲሁም፡ የወንጌልን ሀሁ የማትማር፡ እንንዲህ እና እንዲያ—ከሆነች፡ እንዴት ዘጠኙም ስጦታዎች የሚሠሩባት ቤተ ክርስቲያን ሊኖረው ይችላል? ከዚያም፡ “የተሻለ ሰባኪ ቢኖረኝ ኖሮ” ይላሉ! እንዴ፡ ጥፋቱ የራሳችሁ እኮ ነው። በትክክል።”

211 ለሃይማኖት ነጻነት ብለን ወደዚህ የመጣነው፡ ይህ የእኛ የአሜሪካውያን፡ የአገራችን ጥፋት ነው። ከምን ነጻ ለመሆን? አሁን ግን ተመልሰን ነጻ ለመሆን የመጣንበትን ያንኑ ነገር፡ በዋና ከተማችን እያነገሥን ነው።

212 ይህች አገር ልክ እንደ እስራኤል ናት። እነርሱም፡ እስራኤላውያን፡ ወደ ፍልስጤም ገቡ፡ ነዋሪዎቹንም አባርረው ምድሪቱን ወረሱ። መጀመሪያ ላይ፡ የሚመሯቸው አ—አንዳንድ ጥሩ ጥሩ ሰዎች ነበሯቸው። ዳዊት፡ ሰሎሞንና፡ ታላላቅ ሰዎች። በመጨረሻም፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ እየመረጡ፡ እየገፋና፡ እየሾሙ፡ አረማዊት ሴት ያገባ፡ አክዓብ የሚባል ንጉሥ እስከሚያገኙ ድረስ ቀጠሉ። አሁን፡ አክዓብ በራሱ ጥሩ ሰው ነበረ። እርሱ... ኦህ፡ ት—ትክክለኛውን ነገር ማድረግ ይፈልግ ነበር፡ ነገር ግን በዚያች ሚስቱ ምክንያት፡ ትክክለኛውን ነገር ማድረግ አልቻለም።

213 አሁን፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ስለተናገርኩት ሰው ምንም ቅሬታ የለኝም። ምናልባት ጥሩ ሰው ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አንገቱን የሚያጣምመው ከጀርባው ያለው፡ ያ የአመንዝራዋ ሥርዓት ነው። ነገሩን የሚያበላሸውም ያው ነው። እርሱም በቻለው መጠን፡ በቀላሉ ገብቶ፡ ሁሉንም ነገር ያፈራርሰዋል።

214 ታውቃላችሁ—አሁን እኛ... የአገራችን ዕዳ በጣም ከመብዛቱ የተነሳ፡ ከዛሬ አሥራ አራት ዓመት በኋላ፡ ከምናገኘው ግብር ላይ በተበደርነው ገንዘብ እየከፈልን ነው። ይህ ሥርዓት ሲፈርስ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ታውቃላችሁ?

215 ካስትሮን፡ በእርግጠኝነት፡ እቃወመዋለሁ። እርሱ ኮሚኒስት ነው። ልክ ነው። እቃወመዋለሁ። ነገር ግን የገንዘብ ምንዛሬውን ሲለውጥና ወርቁንም ሲመልስ፡ ቦንዶችን ገዝቶ ወርቁን ሲመልስ ጥሩ ነገር አድርጓል።

216 ይህንን ማድረግ ይኖርብናል፡ ካልሆነ ግን ፊታችን ላይ የተጋረጠ አንድ ግልጽ ነገር አለ፡ ይኸውም፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የዓለምን ሀብት በሙሉ መያዟ ነው። ገንዘቡም አላት። ቦንዶቻችንን መልሳ ለመግዛት፡ ወርቁም አላት። በትክክልም እንደዛው ነው። እነዚህ የውስኪ ነጋዴዎች፡ የትንባሆ ነጋዴዎችና፡ የአገሪቱ ታላላቅ ሰዎች ሥራቸውን ላለማጣትና፡ ገንዘባቸው ዋጋ እንዳያጣ ብለው አገራቸውን አይሸጡም ብላችሁ ታስባላችሁ? ተመልሰው ሄደው ያንን ገንዘብ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ይወስዳሉ፡ ያኔም አገሪቱ ተሸጣለች ማለት ነው። በትክክል። መጽሐፍ ቅዱስ፡ “የዓለም ሀብት” ብሎ አይተነብይምን? እኔ ፖለቲከኛ አይደለሁም፡ ብልጥም ሰው አይደለሁም፡ ነገር ግን ጌታን ስላወቅሁት አመሰግነዋለሁ። ይህ ደግሞ እውነት ነው። ነገሩ የሚያርፈው፡ ልክ እዚያ ላይ ነው። ተመልከቱት። ልክ መሆኑንና አለመሆኑን ትመለከታላችሁ። ብቻ...

ሁላችንም ይህን ለማየት በሕይወት እንቆያለን ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡ ረጅም ጊዜም የምንቆይ አይመስለኝም።

217 ግን ምን ታደርጋላችሁ? ቤተ ክርስቲያንን እንዴት እንገነባለን? አገርን እንዴት እንገነባለን? አሁን በዚህ ሁኔታ ላይ አገርን እንዴት እንገነባለን? ምንስ እናደርጋለን?

218 ምናልባት ዝም ብዬ፡ ወደ ሌላ ርዕስ ብሄድ ይሻላል። ነገር ግን፡ ታውቃላችሁ፡ ምን እያልኩ እንደሆነ እስክትረዱ ድረስ በቂ ነገር ተናግሬአለሁ። አያችሁ? ማለቴ የገባችሁ ይመስለኛል።

219 የምንፈልገውን ተመልከቱ። አንተ፡ የምትፈልገውን ታያለህ? የምታገኘው የምትፈልገውን ነው። ያ የእናንተ ምኞት ነው።

220 ዛሬ ያሉትን ያለ ምንም ቁጥጥር የሚቀርቡ፡ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ተመልከቱ። ቀደም ሲል፡ ለልጆቻችን ስህተት ነበር፡ ወደ ከ—ከተማ ሄደው ባዮስኮፕ እንዲያዩ፡ ፊልም እንዲያዩ—አንፈቅድላቸውም ነበር። አሁን ግን ዲያብሎስ ነገሩን መልሶ ወደ ቴሌቪዥን ለ—ለወጠውና፡ በእያንዳንዱ ቤት ውስጥ አስቀመጠው።

221 ያ ምንም አልነበረም፡ ትክክለኛውን ነገር ካያችሁበት፡ ቴሌቪዥኑ ችግር የለውም፡ በእርግጥም፡ ነው።

222 ነገር ግን ምን ታደርጋላችሁ? በእያንዳንዱ ሰዓት ይበልጥ እየበሰበሰ ነው፡ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት፡ መሳደብ፡ መርገም፡ እርቃን ሴቶች፡ የሥነምግባር ብልሹ ድርጊቶች፡ እነዚህ የልጆችን አእምሮ ይመርዛሉ፡ እንዲያውም ቢትኒኮችንና፡ ወሮበሎችን ነው ያሳደግነው፡ በትክክል። ይህ በትክክል እውነት ነው። ብትመለከቱት ይሻላል።

223 መላው አገራችን ወደ ወሮበላነት እየተቀየረች ነው። ማንኛውም ወጣት ሱሪው በወገቡ ላይ ተንጠልጥሎ፡ ራሱ ወደ ኋላ ተዘቅዝቆ፡ ፀጉሩም እንደ ወይዘሮ ኬኔዲ ወተር-ሄድ የፀጉር አቆራረጥ በአንገቱ ላይ ተዘርግፎ፡ እንደ ወሮበላ፡ እየተዘዋወረ፡ ይህንንም አሜሪካዊነት ብሎ ይጠራዋል? ከጸጋ ወድቃችኋል። ንስሐ ግቡና ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ፡ ካልሆነ ግን ትጠፋላችሁ። ለዚህ ነው፡ የ—የፈለግነውን እንድናደርግ የሚፈቅድልንን ሰው እንዲሾምልን የምንፈልገው። በትክክል።

224 አብያተ ክርስቲያናትም ሁኔታቸው እንደዚሁ ነው። ፓስተር መምረጥ ይፈልጋሉ፡ ነገር ግን እዚያ ቆሞ ወንጌልን የሚገሥጻቸውን አይደለም። ነገር ግን በመዋኛ ልብስ ተዘርግተው እንዲታዩ፡ በቤተ ክርስቲያን ቤዝመንት ቁማር መሰል ጨዋታዎችን እንዲጫወቱ፡ በፈለጉትም መንገድ እንዲኖሩ፡ ያልተመረመሩ የቴሌቪዥን ወይም የሬዲዮ ፕሮግራሞችን፡ ቆሻሻንና ርኩሰትን እንዲከታተሉ፡ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንንና ዓለምን አብሮ የሚያቀላቅልላቸውን ሰው ነው።

225 አሞጽ በእንዲህ ያለ ነገር ላይ ቢጮህ ምንም አያስደንቅም። ሰዎች ነገሩን በምርጫቸው እያስገቡት ባለበት ሁኔታ እርሱን ይቀበሉታል ብላችሁ ታስባላችሁ?

226 ፓስተሩ ከሃያ ደቂቃ በላይ ከሰበከ፡ የአደራ ቦርዱ ወደ ክፍል ጠርተውት እንዲህ ይሉታል፡ “ተመልከት፡ ፓስተር። እኛ አንተን እዚህ ያመጣንህ—እንዲህ ያለ ነገር እንድታደርግ አይደለም። የሃያ-ደቂቃ ፕሮግራም ነው ያለን። ያ ሲያልቅ፡ ታበቃለህ።”

227 ሊያደርገው የሚገባው እነዚያን የአደራ ቦርድ አባላት በሩን ከፍቶ ማባረርና፡ መጽሐፍ ቅዱሰን ይዞ እንደ ጳውሎስ፡ ሌሊቱን ሙሉ መሰበክና፡ የሙታንን ትንሣኤ ማየት ነው። በትክክል። ከሕንፃው ቢያወጡትም፡ የመንገድ ዳር በቂ ነው። “እግዚአብሔር ከነዚህ ድንጋዮች… ”

228 ቴሌቪዥን፡ ያለ ገደብ የሚታዩ ፊልሞች፡ ርኩሰት፡ ቆሻሻ፡ ይህ ሁሉ ምሳሌ ሆኗል። የዛሬዎቹን ትንንሽ ልጆቻችንን ተመልከቱ። ልጃገረዶቻችንን እዩ። ከትምህርት ቤት የሚመለሱ፡ ዕድሜያቸው ከስድስት፡ ከሰባት፡ ከሰምንት ዓመት ያልበለጠ ትንንሽ ልጆች፡ ሲጋራ ሲያበሩ ተመልከቱ። ለምን እንዲህ ሆነ? ምናልባት እናቶቻቸው በፊት ያደርጉት ስለነበረ ይሆናል። እነርሱ ባያደርጉት እንኳ፡ አብረው የሚውሏቸው ልጆች ያደርጉታል። ልጆቻችሁ ከማን ጋር እንደሚጫወቱ ተከታተሉ። በትክክል። እዚህ ደግሞ…

229 ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ ባለቤቴም ታውቀዋለች፡ ማዕድ ላይ ተቀምጠን ነበር። ትንሹ ልጄ ዮሴፍ ሰካራም መርከበኛን እንኳ የሚያሳፍር ቃል ተናገረ። እኔም ዞር አልኩ። “ይህ ምንድን ነው? ” አልኩት፡ እናቱም ራሷን ልትስት ምንም አልቀራትም። ትንሹ ልጅ ግን ምንም የማያውቅ ይመስል ነበር።

230 እርሱም ዓይኖቹ በእንባ ተሞልተው፡ “አባዬ፡ ምንድነው ችግሩ? ” አለኝ።

231 እኔም፡ “ከእንግዲህ እንዲህ ያለ ነገር ፈጽሞ እንዳትናገር” አልኩት። እርሱ ግን ነገሩ ምን እንደሆነ አያውቅም ነበር። ቆይቶ እንደታወቀው ግን፡ በትምህርት ቤት ያሉ ልጆች ያንን ቆሻሻ ቃል ይጠቀሙ ነበር። እኔም፡ “ውዴ፡ ያ ከዲያብሎስ ነው” አልኩት።

232 አያችሁ፡ ነገሩ ይኸው ነው፡ ልጆቻችሁ። ወንድም ሆይ፡ ነገሩ እርስ በርስ እስከመበላላት የደረሰ፡ እንዲህ ያለ የኃጢአት ድብልቅልቅ የሆነበት፡ ደረጃ ላይ ደርሷል። ኦህ፡ ማይ! የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፡ ኃጢአት-ወዳዶች፡ ተድላ-ወዳዶች! ኦህ፡ ማይ!

233 “ሃያ ደቂቃ ይበቃል። የሌሊቱን ፊልም ማየት አለብኝ” ይላሉ። አያችሁ? “ቶሎ በልና ይህንን ከዚህ አውጣው። ያንን ማድረግ አለብኝ” ይላሉ። አያችሁ? ሃይማኖታዊ ግዴታቸውን ተወጥተዋል። ወደዚያ ሄደዋል፡ ያም ይበቃቸዋል።

234 ነገር ግን፡ እነግራችኋለሁ፡ ከእግዚአብሔር መንፈስ የተወለደ እውነተኛ ወንድ ወይም ሴት የእግዚአብሔርን ቃል እየጠጡ፡ ሰዓታትን ተቀምጠው ያሳልፋሉ። ያ ብቻ አይደለም፡ ነገር ግን ቃሉ ሲነካቸው፡ በዚያው መልሕቅ ይሆንላቸዋል ሕይወታቸውንም ይለውጣል። አሜን። አዎ።

235 ይህ የሕዝባችን ሞኞት ነው። አጠቃላይ ሥርዓታችን የበሰበሰና የተበላሸ ነው። ይህ የሕዝባችን ፍላጎት ነው።

236 አንድን ጥሩ ሰው ወሰዳችሁ፡ እንበልና፡ ጥሩ ሰው ወሰዳችሁ፡ ተድላን-በሚወዱ ቤተሰቦች መካከል ብታስቀምጡት፡ የዚያን ሰው ሕይወት የውሻ

ህይወት ያደርጉታል፥ ወይም፡ ጥሩ ሴት ወሰዳችሁ፡ ከሁለቱ አንዱን፡ በተቀላቀለ ቤተሰብ ውስጥ አስቀምጧቸው። ለምን፡ መላው ቤተሰብ ለእግዚአብሔር መገዛት አለበት። ልጆቻችን እስኪድኑ ድረስ፡ መጸለይና፡ ቤታችንን በሥርዓት መጠበቅ የኛ ኃላፊነት ነው። አዎን።

237 እኛም ከጠላቶቻቸው ጋር ስምምነት እንዳደረጉት፡ እንደ እስራኤል ነን። ያንን ለማድረግ ግን በመጀመሪያ ከቃሉ መራቅ ነበረባቸው። ይህም አሜሪካ ከቃሉ ምን ያህል እንደራቀች ያሳያል።

238 ታውቃላችሁ፡ ው—ውሸትን ለማመን መጀመሪያ እውነትን መካድ አለባችሁ። በትክክል። በትክክል እንደዚያ ነው። ሔዋን የሰይጣንን ውሸት ለመቀበል መጀመሪያ የእግዚአብሔርን ቃል መካድ ነበረባት። ያኔ ከቃሉ መራቅ ነበረባቸው፡ አሁንም እንደዚያው ነው፡ ያለምንም ተኩስ ሮም ነገሩን እንድትቆጣጠር እየተፈቀደ ነው። ስለነዚህ ነገሮች የእግዚአብሔር ቃል ምን እንደሚል አያውቁም። ችግሩም ይኸው ነው።

239 ወደ ቃሉ የሚመልሰን፡ እውነተኛ ነቢይ መነሳት ያስፈልገናል። በትክክል። ተስፋ ተሰጥቶናል። ተስፋ ተሰጥቶናል። አዎን፡ በእርግጠኝነት። ሚልክያስ 4 እንዲህ እንደሚያደርግ ተናግሯል። “የሕዝቡንም እምነት እንደገና ወደ እነዚያ የጴንጤቆስጤ አባቶች ይመልሳል።”

240 እስራኤልን የሚወዷት እነዚያ እግዚአብሔርን የማያውቁ ወገኖች አንድ ቀን እንደሚያጠፏት አሞጽ ያውቅ ነበር። አሁን ይህንን በአክብሮት ልናገር። ዛሬም አንድ አማኝ፡ የዚህች አሜሪካ እግዚአብሔርን የማያውቁ ወዳጆች፡ እንደሚያጠፏት ያውቃል። ለፖለቲካ ያላችሁ ፍቅር! ይህ ለጥቂት ጊዜ በልባችሁ ይሰርጽ። ያ አገሪቱን ያጠፋታል። ለዓለም ያላችሁ ፍቅር፡ ከቃሉ ጋር አለመስማማታችሁና ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ አለመጣራችሁ፡ ቤተ ክርስቲያኑን ያጠፋታል። ይህ በትክክል እውነት ነው። ይህ እንደገባችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። ቤተ ክርስቲያን እርሱን ትታለች፡ የሕይወት ቃሉንም ትታለች። ዓለሙ ሁሉ እንደ መሰናከያ ዓለት፡ በእርሱ ላይ ይሰናከላል። ዛሬም ያንኑ ያደርጋሉ። አዎን። አሞጽ እዚህ ቢሆን ኖሮ፡ መላውን ሥርዓት ይቃወም ይጮኽበት ነበር።

241 አሁን፡ በማጠቃለያዬ፡ በቁጥር 8 ላይ ያለውን፡ ይህን ማለት እፈልጋለሁ። በደምብ አዳምጡ። እንዲህ አለ፡ “አንበሳ ሲያገሣ፡ የማይፈራ ማን ነው? ”

242 እኔ አንበሶችን አድኛለሁ። አንበሳ የእንስሳት ንጉሥ ነው። በአፍሪካ በእነዚያ በረሃዎች ውስጥ፡ በሌሊት ሰዓት፡ በነዚያ ትንንሽ ሳሮች፡ ወይም እሾሆች ስር ተኝቼ ነበር።

243 አንበሳ በሚተኩስ ጠመንጃ ፊት ለፊት ይዘላል። ያንን አይፈራም፡ ነገር ግን ወደ እሾህ አይጠጋም። ተረቱን ሰምታችሁ ይሆናል። ነገር ግን፡ ያ እውነት ነው፡ አንበሳ ወደ እሾህ አይጠጋም። እንደዚያ ዓይነት የእሾህ ጎጆዎችን ይሠራሉ፡ አንበሳውም በላዩ ላይ አይዘልም። እንዲያ ባይሆን ኖሮ፡ በቀጥታ፡ መግባት ይችል ነበር።

244 ከቢሊ ጋር። አንድ ቀን ሌሊት እዚያ ተኝተን፡ ያ ግዙፍና ያረጀ አፉ ይህን ያህል ከራሴ ርቆ፡ **በ**አቅራቢያው ድምፅ ሲያወጣ ትዝ ይለኛል፡ አያችሁ፡ ሆኖም

አ—አይቀርብም ነበር። ያ ትልቅ መዳፉም፡ **ያንን** የሚያክል፡ በምድር ላይ ሲራመድ ይሰማ ነበር።

245 ከጅቦች፡ ከሳቂታው ጅብ፡ ከአልቃሻው ጅብ፡ ሁ—ሁ—ሁሉንም ዓይነት ድምፅ ትሰማላችሁ እነርሱም ይጮኻሉ። ዝ—ዝንጀሮዎችን፡ ጦጣዎችን፡ ቀ—ቀጭኔዎችንና፡ ዝሆኖችን በዚያ ታላቅ ድምፃቸው "ዊ" ሲሉ ትሰማላችሁ። እስከ ብዙ ማይሎች ድረስ ድምፃቸው ይሰማል። ትንንሽ ትሎችና ጥንዚዛዎችም የራሳቸውን ድምፅ ያሰማሉ። ነገር ግን አንበሳው በሩቅ ሲያገሳ፡ ጥንዚዛዎቹ ሳይቀር ጸጥ ረጭ ይላሉ። ያዳምጣሉ። ለምን? ንጉሣቸው ነውና። ያዳምጡታል።

246 መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ "እግዚአብሔር... አንበሳ ሲያገሳ፡ የማይፈራ ማነው? እግዚአብሔር ሲናገርስ፡ ትንቢት የማይናገር ማን ነው? " ከዚህ መራቅ እንዴት ይቻላል? እግዚአብሔር ሲናገር፡ ነቢዩ የተነገረውን ቃል ይጮኻል። እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ...

247 አንበሳ ሲያገሳ፡ ጥንዚዛዎቹና፡ ሁሉም ነገር፡ ጸጥ ይላሉ፡ ምክንያቱም ይፈራሉና። ን—ን—ንጉሣቸው እ—እየተናገረ ነው። እ—እርሱ ሲናገር ንጉሣቸውን ለማክበር የሚያስችል በቂ ማስተዋል፡ ድፍረትና፡ አክብሮት አላቸው።

248 ስለዚህ፡ እግዚአብሔር በቃሉ ይናገራል፡ ፍጥረቱ የሆነ ሁሉ ልብ ይበል ይሰማ። በእነዚህ የመጨረሻ ቀናት እርሱ እየተናገረ ነው። ቃሉን እያወጣ ነው። ለመንግሥቱ የሆነ ፍጥረት ሁሉ እርሱ ለሚለው ትኩረት ይስጥ። አቁሙ። ራሳችሁን መርምሩ። አሁን እያገሳ ነው፡ በተረጋገጠው ቃሉ እያገሳ ነው። ራሱን እያሳወቀ ነው። በእነዚህ የመጨረሻ ቀናት እርሱ ሲያገሳ፡ ልብ እንበል፡ እግዚአብሔር መጀመሪያ ሳያገሳ ፈጽሞ አንዳች ነገር እንደማያደርግ አውቀን፡ የሆነ ነገር ሊሆን እንደሆነም እንወቅ። እርሱ ሲያገሳ፡ ከዚያ ጩኸት በኋላ የሆነ ነገር ይከተላል፡ አዎ፡ ምክንያቱም እርሱ እየመጣ ነውና።

249 እርሱም እንዲህ አለ፡ "አ—አ... አንበሳስ ያለ ምክንያት ያገሳልን? ደቦል አንበሳስ፡ አንዳች ሳይዝ፡ ከዋሻው ይጮኻልን? " አያችሁ?

250 እግዚአብሔር የሚያገሳበት ምክንያት አለው፡ ምክንያቱም ፍርድ በደጃፍ መሆኑን ያውቃልና። የእርሱም ቃል፡ የእርሱ ቃል፡ ነቢይ ነው። አዎ። "**ይህ** የኢየሱስ ክርስቶስ ትንቢት ነው።" እግዚአብሔር በተጻፈው ቃሉ አማካኝነት ራሱን ለእኛ የሚገልጥበት፡ መገለጥ ነው። እርሱም ቃሉ ነው። አሁን፡ **ይህ**፡ የእርሱ ቃል ነው። በእርሱ ላይ ምንም ሊጨመር ወይም ከእርሱ ምንም ሊቀነስ አይችልም፡ ነገር ግን ልክ እንዳለ መኖርና መስተካከል አለበት። ከእርሱ አንዳች ልንቀንስ ወይም በእርሱ ላይ አንዳች ልንጨምር፡ አንደፍርም። እግዚአብሔር አሁንም አምላክ ነው። እርሱ እያገሳ ነው።

251 እርሱ እንዲህ አለ፡ "በኖኅ ዘመን እንደነበረው፡ የሰው ልጅ መምጣትም እንዲሁ ይሆናል። ይበሉ፡ ይጠጡ፡ ያገቡና፡ ይጋቡም ነበር፡ ብልግናም ሞልቶ ነበር።"

252 "ደግሞም በሎጥ ዘመን እንደነበረው" ይሆናል፡ እርሱ ራሱ በሥጋ ተገልጦ በመምጣት፡ እዚያ ለአብርሃም ማንነቱን አረጋግጦለታል። "የሰው

ልጅ በሚገለጥበት ቀን እንዲሁ ይሆናል፡” አለ። እነዚህን ነገሮች ተከታተሉ። የምሽቱ ብርሃን እየበራ ነው።

253 ኦህ፡ ዛሬ አሞጽ እዚህ ቢኖርና፡ ቢያገሳ ኖሮ፡ ሥርዓታችንንና ወጋችንን ያፈራርሰው ነበር፡ የእግዚአብሔርም ቃል በድል ይነግሥ ነበር።

እንጸልይ።

254 የሰማይ አባት ሆይ፡ እንደገና ተናገር። ጌታ ሆይ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ በኃይል አገሳ። እርሱ የዘመኑ ነቢይ ነው። እርሱ እውነትን ይናገር ዘንድ፡ በወንዶችና በሴቶች ልብ ውስጥ መንገድ እየፈለገ ያለ፡ የዘመኑ ነቢይ ነው። ጥቂቶችን እያገኘ በመሆኑ በጣም ደስ ይለኛል። የሰማይ አባት ሆይ፡ ዛሬ ምሽት እዚህ ውስጥ ብዙዎችን እንዲያገኝ፡ በአክብሮት ለመቀበል ዝግጁ የሆነንም ሰው እንዲጠቀም፡ እጸልያለሁ። ሁሉን የሚችል አምላክ በቃሉ በኩል ሲያገሳ ሲሰሙ፡ ፍርድ በደጃፍ ነው።

255 አንበሳ ሲያገሳ፡ እየመጣ ነው። ን—ንጉሥ ወደ ፊት እየተራመደ ስለሆነ፡ እያንዳንዱ ፍጥረት ቢደበቅ እንደሚሻለው ያውቃል።

256 አምላክ ሆይ፡ የነገሥታት ንጉሥ ሲያገሳ፡ ያለን የደኅንነት ሰፍራ አንድ ብቻ ነው፡ እርሱም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው። የደኅንነት ሰፍራ አለን። የሰማይ አባት ሆይ፡ ዛሬ ምሽት ልቦችን እንድታነጋግር፡ እጸልያለሁ። አገራት እየተናወጡና፡ ነገሮች ባሉበት ሁኔታ እየቀጠሉ ባለበት በዚህ ጊዜ፡ በክርስቶስ መምጣት ጥላ ስር እንደሚኖሩ፡ ያውቁ ዘንድ እርዳቸው። እናም፡ ሆኖም፡ በቸርነትህ…

257 በጣም በድለናል፡ ጀርባህን የሰጠኸንና፡ የተውከን ይመስል ነበር። ነገር ግን፡ አሁንም፡ ልክ በኤደን እንደነበረው፡ የማምለጫ መንገድ ታደርጋለህ። ለኖኅ የማምለጫ መንገድ አደረግህ። ለሙሴ፡ ለዳንኤልና፡ ለዕብራውያን ልጆችም አደረግህ። አንተ፡ ዘወትር መንገድን ታደርጋለህ። እርሱንም የሚያገኙት፡ በእግዚአብሔር ብርሃን ይመላለሳሉ ሕይወትም አላቸው። እርሱን የማይቀበሉት ግን፡ የተፈረደባቸውና የተጣሉ ናቸው።

258 የሰማይ አባት ሆይ፡ ዛሬ ምሽት እዚህ ካሉት መካከል፡ የተጣለ እንዳይኖር፡ እጸልያለሁ። የሚያንጎዳጉድ የእግዚአብሔርን ድምፅ በለሰለሰ ሁኔታ ይሰሙ፡ መንፈስ ቅዱስም በልባቸው ውስጥ፡ “እኔ ነኝ። አትፍሩ። እኔ ነኝ፡” ሲላቸው ይሰሙ። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

259 የመሠዊያ ጥሪውን ለአሥር ደቂቃ ያህል ለጥቂት ጊዜ አቆየዋለሁ። ትንሽ ዘግይቻለሁ። ነገር ግን ቢሊ ከጥቂት ምሽቶች በፊት፡ በወንድም ግሩመር ዘንድ፡ የጸሎት ካርዶችን የሰጠ ይመስለኛል። ትናንት ምሽትም ሲሰጥ ነበር ብዬ እሰባለሁ። እኔ ግን አልጠራኋቸውም ነበር። እኔ… ዛሬ ምሽትም እንደገና የሰጠ ይመስለኛል። ሰጥቶ እንደሆነና እንዳልሆነ አላውቅም፡ ነገር ግን ከእነዚያ ካርዶች አንዳንዶቹን እንጥራ። ወንድም ግሩመር እዚህ አለ? ግሩመር? አይ፡ አይ። ግሩመር። እዚህ አለ? ከየት ነበር የጀመርነው? ከቁጥር… እዚያ ላይ፡ ከቁጥር አንድ አልነበረም የጀመርነው?

260 ትናንት ምሽት፡ የጸሎት ካርዶች አልነበሩንም። እኛ… መንፈስ ቅዱስ በጉባኤው መካከል አልፎ ሰዎቹን ጠራ። ያንን ትወዱታላችሁ? [ጉባኤው፡

“አሜን” አለ።—እርታዒ።] እኔም፡ እወደዋለሁ። እንደዚህ ጠንከር ያለ ስብከት ከሰበኩ በኋላ፡ ምናልባት በዚህ ላይ ትንሽ አመነታ ይሆናል።

261 ለሰዎች የጸሎት ካርድ ሰ—ሰጥቻለሁ፡ ስለዚህ ለዚያ ሰው የመጸለይ ግዴታ አለብኝ። ያ ነው በቃ። የመለየት ስጦታ ባይኖረንም፡ ችግር የለውም። ነገር ግን ለሰውየው የመጸለይ ግዴታ አለብኝ። ልጄ የጸሎት ካርድ ይሰጣል፡ ለ—ለዚያ ሰው መጸለይ አለብኝ። ያ ነው በቃ። ስለዚህ፡ እኔም—እንደዚያ ይሰማኛል። እግዚአብሔር ቢረዳኝ፡ አደርገዋለሁ። ከአካባቢው ከመውጣቴ በፊት፡ ያ—ያንን አደርጋለሁ።

262 አሁን፡ ብዙ ጊዜ መውሰድ አንችልም። እስቲ እንመልከት፡ በዚያ ምሽት፡ ከአንድ እስከ ሃያ-አምስት፡ እንደጀመርን አስባለሁ። አዎ፡ ከአንድ እስከ ሃያ-አምስት። እኔ… ወንድም ግሩመር፡ እዚህ ነህ? ወንድም ግሩመር? ስሙን በትክክል አልጠራሁት ይሆናል። ግን እንደዛ ይመስለኛል። አንድ…

263 ደህና፡ ዛሬ ምሽት ከሌላ ቦታ እንጀምር። እስቲ፡ ከሰባ-አምስት፡ እስከ፡ መቶ እንጀምር። የጸሎት ካርድ ቁጥር ሰባ-አምስት የያዛችሁ፡ እጃችሁን አንሱ። እስቲ እንይ… እሺ፡ ልክ ነው። ጥሩ ነው። እሺ፡ እመቤት፡ ወደዚህ ነይ። ሰባ-አምስት፡ ሰባ-አራት፡ ሰባ-… ሰባ-አምስት ብቻ። አሁን ሰባ-ስድስት፡ ሰባ-ሰባት፡ ሰባ-ስምንት፡ ሰባ-ዘጠኝ፡ ሰማንያ፡ ሰማንያ-አንድ፡ ሰማንያ-ሁለት፡ ሰማንያ-ሦስት፡ ሰማንያ-አራት፡ ሰማንያ-አምስት፡ ሰማንያ-ስድስት፡ ሰማንያ-ሰባት፡ ሰማንያ-ስምንት፡ እስከ መቶ ድረስ። ወደዚህ ይምጡ። ቢሊ ፖል የት አለ? ይቅርታ። እሺ። ሂድ፡ ወደዚያ ውረድ። ወደ ጸሎት ሰልፉ እስኪገቡ ድረስ አንዳንድ አሸሮች ይርዱት።

264 አሁን፡ የቀራችሁት፡ ለአንድ አፍታ ወደ እኔ ተመልከቱ። አዎን። ትወዱታላችሁ? አንዳንድ አሸር ወንድሞች ወደዚያ እስከሚወርዱ ድረስ፡ ለአንድ ደቂቃ ያህል፡ በለስለስና፡ በጣፋጭ ዜማ እንዘምር። ኦህ፡ አመሰግናለሁ። እዚያ፡ አግኝተዋቸዋል፡ ስለዚህ… ሰልፉ እንዳይመሰቃቀል ነው። ለእነዚህ ሰዎች መጸለይ እፈልጋለሁ። ከዚያም፡ ነገም፡ ምናልባት ልክ እንደዚሁ ለታመሙት እንጸልያለን፡ እንዲህም እያለ፡ ታላቁ ሰብሰባ እስኪጀምር ይቀጥላል። እኔ…

265 ምናልባት ወንድም ሮበርትሰም፡ እዚያ በቦታው የጸሎት ሰልፍ፡ ይኖረው ይ—ይሆናል። ምናልባት ሁለታችንም በአንድነት ብናደርግ፡ አንዱን በአንድ በኩል፡ ሌላው ደግሞ በሌላ በኩል ብዬ አስቤ ነበር። ነገር ግን እ—እርሱ ይህን ይፈልግ እንደሆነና እንዳልሆነ አላውቅም። አላናገርኩትም፡ መጀመሪያ ባናግረው ይሻላል፡ እያችሁ። ወንድም ኦራል ድንቅ ወንድም ነው፡ እውነተኛ የክርስቶስ አገልጋይ ነው። እርሱም ይህን ለማድረግ ትሑት ነው፡ ነገር ግን እኔ ራሴን እንደዛ ያለ ሰው ጋር ዝም ብዬ መጨመር አልፈልግሁም፡ እያችሁ። ስለዚህ ዝም ብዬ ብተወው ይሻላል። እንግዲህ፡ እርሱ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ናና እርዳኝ፡” ብሎ ቢጠይቀኝ፡ ያ—ያንን በማድረጌ ደስተኛ እሆናለሁ። አሁን፡ ግን፡ እርሱ ትሑትና በጣም ጣፋጭ ወንድም ነው። እንዳደርገው፡ ቢጠይቀኝ፡ በእርግጥ፡ አደርገዋለሁ። ነገር ግን መጀመሪያ፡ እርሱ እንዲጠይቀኝ እፈልጋለሁ፡ እያችሁ። ስለዚህ ጉዳይ ምንም ባልል ይሻላል። እናንተም

አሁን፡ ለእርሱ እንዳትነግሩት። እርሱ ብቻ ይ—ይጠይቀኝ፡ ያኔ ደህና መሆኑን አውቃለሁ። አያችሁ?

266 አ—አሁን ግን እንመለከታለን። ሰንት... ደህና፡ አሁን፡ እስቲ እንይ። በህንጻው ሰንት የጸሎት ካርዶች አሉ? እስቲ እጃችሁን አሳዩኝ። ኦህ፡ ገና ብዙ ናቸው፡ ምናልባት ተጨማሪ ሃምሳ ያህል። አርባ፡ ሃምሳ ተጨማሪ፡ ሊሆኑ ይችላሉ። ኦህ፡ አዎ፡ ምናልባት ተጨማሪ ሰላሳ። መልካም። አ—አሁን እናገኛቸዋለን...

267 እንጠራቸዋለን። አሁን እ... ካልተጠራችሁ፡ ካርዳችሁን ብቻ ያዙ። አያችሁ፡ አሁን አሰር ሰዓት ከአሥር ደቂቃ ሆኗል፡ ነ—ነገ ጠዋት ሰንበት ትምህርት ቤት እንድትገኙ እፈልጋለሁ። ምናልባት ነገ፡ ሁለት አገልግሎቶች ሰላሉን፡ ያሉንን ካርዶች ሁሉ ልንጨርሰ እንችላለን፡ ከ—ከዚያም ለሰኞ እንደገና በአዲስ እንጀምራለን።

268 ሰኞ ምሽት የት ነን? ኦህ፡ እዚያ ታች፡ በቱሰን፡ ነን። አሁን ወደ ቱሰን ወደሚደረገው ሰብሰባ፡ መምጣትን አትርሱ። ከቱሰን የመጣ ሰው እዚህ አለ? አዎ። እርግጥ ነው። የዓለም የአትክልት ሰፍራ፡ በእርግጥም፡ የዚያ አገር ሰው መሆን ነበረብህ። ወንድም ካርል ዊሊያምሰ ከነዚህ ቀናት በአንዱ፡ በዚህ ምክንያት ይጣላኛል ይወቅሰኛል። መጀመሪያ እዚህ በመጣሁ ጊዜ፡ ተቀናቃኝ ከተሞች ነበሩ፡ አሁንም እንደዛው እንደሆኑ አያለሁ።

269 ለዚህ ተላምጃለሁ። እዚያ አገራችን ያለው፡ የቤዝቦል፡ ወይም የቅርጫት ኳሰ ቡድናችን፡ እነዚያ ተቀናቃኝ ከተሞች፡ ጄፈርሰንቪልና ኒው አልባኒ፡ ኦህ፡ ማይ፡ ማይ፡ ማይ! ዊው! ጨዋታ በሚኖርበት ምሽት፡ ትልቅ ግጭት የማይፈጠርበት ጊዜ ቢኖር፡ ሌላ የት ሊሆን እንደሚችል አላውቅም።

270 በቱሰንም፡ ሁልጊዜ፡ እንደዚያ እንደሆኑ አውቃለሁ። ነገር ግን ፊኒክሰ ከቱሰን በብዙ-እጥፍ አድጋለች ብዬ፡ አምናለሁ፡ ምክንያቱም... ቱሰን፡ የፊኒክሰን አንድ-ሦሰተኛ ያህል እንኳ የምትሆን አይመሰለኝም። ነገር ግን...

271 እዚያ አንዳንድ፡ ጥሩ ቅዱሳን ሰዎች ሰላሉ፡ እርግጠኛ ሰለሆንኩ፡ ወደዚያ እንወርዳለን። በዓለም ዙሪያ በሄድኩበት ሁሉ፡ እሰከ አፍሪካ ጫካዎች ድረሰ እንኳ፡ አሁንም አገኛቸዋለሁ። ኦህ፡ ማይ! ባለቤቴ መጥታ እንዲህ የሚለውን መዝሙር አንድ ምሽት ብትዘምርላችሁ ደሰ ባለኝ ነበር፡ “ከምሥራቅና ከምዕራብ፡ ከሩቅ አገሮች ይመጣሉ” የሚለውን። አሁን፡ ይህንን ሰናገር ግን ተነሥታ ሾልካ ትወጣለች።

272 ሰለዚህ፡ ወንድም ሮዝን በጣም ትፈራዋለች። ወንድም ሮዝ፡ “እህት ብራንሃም እዚህ አለች። ወደ መድረክ ወጥታ፡ አንዲት ቃል እንድትናገር እናደርጋለን” አለ።

273 እሷም፡ “ልቤ አሥራ አምሰት ጊዜ ያህል ትርታ አምልጦታል” አለች። “ራሴንም ዝቅ አደረግሁ፡” አለች። እንዲህ አለች፡ “ቢል፡ እርሱ በየትኛውም ሰብሰባ ላይ ካለ፡” “በእርግጥም እደበቃለሁ፡” አለች። እሷ በጣም ዓይናፋር ናት። ሰለዚህ፡ ቤት ሰገባ ወሬውን እ—እ—እሰማዋለሁ።

274 እዚህ ያላችሁ ወጣት ሰዎች... ይህንን የምናገረው፡ እሷ እዚህ ሰላለች አይደለም። እናንተና የሚያውቋት ሁሉ፡ ያንን ታውቃላችሁ። በዚህ ሕንፃ ውሰጥ

ያለ እያንዳንዱ ወጣት፡ ሚስት ሲያገባ፡ ባለቤቱ ለእርሱ እንዲህ ጣፋጭ እንድትሆንለትና፡ እኔና ባለቤቴ በእነዚህ ዓመታት በደስታ አብረን እንደኖርነው፡ እናንተም በደስታ አብራችሁ እንድትኖሩ እመኛለሁ። ለብራንሃም ቤተሰብ የሚሰጥ ምስጋና ካለ፡ ለሷ ይሁን። እሷ ንግሥት ናት። በእርግጥም ናት። አንዱ ነገር፡ እርሷ እውነተኛ እናት ናት። ደግሞም የምትታገሠውን ነገር ተመልከቱ፡ እያችሁ፡ ከዚያም፡ ደህና፡ ም——ምን እንደሆነ ብታውቁ ትገረማላችሁ። ለምን፡ ቀንና ሌሊት፡ ሰዎች በደጃፋችን ናቸው። እሷም እዚያው፡ ቤት ውስጥ፡ በእኔና በሕዝቡ መካከል ትቆማለች፡ እያችሁ። ስለዚህ ያ በእውነት ከባድ ሥራ ነው።

275 ስለ ትንሹ ቢሊ ፖልም፡ ብዙ ጊዜ፡ እሰባለሁ፡ እናቱ በሞተች ጊዜ፡ ገና ሕፃን እያለ፡ እዝዬው እዞር ነበር። ዶክተር አዴር፡ “አንተ እንግዳ ሰው ነህ” ይለኝ ነበር። እኔም መንገድ ላይ ሆኜ፡ እናቱን እየፈለገ ሲያለቅስ፡ አዝለውና እዞር ነበር፡ አየሩም ቀዝቃዜ ነበር፡ ታውቃላችሁ፡ **እንዲህ**፡ በትከሻዬ ላይ ይዤው እዞር ነበር።

276 እውነተኛ ጡጦ ለመግዛት... የሚበቃ ገንዘብ አልነበረኛም። የኮካ ኮላ ጠርሙስ ላይ የጡጦ ላስቲክ አድርጌለት ነበር። እንዲሞቅልኛም፡ **እዚህ** ጋር በክንዴ ስር፡ እይዘው ነበር። በጣም ሲያለቅሰብኛም፡ እጄን ሰድጄ፡ ጡጦውን በአፉ እከትለት ነበር። ለጥቂት ጊዜ እንዲጠባ አደርገውና፡ ጠርሙሱን መልሼ **እዚህ** ጋር አኖረዋለሁ። ሰውነቴም ሁሉ፡ ወተት ሆኖ ነበር፡ ታውቃላችሁ።

277 እንዲህ ይዤው፡ ጉዞዬን እቀጥል ነበር፡ ታውቃላችሁ፡ እወስደው ነበር። ሌሊት ሌሊት፡ ማይ፡ ማይ፡ እንዴት አድርጌ ላሰተኛው እንደምሞክር፡ ለታመሙት ለመጸለይ ስሄድ ደግሞ እንዲጠብቅልኝ የሆነ ሰው እፈልግ ነበር። በአንድነት ረጅም መንገድ ተጉዘናል። ጌታም በዚሁ ሁኔታ እንዲጠብቀን ተስፋ አደርጋለሁ።

278 ትናንትና፡ ትንሹን ልጁን አዝሎት አየሁት። እኔም እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ “ቢሊ፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ አንተም እንዲህ ነበርክ።” እንግዲህ፡ እኛ ማድረግ ያለብን፡ እንደዚህ ነው፡ ከመንገዱ ገለል ብለን ለሌሎች ዕድል መስጠት። የጌታ ስም የተባረከ ይሁን።

279 “አንበሳ ሲያገሳ፡ እያችሁ፡ የማይፈራ ማን ይኖራል? ” “እግዚአብሔርንም መፍራት የጥበብ መጀመሪያ ነው።” ልክ ነው? ጠቢቡ ሰው ያለው ይህንን ነው። “እግዚአብሔርን መፍራት።”

280 አሁን፡ እዚያ የጸሎት ሰልፍ ላይ፡ የቆማችሁት ሰዎች፡ ስለ እናንተ ምንም እንደማላውቅ የምታውቁ ሁላችሁ፡ እጆቻችሁን አንሱ። እያንዳንዳችሁ። ያ ቸሩ የሰማይ ጌታ ፈራጄ ይሁን፡ በሕይወቴ እስከማውቀው ድረስ፡ ከእነርሱ መካከል አንዱንም አይቼ አላውቅም። እነርሱ ምናልባት በጉባኤው መካከል ተቀምጠው፡ አይተውኝ ይሆናል።

281 አሁን፡ እዚያ በጉባኤው መካከል፡ ስለ እናንተ ምንም እንደማላውቅ የምታውቁ ስንቶች ናችሁ? ነገር ግን፡ ሆኖም፡ ታምማችኋል፡ ልክ እንደ መጀመሪያዋ ሴት፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የእርሱን ልብስ ጫፍ ብትነኩ፡ እግዚአብሔር፡ እናንተን እንድጠራችሁ ይነግረኛል ብላችሁ፡ ታምናላችሁ? ኦህ፡ ማይ! ረጅም ሰዓት የሰበክሁት ያለምክንያት አይደለም። እንዲህ ያለ፡ እምነት ያለው ጉባኤ፡ ይህንን ሊያደርግ ይገባዋል።

282 ይህች እመቤት ናት? አሁን፡ እነሆ አንዲት እመቤት እዚህ አለች። ዛሬ ምሽት እንደ እንግዶች ተገናኝተናል፡ አሁን ግን እዚህ ቆማለች። እርግጥ ነው፡ ምናልባት ታማ ይሆናል፡ ወይም ደግሞ ሌላ ችግር ይኖርባት ይሆናል።

283 አያችሁ፡ እግዚአብሔር የታመሙትን ከመፈወስ ውጭ ሌሎች ነገሮችንም ያደርጋል፡ ታውቃላችሁ። ስለዚህ… ሞኞታችንን ወይም መሻታችንን ባይሆንም እንኳ፡ አስፈላጊ ነገሮቻችንን፡ ፍላጎታችንን ሁሉ፡ ሊያሟላልን ቃል ገብቷል። አሁን ይህንን አንድ ነገር፡ እንድታስቡ እፈልጋለሁ፡ ቤት ስትሄዱ፡ ወይም ከዚህ በፊት አንብባችሁት የማታውቁ ከሆነ፡ ዮሐንስ ምዕራፍ 4ን አንብቡና፡ ተ—ተመልከቱ። አሁን፡ እዚህ ጋር፡ አሁን፡ አላስታውስም…

284 ይህንን ልናገር። ይህ አገልግሎት፡ ወይ እርሱ ወደ ቤት ሊወስደኝ ነው ወይም ደግሞ ወደ ላቀ ደረጃ ሊያሸጋግረኝ ነው፡ ብዬ አምናለሁ። ልክ በ—በዚህ በመጨረሻ-ዘመን ላይ ነው። ወይም፡ ወደ ባሕር ማዶ ወይም ደግሞ ወንጌሉ ወዳልተሰማበት ስፍራ ሊልከኝ ነው። አያችሁ? የሆነ ነገር ሊፈጠር ነው። ይህንን ብቻ አስታውሱ።

285 እና፡ አዳምጡ፡ እኔ የቴፕ ነጋዴ አይደለሁም። ነገር ግን እነዚህን ቴፖች የሚቀርጽ አንድ ጥሩ ወንድም እዚህ አለኝ፡ እርሱም ሚስተር ማጓየር ነው። ጄምስ ማጓየር መሰለኝ። እናም እ—የሚስቱ-አባት-አማቹም፡ ወንድም ሶስማን እዚያ ኋላ አሉ፡ እነርሱ ከእነዚህ ቴፖች ጋር ናቸው። የቴፕ መቅጃ ካላችሁ፡ እኔ… ስለ እሱ አሁን ምንም አልናገርም፡ ምክንያቱም እኔ ስለ እርሱ ምንም አላውቅምና። ነገር ግን ከእነርሱ ቴፕ ገዝታችሁ የምታውቁ ከሆነ፡ **ጌቶች ሆይ፡ ስንት ሰዓት ሆነ?** የሚለውን ቴፕ ግዙ። ያንን ቴፕ አዳምጡት፡ **ጌቶች ሆይ፡ ስንት ሰዓት ሆነ?** በጸሎት መንፈስ ሆናችሁ አጫውቱት፡ ያኔ ለእኔ መጸለይ ትጀምራላችሁ። አያችሁ? ያኔ… ምክንያቱም፡ ያኔ ዛሬ ምሽት እዚህ በ—በምን ዓይነት ወሳኝ ሁኔታ ውስጥ እንደቆምኩ ታያላችሁ። አሁኑኑ፡ እዚህ፡ በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ፡ እንደቆምኩ ብታውቁ ኖሮ! አያችሁ? ነገር ግን መቀጠል አለብኝ። አሸናፊ በጭራሽ ተስፋ አይቆርጥም፡ ተስፋ የሚቆርጥም ደግሞ በጭራሽ አያሸንፍም። ልክ ነው። የሰበክሁትን በተግባር ማዋል አለብኝ። አያችሁ? አሁን፡ እግዚአብሔርን እምናለሁ። አሁኑኑ እምነዋለሁ።

286 አሁን፡ ነገሩ በዚህ መሠረት ላይ ነው። እ—አሁን፡ እኔ ጌታ ኢየሱስ ሆኜ እዚህ ብቆም፡ ይህችም እመቤት ታማ ብትሆን፡ እኔ ጌታ ኢየሱስ ብሆን ኖሮ ልፈውሳት እንደማልችል ታውቃላችሁ። ምክንያቱም ቀድሞውኑ አድርጌዋለሁና፡ ላደርገው አልችልም ነበር። አሁን፡ ይህ እውነት መሆኑን ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።] አያችሁ? በእርግጠኝነት።

287 እርሱ አስቀድሞ ኃጢአትን ሁሉ ይቅር ብሏል። የታመመውንም ሁሉ አስቀድሞ ፈውሷል። በቀራንዮም ያንን ደም መድቧል። ዋጋው ቀድሞውኑ ተከፍሏል። ሁሉም ተከፍሏል። እናንተ ማድረግ ያለባችሁ ብቸኛው ነገር እርሱን መቀበል፡ ማመንና መቀበል ብቻ ነው። መጀመሪያ ካላመናችሁበት ደግሞ ልትቀበሉት አትችሉም። አያችሁ? በወንጌሉ እመኑ።

288 አሁን ግን፡ እርሱ እዚህ ቆሞ ቢሆን፡ ከአምስት ወይም ከስድስት ዓመታት በፊት ቸሩ ጌታ ወንድምና እህት ዊሊያምስ እንዲገዙልኝ ባደረገው፡ በዚህ ሱፍ

ተጎናጽፎ እዚህ ቢቆምስ? እርሱ በዚህ ሱፍ፡ እዚህ ቢቆም፡ ይህችም እመቤት እዚህ ብትቆምስ?

289 አሁን፡ በእጁ ላይ ጠባሳ ቢኖረውና፡ እንዲህ ቢል፡ “እኔ መሲሑ እንደሆንኩ፡ አያችሁ። እኔ… ጠባሳዎቹን አያችሁ? ግንባሬንም ተመልከቱ” ቢል። አሁን፡ ማንኛውም አስመሳይ ይህን ሊያደርግ ይችላል። ልክ ነው። በዚህ አታውቁትም ነበር። እርሱ እንደዚያ ሆኖ እዚህ ቢቆም ኖሮ፡ እርሱ እንዳልሆነ አውቅ ነበር። እንዳልሆነ አውቅ ነበር።

290 ምክንያቱም፡ እርሱ በሚመጣበት ጊዜ፡ መለከት ይነፋል። እኛ… እርሱ ወደ ምድር እንኳ አይመጣም። እርሱን ለመቀበል፡ በአየር ላይ እንነጠቃለን። አያችሁ? በአየር ላይ ነው የምንገናኘው። “እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል፡ ከእነርሱ ጋር በአንድነት እንነጠቃለን።” እርሱ ወደ ምድር አይመጣም። እኛ በአየር ላይ እንቀበለዋለን።

291 እርሱ ግን፡ እንዲህ አለ፡ “እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ። ከቶ አልተዋችሁም አልጥላችሁም።” እንዴት ሊሆን ይችላል? በሕይወቱ በኩል ነው። እንግዲህ፡ የእርሱ ሕይወት በእኔ ውስጥ ካለ፡ እኔ እርሱን እየወከልኩ ነው ማለት ነው። ከዚያም፡ ያ ደግሞ፡ በእርሱ ውስጥ የነበረው ያው ሕይወት ከሆነ፡ እርሱ ያደረገውን ያንኑ ነገር ያደርጋል።

292 አሁን፡ እዚህ ጋር ልክ እንደ የሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 4 አንድ ወንድና አንዲት ሴት ተገናኝተዋል። ያችን ሴት አገኛት። ከዚያ በፊት አግኝቷት አያውቅም። እሷም ቀድሞ አይታው አታውቅም። እዚያም አብረው፡ ቆሙ። እርሱም ያቺን በውኃው ጉድጓድ አጠገብ የነበረችውን ሴት፡ ችግሯ ምን እንደሆነ፡ ነገራት። ይህን ባደረገ ጊዜ፡ እሷም፡ “ጌታ ሆይ፡ አ—አንተ ነቢይ እንደሆንህ አያለሁ” አለች። ቀጥላም፡ “መሲሑ፡ እርሱም **ክርስቶስ** የተባለው፡ ማለትም፡ ‘የተቀባው፡’ ሲመጣ፥ እርሱ ሲመጣ፡ እነዚህን ነገሮች ሁሉ፡ እንዲነግረን እናውቃለን” አለች።

እርሱም፡ “የማናግርሽ፡ እኔ እርሱ ነኝ” አላት።

293 አሁን፡ እርሱ ትናንት፡ ዛሬ፡ ለዘላለምም ያው ከሆነ፥ እርሱ አካላችንን፡ ይጠቀማል… አካላችንን ይጠቀመዋል። “እርሱ የወይን ግንድ ነው። እኛ ቅርንጫፎች ነን።” እንግዲያውስ፡ ያ መንፈስ በእርሱ ውስጥ በነበረበት ጊዜ እንዳደረገው አሁንም ልክ እንደዛው ያደርጋል። ልክ ነው? ይህ እንድታምኑ ያደርጋችኋል? እንደዛ ከሆነ፡ “አሜን፡” በሉ። [ጉባኤው፡ “አሜን፡” አለ—አርታዒ።]

294 አሁን፡ እመቤት ሆይ፡ እኔ አንቺን አላውቅሽም፡ እስከማውቀው ድረስ፡ በሕይወቴ አይቼሽ አላውቅም። በእርግጥ፡ ምናልባት መንገድ ላይ ወይም በስብሰባዎች ላይ፡ አይተሽኝ ይሆናል። ነገር ግን ይህ መጀመሪያ የምንገናኝበት ጊዜ ነው።

295 አሁን፡ የ—የሚያስፈልግሽ ፈውስ ከሆነ፡ ደህና፡ እኔ፡ ማድረግ የምችል ከሆነና፡ የሆነ መንገድ ቢኖረኝ፡ አደርገው ነበር። የገንዘብ ችግርም ከሆነና፡ ል—ልረዳሽ የምችል ከሆነ፡ አደርገው ነበር። ወይም ደግሞ ምናልባት፡ ለሌላ ሰው ቢሆንና፡ እንዲህ ብትይ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ስለ ልጄ፡ ወይም ሰ—ስለ ሴት ልጄ፡ ስለ እህቴ፡ ወይም ስለ አባቴ፡ እንድትጸልይልኝ መጥቻለሁ” ብትዪ፡ ወይም ሌላ ሰው። አያችሁ፡ የምችለውን ሁሉ፡ አደርግ ነበር።

296 የ—የቤተሰብ ችግር ቢኖርብሽ፡ እንዲህ እል ነበር፡ “ከዚህ ሰፍራ ውጭ የሆነ ቦታ አንቺንና ባለቤትሽን፡ አንድ ላይ፡ ማግኘት እፈልጋለሁ፡ አየሽ፡ በዚህም ሁለታችሁንም እነጋግሬ ስህተቱ የት ጋር እንደሆነ ማየት እችል ዘንድ ነው።” ከዚያም፡ መንፈስ ቅዱስ ሲገልጥ፡ “ቆይ አንድ ደቂቃ። **በዚህ** በሆነ ጊዜ **ይህንን** አድርገሃል” እላለሁ። ያ ነገሩን ይቋጨዋል። ያንን መካድ አትችሉም። አያችሁ? “አንቺ ደግሞ **እዚህ** ጋር እንዲህ አድርገሻል፡” እላለሁ፡ ያኔ፡ ነገሩ ይቋጫል፡ አየሽ። አሁን፡ ከእዚያው ትጀምራላችሁ። አያችሁ? በዚያ መንገድ፡ ነገሩ ይጠናቀቃል።

297 አሁን፡ የሆነ ዓላማ ኖሮኝ እያወራሁሽ እንደሆነ ታውቂያለሽ። ስሰብክ ነበር። አየሽ? እ—አሁን ደግሞ ራሴን ለ—ለሌላ ነገር በቅባት ውስጥ እያዘጋጀሁ ነው፡ አየሽ፡ ይህም መንፈስ ቅዱስ በመለኮታዊ ስጦታው በእኔ ላይ መጥቶ ይሠራ እንደሆነ ለማየት ነው፥ ይኸውም፡ ሁለቱ ንቃተ ሕሊናዎች አብረው በመሆን፡ የእግዚአብሔርን ጸጋ የሚሰጡኝና ራእዮችን እንዳይ፡ ምን እየሆነ እንደሆነ፡ ምን እንደሚሆንና፡ ምን እንደነበረ እንዳይ የሚያደርጉኝ ናቸው።

298 እውነት መሆኑን ወይም አለመሆኑን ታውቂያለሽ። ቢያንስ አምስት መቶ፡ አየሽ፡ ወይም ወደ ሦስት መቶ፡ በሚጠጋ፡ ሕዝብ ፊት ነው የቆምሽው። አየሽ? እ—እናም እንደምታውቂው—ያኔ... እውነት መሆኑንና አለመሆኑን ታውቂያለሽ። እ—እውነት ከሆነ፡ እርሱ እግዚአብሔር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፡ “ከእናንተ መካከል፡ መንፈሳዊ ወይም ነቢይ ቢኖር፡ የተናገረውም ቢፈጸም፡ ያኔ ስሙት” ይላል። አያችሁ? አሁን፡ “ካልተፈጸመ ግን፡ አትስሙት።”

299 አሁን፡ ይህች እመቤት ለምን እዚህ እንደቆመች ምንም አላውቅም። ነገር ግን አሁን መንፈስ ቅዱስ ይምጣና፡ ካልነገረን እንመልከት። አያችሁ? ያ ደግሞ ጌታችን ካደረገው ጋር አንድ ዓይነት አይሆንም! እርሱ እራሱ እዚህ ቢቆም ሊያደርገው የሚችለው ያንኑ ብቻ ነው፡ ምክንያቱም፡ አስታውሱ፡ እርሱ ነው። እርሱ ነው። እኔ አይደለሁም። እኔ አላውቃትም። አላውቃትም ብዬ፡ እየተናገርኩ ነው። ስለዚህ፡ እርሱ ኢየሱስ ያስፈልጋል።

አሁን፡ በእርግጥ፡ ይህች እመቤት በመንፈሷ ውስጥ ድንቅ የሆነ ስሜት አላት።

300 እጇን ስላነሳች ብቻ አይደለም። እናንተ በስብሰባዎች ላይ፡ ሰዎች እጃቸውን ሲያነሱ አይታችኋል፡ **እንደዚህ** ያደርጋሉ፡ መንፈስ ቅዱስ ግን ወዲያውኑ ምን እንደነበሩ ይነግራቸዋል። አያችሁ? ልክ ነው። ያ ምንም ማለት አይደለም። ሲጮሁና እልል ሲሉ ትሰማላችሁ፥ በዚያው ቅጽበት ግን፡ “አንተ **ከዚህ** ሰው ሚስት ጋር እየኖርክ ነው፡” ትላቸዋለህ፡ ምክንያቱም **እዚህ** ጋር፡ አይተኸዋልና። እንግዲህ፡ ታውቃላችሁ። በስብሰባዎች ላይ እንደዚህ ያሉ ነገሮችን አይታችኋል፡ ያ ደግሞ እንዴት በራሱ ምንም ትርጉም፡ እንደሌለው አይታችኋል።

301 ነገር ግን ይህች እመቤት ለመንፈሷ መልካም ስሜት ያለ ይመስላል። አሁን፡ ይህች እመቤት በሆነ ችግር እየተሰቃየች ነው። ስትመገብ፡ እያየኋት ነው። አሁን በፊቴ፡ በጠረጴዛ ላይ ሆና፡ የሆነ የምግብ መቆጠብ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ስታደርግ፡ የሆነ የተለየ-ዓይነት የአመጋገብ ሥርዓት ስትከተል ይታየኛል። በትክክል። እውነት ነው? [እህት፡ “ልክ ነው” አለች።—እርታዒ።]

እንግዲያውስ ሕዝቡ እንዲያየው እጅሽን አንሺ። አያችሁ? በፊቴ ያለችው እመቤት፡ የሆነ ነገር ስታደርግ አየኋት። የፈለገው ቢሆን፡ በቴፕ ተቀርጿል። አያችሁ? እሺ። እንግዲህ፡ ለምን እንደሆነ ታውቁ ዘንድ… እርሷ ጥሩ ሰው ናት።

302 ለአንድ አፍታ ተመልከቱ። አሁን መንፈሱ እየቀባ ነው። አሁን፡ ሁሉም ሰው በጣም በአክብሮት ይቀመጥ። መጸለያችሁን ቀጥሉ። በጸሎት ሁኑ፡ ምክንያቱም አሁን በጉባኤው ላይ ሲንቀሳቀስ አይቼዋለሁና። አያችሁ? አሁን በጣም በአክብሮት ሁኑ።

303 ለማነጋገር ያህል፡ እመቤቲቱን እንደገና እንመልከታት። እርሱ የነገረሽን ማንኛውንም ነገር… አዎ። ይኸውና። ጠረጴዛ ጋ ነው። የ—የጨጓራ ችግር ነው። የሆነ የኢንፌክሽን ዓይነት ወይም በጨጓራ ውስጥ ያለ የሆነ ነገር። ሐኪም ይህንን ሲመለከተው ቆይቷል። ይህ ችግር ካለብሽም፡ ረጅም ጊዜ፡ ሆኖሻል። እናም፡ በአንድ ወቅት ደግሞ፡ "የጨጓራ፡ ቁስለት፡" ተብሎ ነበር። አሁን ደግሞ ሐኪሙ አንድ ነገር አለ። ምን ነበረ? "ዲደነም፡ ዲደነም። ዲደነም፡" ያንን ሲል ሰማሁት። አያችሁ? ያ ልክ ነው። በትክክል ልክ ነው። ሰምሽ ወይዘሪት ማክሮ ይባላል። በትክክል። ሂጂ አሁን፡ በፍጹም ልብሽ እመኚ።

ታምኚያለሽ?

304 እዚያ ኋላ ተቀምጠህ፡ እንደዚያ ካለቀሰክ በኋላ፡ ወዳጄ፡ ካመንክ፡ የነበረብህ የሳንባ መኮማተር አሁን በጣም የተሻለ ሊሆንልህ ይገባል። አሁን ሁሉም ነገር ደህና ነው። እሺ፡ ያ አድርጎታል። አሜን።

እርሱ ምንን ነካ?

305 ከእርሱ በስተጀርባ በሁለተኛው ረድፍ ላይ፡ ያለኸው ሰው፡ የደም ሥር መጠጠር ያለብህ፡ አንተም ብታምን ትፈወሳለህ፡ ጌታዬ!

306 እርሱ ምንን ነካ? ያ ብርሃን እዚያ ተንጠልጥሎ አይታያችሁምን? ያንን አምበር ብርሃን **እዚያ** እዩት። ሰውየውን አላውቀውም፡ በሕይወቴም አይቼው አላውቅም። በጌታ በኢየሱስ ብቻ እመን።

307 አሁን፡ የሆነ ቦታ፡ እዚህ አንገቱ የተጣመመ፡ አንድ ሕፃን አለ። **ይኸውና**። አላውቃትም። እመኚ፡ እህቴ። ብታምኚ፡ የሕፃኑ አንገት ይቃናል።

እርሷ ምን ነካች? ሃሌሉያ።

308 ስለ አንገት ሌላም ነገር አለ። አይቼዋለሁ። አንዲት ሴት ናት። የት እንዳለች ግን ማየት አልቻልኩም ነበር። አዎ። እዚህ ተቀምጣ፡ እያለቀሰች ነው። ወይዘሮ ራይሊ፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመኚ፡ አንገትሽ ይፈወሳል። እመኚ።

309 ሴቲቱን አላውቃትም። በሕይወቴም አይቻት አላውቅም። ማድረግ ያለብሽ ብቸኛው ነገር በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ ነው። ይህን ታምኚያለሽ? እምነት ይኑርሽ።

310 ጌታዬ፡ አላውቅህም። እስከማውቀው ድረስ፡ እርስ በርስ እንግዳ ነን። ኢየሱስ ክርስቶስ ችግርህ ምን እንደሆነ ሊነግረኝ እንደሚችል ታምናለህ? ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ታውቃለህ፡ አይደል? አሁን በፍጹም ልብህ ማመን ብትችል! መንፈሱ ወደ ጉባኤው መሄዱን ቀጥሏል። እዚያ ያለችው ባለቤትህም ጭምር፡ ደህና እንደምትሆን ታምናለህ? [ወንድም፡ "አዎ" አለ።—እርታዒ።] የዐይን ሕመም፡ በዐይን ሕመም ትሰቃያለች። ታምናለህ?

የዚህ አካባቢ ሰው አይደለህም። አይ። በሆነ መንገድ ብዙ ውኃ ካለበት ቦታ፡ ነው የመጣኸው። የባሕር ዳርቻ ከተማ ነው። ካሊፎርኒያ፡ ሎስ አንጀለስ ነው። ሚስተር ቦውማን፡ ተመለስና፡ ተፈወስ። ኢየሱስ ክርስቶስም ደህና ያደርግሃል።

311 ታምናላችሁ? አሁን፡ ብታምኑ፡ እያንዳንዳችሁ አሁኑኑ መፈወስ ትችላላችሁ። ይህን ታምናላችሁ?

312 በጸሎት ሰልፍ ላይ ያላችሁትስ፡ እናንተም፡ ታምናላችሁ? እምነት ይኑራችሁ፡ አትጠራጠሩም። ለአንድ ደቂቃ፡ በፍጹም ልባችሁ እመኑ።

313 ይህች እመቤት፡ እሷ ጋ የቆምኩበት ምክንያት፡ በጣም አሰጊ ሁኔታ ላይ ስለሆነች ነው። የሆነ ነገር ካልተደረገላት በቀር ይህች ሴት አሁኑኑ ትሞታለች፡ ምክንያቱም የሞት ጥላ አጥልቶባታል። ያንን ጥቁር ጥላ በላይዋ ላይ ታያላችሁ?

314 በነገራችን ላይ፡ ታውቃላችሁ፡ ልክ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ሁሉ፡ በሰዎች ላይ ያረፈውን ያንን የሞት ጥላ፡ በካሜራ ፎቶግራፍ እንዳነሳን ታውቃላችሁን? እኛ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰቅለነዋል፡ በአንዲት ሴት ላይ፡ እንደ ዓውሎ ነፋስ ተንጠልጥሎ የሚታይ፡ ትልቅና፡ ጥቁር-ነገር ነው። ፎቶውን እንዳታነሳ ብለው ነበር። መንፈስ ቅዱስ ግን፡ "አሁኑኑ አንሺው" አላት። ፎቶውንም አነሱት፡ እዚያውም ተገኘ። አያችሁ? በሁለቱም ወገን፡ እዚህ አለ። ልክ እዚያው ተንጠልጥሏል።

315 እናንተ የተብርናክል ሰዎች፡ እዚህ ያላችሁት፡ አንዳንዶቻችሁ፡ ወንድም ፍሬድ እና ሌሎቻችሁ፡ ያው ነገር አሁን በዚህች ሴት ላይ ተንጠልጥሎ ይታያል።

316 የሽንት ፊኛ፡ ካንሰር አለባት፡ ልክ ነው። በትክክል። ልክ ነው? ይህ እውነት ከሆነ እጅሽን አንሺ። አያችሁ? አሁን ምንም ነገር ሳይባል፡ ያ ጨለማ ተወግዷል። አያችሁ፡ ይህንን ያደረገው፡ የእሷ እምነት ብቻ ነው። ሂጂ፡ እመኚ። አሜን። አሜን። አትጠራጠሪ። ሂጂና በፍጹም ልብሽ እመኚ።

317 የልብ ህመም ብዙ ሰዎችን ይገድላል፡ ነገር ግን ካመንክ አንተን አይገድልህም። አሜን። "ጌታ ይመስገን፡" እያልክ፡ ሂድ። ሂድና ተፈወስ። እሺ።

318 ዲያብሎስ ይህ የአርትራይተስ የመገጣጠሚያ ህመም ዕድሜ ልክሽን እንዲኖርሽ ይፈልጋል። ነገር ግን በፍጹም ልብሽ ካመንሽ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሻል። ታምኚያለሽ? እግዚአብሔርን እያመሰገንሽ፡ መንገድሽን ቀጥዪ።

319 በፍጹም ልብህ ታምናለህ? ሄደህ እራትህን መብላት ትችላለህ፡ ያ የጨጓራ ህመምህም ይለቅሃል። ዝም ብለህ "ጌታ ይመስገን!" እያልክ ሂድ፡ ሂድና፡ በፍጹም ልብህ በእርሱ እመን።

320 አንተም፡ ደግሞ፡ የጨጓራ ህመም ነበረብህ። በፍጹም ልብህ እመንና፡ ሂድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስም ይፈውስሃል። እሺ።

321 ለምን እንዲህ ትፈራለህ? በጭንቀት እየተሰቃየህ ነው። ሊጥልህ ምንም አልቀረውም፡ አእምሮህም ሊዝል ደርሶ ነበር፡ ሰይጣን እየዋሸህ ነው። አሁን ግን አብቅቷል። ታምነኛለህ? ሂድና፡ "ጌታ ይመስገን፡" በል!

322 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እህታችንን እንድትፈውሳትና ደህና እንድታደርጋት፡ በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ። አሜን።

323 እህቴ፡ እያመንሽ፡ ነይ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ለፈውሷ እጄን እጭንባታለሁ።

324 ወንድሜ፡ ና። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ለፈውሱ በወንድሜ ላይ እጄን እጭናለሁ። አሜን።

325 የሚያምን ልብ ኖሯችሁ፡ እጃችሁን የምታነሱ ሰንቶቻችሁ ናችሁ? አሁን ያንን እጃችሁን አጠገባችሁ ባለው ሰው ላይ ጫኑ። "አሞጽ እንዲህ ይል ነበር?" ትሉ ይሆናል፡ በእርግጥም ይል ነበር። ያ የጌታ ቃል ነው። እጃችሁን አንሰታችኋል፡ ታምናላችሁም።

326 ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ "ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል። በድውዮች ላይ እጃቸውን ቢጭኑ..." እንዲያውም ስለእነርሱ እንደሚጸልዩ አላለም። "በድውዮች ላይ እጃቸውን ቢጭኑ፡ እጁ ብቻ ቢጫንባቸው፡ ይፈወሳሉ፡" አለ።

እንጸልይ።

327 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ንጉሡ በድምፁ አገሳ፡ "ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል። በድውዮች ላይ እጃቸውን ቢጭኑ፡ ይፈወሳሉ።" ጌታ አምላክ ሆይ፡ እያንዳንዱ ጋኔን ይጮኽ። እያንዳንዱ ሕመም ይወገድ። ዲያብሎስ ይሸነፍ፡ የእግዚአብሔር ልጆችም ዛሬ ምሽት ከዚህ ሕንፃ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ድልና ኃይል ወጥተው ይሂዱ።

328 እመኑት። በትክክል። ዝም ብላችሁ ከእርሱ ጋር ጸኑ። እጅህን በአንድ ሰው ላይ በመጫን፡ እንዲህ፡ "ጌታ ሆይ፡ ፈውሳቸው፡" በል። እንድትጸልዩ እፈልጋለሁ። እኔ ጸልያለሁ። እናንተ ለአንድ ሰው እንድትጸልዩ እፈልጋለሁ። እ—እናንተም... እንደ እኔ ክርስቲያን ናችሁ። ሁላችንም ክርስቲያኖች ነን። አሁን ለሌላ ሰው ጸልዩ። እነርሱም ለእናንተ እየጸለዩ ነው።

329 አሁን፡ አንድ ሰው ለእናንተ እንዲጸልይ የምትፈልጉት እንዴት ነው? ለእናንተ እንዲጸልዩላችሁ እንደምትፈልጉት ሁሉ ለነርሱም ጸልዩ። "ሌሎች እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ሁሉ፡ እናንተም ለሌሎች አድርጉ።" ልክ እነርሱ ለእናንተ እንዲጸልዩ እንደምትፈልጉት፡ በቅንነት፡ ጸልዩ።

330 "የእምነትም ጸሎት በሽተኛውን ያድናል። እግዚአብሔርም ያስነሳዋል። አለማመን ቢኖርባቸውም፡ ይወሰዳል።" ለምን? "ንጉሥ ያገሳልና። ማን ትንቢት ከመናገር ይቆጠባል? ንጉሥ ሲያገሳስ ማን ከመመስከር ይቆጠባል?" ቃሉ፡ "ትናንትና፡ ዛሬ፡ ለዘላለምም ያው ነው" ይላል።

ወንድም ፉለር፡ ና። እግዚአብሔር ይባርክህ።

63-0119 የእውነተኛ ነቢይ አካሄድ
ፈይዝ ቴምፕል
ፊኒክስ, አሪዞና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡



Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org